# የዮሐንስ ወንጌል

የጌታችንና የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ወንጌል
ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ እንደ ጻፈው።

---

## ምዕራፍ ፩

### ስለ ቃል ቀዳማዊነት

፩በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብ
ሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።
፪ይህም በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ
ነበረ። ፫ሁሉም በእርሱ ሆነ፤ ከሆነውም ሁሉ
ያለ እርሱ ምንም የሆነ የለም። ፬ሕይወት በእ
ርሱ ነበረ፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረ፤
፭ብርሃንም በጨለማ ያበራል፤ ጨለማም አላ
ገኘውም።

### ስለ መጥምቁ ዮሐንስ መላክ

፮ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከ ስሙ ዮሐንስ
የሚባል አንድ ሰው ነበር። ፯እርሱም ሁሉ በእ
ርሱ በኩል እንዲያምን ስለ ብርሃን ይመሰክር
ዘንድ ለምስክርነት መጣ። ፰ስለ ብርሃን ምስ
ክር ሊሆን መጣ እንጂ እርሱ ራሱ ብርሃን
አልነበረም።

፱ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃ
ንስ ወደ ዓለም የመጣው ነው። ፲በዓለም ነበረ፤
ዓለሙም በእርሱ ሆነ፤ ዓለሙ ግን አላወቀ
ውም። ፲፩ወደ ወገኖቹ መጣ፤ ወገኖቹ ግን አልተ
ቀበሉትም። ፲፪ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚ
ያምኑ የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ ሥልጣ
ንን ሰጣቸው። ፲፫እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወ
ለዱ እንጂ ከሥጋዊና ከደማዊ ግብር ወይም ከወ
ንድና ከሴት[፩] ፈቃድ አልተወለዱም።

### ቃል ሥጋ ስለመሆኑ

፲፬ያም ቃል ሥጋ ሆነ፤ በእኛም አደረ፤ ለአ
ባቱ አንድ እንደ ሆነ ልጅ ክብር ያለ ክብሩን
አየን፤ ጸጋንና እውነትን የተመላ ነው። ፲፭ምስ
ክሩ ዮሐንስ ስለ እርሱ ድምፁን ከፍ አድርጎ
ተናገረ፤ እንዲህም አለ፥ "እኔ ስለ እርሱ ከእኔ
በፊት የነበረ ከእኔ በኋላ ይመጣል ያልኋችሁ
ሰው ይህ ነው፥ እርሱ ከእኔ አስቀድሞ ነበረና።"
፲፮እኛም ሁላችን ከሙላቱ በጸጋ ላይ ጸጋን ተቀ
በልን። ፲፯ኦሪት በሙሴ ተሰጥታን ነበርና፤ ጸጋና
እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነልን። ፲፰በአ
ባቱ ዕቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ገለጠልን እንጂ
እግዚአብሔርንስ ከቶ ያየው የለም።

### ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ምስክርነት
(ማቴ. ፫፥፩-፲፪፤ ሉቃ. ፫፥፩-፲፰)

፲፱አይሁድ፥ "አንተ ማን ነህ?" ብለው ይጠ
ይቁት ዘንድ ካህናትንና ሌዋውያንን ከኢየሩሳ
ሌም በላኩ ጊዜ የዮሐንስ ምስክርነት ይህ ነው።
፳እርሱም፥ "እኔ ክርስቶስ አይደለሁም" ብሎ
አመነ እንጂ አልካደም። ፳፩"እንኪያ አንተ
ማነህ? አንተ ኤልያስ ነህን?" ብለው ጠየቁት፤
"አይደለሁም" አለ፤ "እንኪያ አንተ ነቢዩ
ነህን?" አሉት፤ "አይደለሁም" አለ። ፳፪"እን
ኪያስ አንተ ማነህ? ለላኩንም መልስ እንድን
ሰጥ ስለ ራስህ ማን ትላለህ?" አሉት። ፳፫እር
ሱም፥ "ነቢዩ ኢሳይያስ እንደ ተናገረ የእግዚ
አብሔርን መንገድ ጥረጉ እያለ በምድረ በዳ
የሚሰብክ የዐዋጅ ነጋሪ ድምፅ እኔ ነኝ" አለ።
፳፬የተላኩትም ከፈሪሳውያን ነበሩ። ፳፭"እንኪ
ያስ ክርስቶስን ካልሆንህ፥ ኤልያስንም ካል
ሆንህ፥ ነቢይንም ካልሆንህ ለምን ታጠምቃ
ለህ?" ብለው ጠየቁት። ፳፮ዮሐንስም መልሶ
እንዲህ አላቸው፥ "እኔ በውኃ አጠምቃችኋ
ለሁ፤[፪] ነገር ግን እናንተ የማታውቁት በመካ
ከላችሁ ቆሞአል። ፳፯ከእኔ በኋላ የሚመጣው፥

---

፩ "ከሴት" የሚለው በግሪኩ እኛ በአብዛኛው የግእዝ ዘርዕ የለም።

፪ በግሪኩ "አጠምቃለሁ" ይላል።

፩፥፯ ማቴ. ፫፥፩፤ ማር. ፩፥፬፤ ሉቃ. ፫፥፩-፪። ፩፥፳፩ ዘዳ. ፲፰፥፲፭፤ ፲፰፤ ሚል. ፬፥፭። ፩፥፳፫ ኢሳ. ፵፥፫።

ከእኔ በፊት የነበረው፥ የጫማውን ጠፍር
ልፈታ እንኳ የማይገባኝ ነው።"[፫] ፳፰ዮሐንስ
ያጠምቅበት በነበረው በዮርዳኖስ ማዶ በቢታ
ንያ በቤተ ራባ እንዲህ ሆነ።
፳፱በማግሥቱም ዮሐንስ ወደ እርሱ ሲመጣ
ጌታችን ኢየሱስን አይቶ እንዲህ አለ፤ "እነሆ፥
የዓለሙን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብ
ሔር በግ። ፴ከእኔ በፊት የነበረ ሰው ከእኔ
በኋላ ይመጣል ብዬ ስለ እርሱ የነገርኋችሁ
ይህ ነው፤ እርሱ ከእኔ አስቀድሞ ነበርና።
፴፩እኔ አላውቀውም ነበር፤ ነገር ግን እስራ
ኤል እንዲያውቁት ስለዚህ እኔ በውኃ ላጠ
ምቅ መጣሁ።" ፴፪ዮሐንስም ምስክርነቱን እን
ዲህ ብሎ ተናገረ፥ "መንፈስ ቅዱስ ከሰማይ
እንደ ርግብ ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥ አየሁ።
፴፫እኔም አላውቀውም ነበር፤ ነገር ግን በውኃ
እንዳጠምቅ የላከኝ እርሱ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ
ሲቀመጥበት የምታየው በመንፈስ ቅዱስ የሚያ
ጠምቅ እርሱ ነው አለኝ። ፴፬እኔም ራሴ አይቻ
ለሁ፤ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ
እኔ ምስክሩ ነኝ።"

## ስለ መጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት

፴፭በማግሥቱም ደግሞ ዮሐንስ ከሁለቱ ደቀ
መዛሙርቱ ጋር ቆሞ ሳለ፥ ፴፮ጌታችን ኢየሱስን
ሲሄድ አይቶ "እነሆ፥ የዓለሙን ኀጢአት የሚ
ያስወግድ[፬] የእግዚአብሔር በግ" አለ። ፴፯ሁለቱ
ደቀ መዛሙርቱም እንዲህ ሲል ሰምተው ጌታ
ችን ኢየሱስን ተከተሉት። ፴፰ጌታችን ኢየሱ
ስም ዘወር ብሎ ሲከተሉት አየና፥ "ምን ትሻ
ላችሁ?" አላቸው። ፴፱እነርሱም፥ "ረቢ፥ ትር
ጓሜውም መምህር ሆይ፥ ማለት ነው፤ ወዴት
ትኖራለህ?" አሉት። ፵እርሱም "መጥታችሁ
እዩ" አላቸው፤ ሄደውም የሚኖርበትን አዩ፤
ያን ዕለትም እስከ ዐሥር ሰዓት ድረስ በእርሱ
ዘንድ ዋሉ። ፵፩ከዮሐንስ ዘንድ ሰምተው ጌታ
ችን ኢየሱስን ከተከተሉት ከሁለቱም አንዱ
የስምዖን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ ነበር።
፵፪እርሱም መጀመሪያ ወንድሙ ስምዖንን አግ
ኝቶ "በትርጓሜው ክርስቶስ የሚሉት መሲ
ሕን አገኘነው" አለው። ፵፫እርሱም ወደ ጌታ
ችን ወደ ኢየሱስ ወሰደው፤ ጌታችን ኢየሱስም
ባየው ጊዜ፥ "አንተ የዮና ልጅ ስምዖን ነህን?
አንተ ኪፋ ትባላለህ፤" አለው፤ ትርጓሜውም
ጴጥሮስ ማለት ነው።

## ስለ ፊልጶስና ስለ ናትናኤል

፵፬በማግሥቱም ጌታችን ኢየሱስ ወደ ገሊላ
ሊሄድ ወደደ፤ ፊልጶስንም አገኘውና "ተከተ
ለኝ" አለው። ፵፭ፊልጶስ ግን ከእንድርያስና
ከጴጥሮስ ከተማ ከቤተ ሳይዳ ነበር። ፵፮ፊልጶ
ስም ናትናኤልን አገኘውና፥ "ሙሴ በኦሪት፥
ነቢያትም ስለ እርሱ የጻፉለትን የዮሴፍን ልጅ
የናዝሬቱን ኢየሱስን አገኘነው" አለው። ፵፯ናት
ናኤልም፥ "በውኑ ከናዝሬት ደግ ሰው[፭] ሊወጣ
ይቻላልን?" አለው፤ ፊልጶስም፥ "መጥተህ
እይ" አለው። ፵፰ጌታችን ኢየሱስም ናትናኤ
ልን ወደ እርሱ ሲመጣ ባየው ጊዜ ስለ እርሱ
"እነሆ፥ በልቡ ተንኰል የሌለበት እውነተኛ
እስራኤላዊ ይህ ነው" አለ። ፵፱ናትናኤልም፥
"በየት ታውቀኛለህ?" አለው፤ ጌታችን ኢየ
ሱስም መልሶ፥ "ገና ፊልጶስ ሳይጠራህ በበ
ለስ ዛፍ ሥር ሳለህ አይቼሃለሁ" አለው። ፶ናት
ናኤልም መልሶ፥ "መምህር ሆይ፥ በእውነት
አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፤ የእስራኤልም
ንጉሥ አንተ ነህ" አለው። ፶፩ጌታችን ኢየሱ
ስም መልሶ፥ "በበለስ ዛፍ ሥር አየሁህ ስለ
አልሁህ አመንህን? ከዚህ የሚበልጥ ታያለህ"
አለው። ፶፪"እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ ከእ
ንግዲህ ወዲህ ሰማያት ሲከፈቱ፥ የእግዚአብ
ሔርም መላእክት ወደ ሰው ልጅ ሲወርዱና
ሲወጡ ታያላችሁ" አላቸው።

## ምዕራፍ ፪

## በቃና ዘገሊላ ስለ ተደረገው ሰርግ

፩በሦስተኛውም ቀን የገሊላ ክፍል በምትሆን
በቃና ሰርግ ሆነ፤ የጌታችን የኢየሱስ እናትም
በዚያ ነበረች። ፪ጌታችን ኢየሱስና ደቀ መዛሙ
ርቱም ወደ ሰርጉ ታደሙ።

## ስለ እናቱ ምልጃ

፫የወይን ጠጃቸውም ባለቀ ጊዜ እናቱ ጌታ
ችን ኢየሱስን፥ "የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም"

---

፫ "እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል" የሚል በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ ይገኛል።

፬ "የዓለሙን ኀጢአት የሚያሰወግድ ..." የሚለው በግሪኩ የለም።

፭ በግሪኩ "መልካም ነገር" ይላል።

፮፥፶፩ ዘፍ. ፳፰፥፲፪።

አለችው። ፬ጌታችን ኢየሱስም፥ “አንቺ ሆይ
ካንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዬ ገና አልደረ
ሰም” አላት። ፭እናቱም ለአሳላፊዎቹ፥ “የሚ
ላችሁን ሁሉ አድርጉ” አለቻቸው።

## ስለ መጀመሪያው ተአምር

፮በዚያም እንደ አይሁድ ልማድ የሚያነጹባ
ቸው ስድስት የድንጋይ ጋኖች ነበሩ፤ ከእነር
ሱም እያንዳንዱ ሁለት ወይም ሦስት እንስራ
ይይዙ ነበር። ፯ጌታችን ኢየሱስም፥ “ጋኖቹን
ውኃ ሙሉአቸው” አላቸው፤ እስከ አፋቸውም
እስከ ላይ ሞሉአቸው። ፰“አሁንም ቅዱና ወስ
ዳችሁ ለአሳዳሪው ስጡት” አላቸው፤ ወስደ
ውም ሰጡት። ፱አሳዳሪውም ያን የወይን ጠጅ
የሆነውን ውኃ ቀምሶ አደነቀ፤[፩] ከወዴት እንደ
መጣም አላወቀም፤ የቀዱት አሳላፊዎች ግን
የወይን ጠጅ የሆነውን ያን ውኃ ያውቁ ነበር።
ውኃዉን የሞሉ እነርሱ ነበሩና። ፲አሳዳሪውም
ሙሽራውን ጠርቶ፥ “ሰው ሁሉ መልካሙን
የወይን ጠጅ አስቀድሞ ያጠጣል፤ ከጠገቡ በኋ
ላም ተርታውን ያመጣል፤ አንተ ግን መልካ
ሙን የወይን ጠጅ እስካሁን አቈየህ” አለው።
፲፩ጌታችን ኢየሱስም በቃና ዘገሊላ ያደረገው
የተአምራት መጀመሪያ ይህ ነው፤ ክብሩንም
ገለጠ፤ ደቀ መዛሙርቱም አመኑበት።

## ወደ ኢየሩሳሌም ስለ መውጣቱ

(ማቴ. ፳፩፥፲፪፡፲፫፤ ማር. ፲፩፥፲፭-፲፯)

፲፪ከዚህም በኋላ እርሱና እናቱ፥ ወንድሞቹና
ደቀ መዛሙርቱም ወደ ቅፍርናሆም ወረዱ፤
በዚያም ብዙ ያይደለ ጥቂት ቀን ተቀመጡ።
፲፫የአይሁድም የፋሲካቸው በዓል ቀርቦ ነበር፤
ጌታችን ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ።
፲፬በቤተ መቅደስም በሬዎችንና በጎችን፥ ርግቦ
ችንም የሚሸጡትን፥ ገንዘብ ለዋጮችንም ተቀ
ምጠው አገኘ። ፲፭የገመድም ጅራፍ አበጀ፤ በጎ
ችንና በሬዎችን፥ ሁሉንም ከቤተ መቅደስ አስ
ወጣ፤ የለዋጮችንም ገንዘብ በተነ፤ ገበታዎቻቸ
ውንም ገለበጠ። ፲፮ርግብ ሻጮችንም፥ “ይህን
ከዚህ አውጡ፤ የአባቴን ቤት የንግድ ቤት
አታድርጉ” አላቸው። ፲፯ደቀ መዛሙርቱም፥
“የቤትህ ቅናት በላኝ” የሚል ቃል ተጽፎ እን
ዳለ ዐሰቡ።

## ስለ መሞቱና ስለ መነሣቱ

፲፰አይሁድም መልሰው፥ “ይህን የምታደርግ
ምን ምልክት ታሳያለህ?” አሉት። ፲፱ጌታችን
ኢየሱስም፥ “ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፤
በሦስተኛውም ቀን አነሣዋለሁ” ብሎ መለሰላ
ቸው። ፳አይሁድም፥ “ይህ ቤተ መቅደስ በአ
ርባ ስድስት ዓመት ተሠራ፤ አንተስ በሦስት
ቀኖች ውስጥ ታነሣዋለህን?” አሉት። ፳፩እርሱ
ግን ይህን የተናገረው ቤተ መቅደስ ስለ ተባለ
ሰውነቱ ነበር። ፳፪ከሙታን በተነሣ ጊዜም ደቀ
መዛሙርቱ ስለዚህ እንደ ነገራቸው ዐሰቡ፤
በመጻሕፍት ቃልና ጌታችን ኢየሱስ በነገራቸ
ውም ነገር አመኑ።

## በበዓሉ ውስጥ ብዙዎቹ ስለ ማመናቸው

፳፫ጌታችን ኢየሱስም በፋሲካ በዓል በኢየሩ
ሳሌም ሳለ ብዙ ሰዎች ያደረገውን ተአምራት
ባዩ ጊዜ በስሙ አመኑ። ፳፬እርሱ ጌታችን ኢየ
ሱስ ግን አያምናቸውም ነበር፤ ሁሉን እያንዳ
ንዱን ያውቀዋልና። ፳፭የሰውንም ግብሩን ሊነ
ግሩት አይሻም፤ እርሱ በሰው ያለውን ያውቅ
ነበርና።

# ምዕራፍ ፫

## ፈሪሳዊው ኒቆዲሞስ ወደ ኢየሱስ ስለ መምጣቱ

፩ከፈሪሳውያን ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ
ኒቆዲሞስ የተባለ አንድ ሰው ነበረ። ፪እርሱም
በሌሊት ወደ ጌታችን ኢየሱስ መጥቶ እንዲህ
አለው፥ “መምህር ሆይ፥ ልታስተምር ከእግዚ
አብሔር ዘንድ እንደ መጣህ እናውቃለን፤ እግዚ
አብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታ
ደርገውን ይህን ተአምር ሊያደርግ የሚችል የለ
ምና።” ፫ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፥ “እውነት
እውነት እልሃለሁ፤ ዳግመኛ ያልተወለደ ሰው
የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማየት አይች
ልም” አለው። ፬ኒቆዲሞስም፥ “ሰው ከሽመገለ
በኋላ ዳግመኛ መወለድ እንደምን ይችላል? ዳግ
መኛ ይወለድ ዘንድ ወደ እናቱ ማኅፀን ተመልሶ
መግባት ይችላልን?” አለው። ፭ጌታችን ኢየሱ
ስም መልሶ እንዲህ አለው፥ “እውነት እውነት

---

፩ “አደነቀ” የሚለው በግሪኩ የለም።

፪፡፲፪ ማቴ. ፬፥፲፫። ፪፥፲፫ ዘፀ. ፲፪፥፩-፳፯። ፪፥፲፯ መዝ. ፷፰፥፱።

፪፡፲፱ ማቴ. ፳፮፥፷፩፤ ፳፯፥፵፤ ማር. ፲፬፥፶፰፤ ፲፭፥፳፱።

እልሀለሁ፤ ዳግመኛ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ
ያልተወለደ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግ
ሥት ሊገባ አይችልም። ፮ከሥጋ የተወለደ ሥጋ
ነውና፤ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነውና።
፯ስለዚህም ዳግመኛ ልትወለዱ ይገባችኋል ስለ
አልሁህ አታድንቅ። ፰ነፋስ ወደ ወደደው ይነፍ
ሳልና፤ ድምፁንም ትሰማለህ፤ ነገር ግን ከየት
እንደሚመጣ ወዴትም እንደሚሄድ አታውቅም፤
ከመንፈስ የሚወለድ ሁሉ እንዲሁ ነው።” ፱ኒቆ
ዲሞስም መልሶ፥ “ይህ ሊሆን እንዴት ይቻ
ላል?” አለው። ፲ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፥
“አንተ የእስራኤል መምህራቸው ነህ፤ ነገር ግን
እንዴት ይህን አታውቅም?” አለው። ፲፩እውነት
እውነት እልሃለሁ፤ የምናውቀውን እንናገራለን፤
ያየነውንም እንመሰክራለን፤ ነገር ግን ምስክርነ
ታችንን አትቀበሉንም። ፲፪በምድር ያለውን ስነ
ግራችሁ ካላመናችሁኝ[፩] በሰማይ ያለውን ብነግ
ራችሁ እንዴት ታምኑኛላችሁ? ፲፫ከሰማይ ከወረ
ደው የሰው ልጅ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ የለም፤
እርሱም በሰማይ የሚኖረው ነው። ፲፬ሙሴ በም
ድረ በዳ እባቡን እንደ ሰቀለው የሰው ልጅ እን
ዲሁ ይሰቀል ዘንድ አለው። ፲፭ያመነበት ሁሉ
ለዘለዓለም ሕያው ሆኖ እንዲኖር እንጂ እንዳ
ይጠፋ። ፲፮በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም
ሕይወትን እንዲያገኝ እንጂ እንዳይጠፋ እግዚ
አብሔር አንድያ ልጁን ቤዛ አድርጎ እስኪሰጥ
ድረስ ዓለሙን እንዲህ ወዶታልና። ፲፯ዓለም በእ
ርሱ ይድን ዘንድ ነው እንጂ በዓለም እንዲፈ
ርድ እግዚአብሔር ልጁን ወደዚህ ዓለም አል
ላከውምና። ፲፰በእርሱ ያመነ አይፈረድበትም፤
በእርሱ ያላመነ ግን ፈጽሞ ተፈርዶበታል፤ በአ
ንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም አላመነምና።
፲፱ፍርዱም ይህ ነው፤ ብርሃን ወደ ዓለም መጥ
ቶአልና፤ ሰውም ሥራው ክፉ ስለሆነ ከብር
ሃን ይልቅ ጨለማን መርጦአልና። ፳ሥራው
ክፉ የሆነ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና፤ ክፉም ስለ
ሆነ[፪] ሥራው እንዳይገለጥበት ወደ ብርሃን አይ
መጣም። ፳፩እውነትን የሚሠራ ግን ሥራው ይገ
ለጥ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል፤ ስለ እግዚአ
ብሔር ብሎ ይሠራልና።

## ጌታችን ወደ ይሁዳ ምድር ስለ መሄዱ

፳፪ከዚህም በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ከደቀ መዛ
ሙርቱ ጋር ወደ ይሁዳ ምድር ሄደ፤ በዚያም
እያጠመቀ አብሮአቸው ተቀመጠ። ፳፫ዮሐንስም
በዮርዳኖስ ማዶ[፫] በሳሌም አቅራቢያ በሄኖን ያጠ
ምቅ ነበር፤ በዚያ ብዙ ውኃ ነበርና፤ ብዙ ሰዎ
ችም ወደ እርሱ እየመጡ ያጠምቃቸው ነበር።
፳፬ዮሐንስ ገና ወደ ወኅኒ ቤት አልገባም ነበርና።

## ስለ ማንጻት የተደረገ ክርክር

፳፭ከዚህም በኋላ በዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና
በአይሁድ መካከል ስለ ማንጻት ክርክር ሆነ፤
፳፮ወደ ዮሐንስም ሄደው፥ “መምህር ሆይ፥ በዮ
ርዳኖስ ማዶ ካንተ ጋር የነበረው፥ አንተም የመ
ሰከርህለት እርሱ እነሆ፥ ያጠምቃል፤ ሁሉም
ወደ እርሱ ይሄዳል” አሉት። ፳፯ዮሐንስም
መልሶ እንዲህ አለ፥ “ሰው ከሰማይ ካልተሰ
ጠው በስተቀር እርሱ ራሱ ጸጋን ገንዘብ ሊያ
ደርግ ምንም አይችልም። ፳፰እኔ ክርስቶስ አይ
ደለሁም፤ ነገር ግን እንድሰብክለት[፬] ከእርሱ
በፊት ተልኬአለሁ እንዳልኋችሁ እናንተ ራሳ
ችሁ ምስክሮች ናችሁ። ፳፱ሙሽራ ያለችው
ሙሽራ ነው፤ ቆሞ የሚሰማው የሙሽራው
ሚዜ ግን በሙሽራው ቃል እጅግ ደስ ይለ
ዋል፤ የእኔ ደስታ አሁን ተፈጸመች። ፴የእርሱ
ትበዛለች፤ የእኔ ግን ታንስ ዘንድ ይገባል።”
፴፩ከላይ የመጣው ከሁሉ በላይ ነው፤ ከም
ድር የተገኘውም ምድራዊ ነው፤ የምድሩንም
ይናገራል፤ ከሰማይ የመጣው ግን ከሁሉ በላይ
ነው። ፴፪ባየውና በሰማው ይመሰክራል፤ ነገር
ግን ምስክርነቱን የሚቀበለው የለም። ፴፫ምስክ
ርነቱን የተቀበለ ግን እግዚአብሔር እውነተኛ
እንደ ሆነ አተመ። ፴፬እግዚአብሔር የላከው የእ
ግዚአብሔርን ቃል ይናገራል፤ እግዚአብሔር
መንፈሱን ሰፍሮ አይሰጥምና። ፴፭አብ ልጁን
ይወዳልና፥ ሁሉን በእጁ ሰጠው። ፴፮በወልድ
የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ በወልድ
የማያምን ግን የእግዚአብሔር የቍጣ መቅሠ
ፍት በላዩ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም።

---

፩ በግሪኩ “... ካላመናችሁ ... እንዴት ታምናላችሁ” ይላል።

፪ በግሪኩ “ክፉም ስለሆነ ...” አይልም።

፫ “በዮርዳኖስ ማዶ” የሚለው በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ የለም።

፬ “እንድሰብክለት” የሚለው በግሪኩ የለም።

፫፥፲፬ ዘኁ. ፳፩፥፱።   ፫፥፳፬ ማቴ. ፲፬፥፫፤ ማር.፮፥፲፯፤ ሉቃ. ፫፥፲፱-፳።   ፫፥፳፰ ዮሐ. ፩፥፳።
፫፥፴፭ ማቴ. ፲፩፥፳፯፤ ሉቃ. ፲፥፳፪።

## ምዕራፍ ፬

### ወደ ገሊላ ስለ መሄዱ

፩ጌታችን ኢየሱስ ከዮሐንስ ይልቅ ደቀ መዛ
ሙርትን እንደ አበዛና እንደሚያጠምቅ ፈሪሳ
ውያን መስማታቸውን ዐወቀ። ፪ነገር ግን ደቀ
መዛሙርቱ እንጂ እርሱ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ
አላጠመቀም። ፫የይሁዳንም ምድር ትቶ ዳግ
መኛ ወደ ገሊላ ሄደ። ፬በሰማርያ በኩልም ሲያ
ልፍ ሳለ፥ ፭ያዕቆብ ለልጁ ለዮሴፍ በሰጠው
በወይን ቦታ አቅራቢያ ወደ አለችው ሲካር ወደ
ምትባለው የሰማርያ ከተማ ደረሰ። ፮በዚያም
የያዕቆብ የውኃ ጕድጓድ ነበረ። ጌታችን ኢየሱ
ስም መንገድ በመሄድ ደክሞ በዚያ ጕድጓድ
አጠገብ ተቀመጠ፤ ጊዜውም ስድስት ሰዓት
ያህል ነበር።

### ስለ ሳምራዊት ሴት

፯እነሆ፥ ከሰማርያ አንዲት ሴት ውኃ ልት
ቀዳ መጣች፤ ጌታችን ኢየሱስም፥ "ውኃ
አጠጪኝ" አላት። ፰ደቀ መዛሙርቱ ምግብ
ሊገዙ ወደ ከተማ ሄደው ነበርና። ፱ያቺ የሰ
ማርያ ሴትም፥ "አንተ አይሁዳዊ ስትሆን፥
እኔም ሳምራዊት ስሆን እንዴት ከእኔ ዘንድ
ውኃ ልትጠጣ ትለምናለህ?" አለችው፤ አይ
ሁድ ከሳምራውያን ጋር በሥርዐት፩ አይተባበ
ሩም ነበርና። ፲ጌታችን ኢየሱስም፥ "የእግዚአ
ብሔርን ስጦታና ውኃ አጠጪኝ፪ ብሎ የሚለ
ምንሽ ማን እንደ ሆነ ብታውቂስ አንቺ ደግሞ
በለመንሺው ነበር፤ እርሱም የሕይወትን ውኃ
በሰጠሽ ነበር" ብሎ መለሰላት። ፲፩ያቺ ሴትም
እንዲህ አለችው፥ "ጌታዬ መቅጃ እንኳ የለ
ህም፤ ጕድጓዱም ጥልቅ ነው፤ እንግዲህ የሕይ
ወት ውኃ ከወዴት ታገኛለህ? ፲፪ይህን ጕድጓድ
ከሰጠን ከአባታችን ከያዕቆብ አንተ ትበልጣለ
ህን? እርሱም፫ ልጆቹም፥ ከብቶቹም ከእርሱ
ጠጥተዋል።" ፲፫ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እን
ዲህ አላት፥ "ከዚህ ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ዳግ
መኛ ይጠማል። ፲፬እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚ
ጠጣ ግን ለዘለዓለም አይጠማም፤ እኔ የምሰ
ጠው ውኃ በውስጡ ለዘለዓለም ሕይወት የሚ
ፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆንለታል እንጂ።"
፲፭ሴቲቱም፥ "ጌታዬ ሆይ፥ እንዳልጠማ፥ ዳግ
መኛም ውኃ ልቀዳ ወደዚህ እንዳልመጣ እባ
ክህ ከዚህ ውኃ ስጠኝ፤" አለችው።

፲፮ጌታችን ኢየሱስም፥ "ሂደሽ ባልሽን ጥሪና
ወደዚህ ነይ" አላት። ፲፯ሴቲቱም፥ "ባል የለ
ኝም" ብላ መለሰችለት፤ ጌታችን ኢየሱስም
እንዲህ አላት፥ "ባል የለኝም በማለትሽ መል
ካም ተናገርሽ። ፲፰ቀድሞ አምስት ባሎች ነበ
ሩሽ፤ ዛሬ አብሮሽ ያለው ግን ባልሽ አይደ
ለም፤ ይህንስ እውነት አልሽ።" ፲፱ሴቲቱም
እንዲህ አለችው፥ "ጌታዬ፥ አንተ ነቢይ እንደ
ሆንህ አያለሁ። ፳አባቶቻችን በዚህ ተራራ
ሰገዱ፤ እናንተ ግን ይሰግዱበት ዘንድ የሚ
ገባው ስፍራ በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ።"
፳፩ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ አላት፥ "አንቺ
ሴት በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም ብቻ
ለአብ የማይሰግዱበት ሰዓት እንደምትመጣ እመ
ኝኝ። ፳፪እናንተ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ፤
እኛ ግን ለምናውቀው እንሰግዳለን፤ መድኀኒት
ከአይሁድ ወገን ነውና። ፳፫ነገር ግን በእውነት
የሚሰግዱ በመንፈስና በእውነት ለአብ የሚሰግ
ዱባት ጊዜ ትመጣለች፤ እርስዋም አሁን ናት።
አብ እንዲህ የሚሰግዱለትን ይሻልና። ፳፬እግዚአ
ብሔር መንፈስ ነውና፤ የሚሰግዱለትም በመ
ንፈስና በእውነት ይሰግዱለት ዘንድ ይገባል።"
፳፭ሴቲቱም፥ "ክርስቶስ የሚሉት መሲሕ እን
ደሚመጣ እናውቃለን፤ እርሱም በሚመጣ ጊዜ
ሁሉን ይነግረናል" አለችው። ፳፮ጌታችን ኢየሱ
ስም፥ "የማነጋግርሽ እኔ እርሱ ነኝ" አላት።

፳፯በዚያም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ መጡ፤
ከሴት ጋርም ይነጋገር ነበርና ተደነቁ፤ ነገር
ግን፥ "ምን ትሻለህ? ወይስ ከእርስዋ ጋር
ለምን ትነጋገራለህ?" ያለው የለም። ፳፰ሴቲ
ቱም እንስራዋን ትታ ወደ ከተማ ገባች፤ ለሰ
ዎችም ነገረች። ፳፱"የሠራሁትን ሁሉ የነገረ
ኝን ሰው ታዩ ዘንድ ኑ፤ እንጃ፥ እርሱ ክርስ
ቶስ ይሆን?" ፴ከከተማም ወጥተው ወደ እርሱ
ሄዱ።

፴፩በዚህም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ፥ "መምህር
ሆይ፥ እህል ብላ" ብለው ለመኑት። ፴፪ጌታችን
ኢየሱስም፥ "እኔ የምበላው እናንተ የማታው

---

፩ "በሥርዐት" የሚለው በግሪኩ የለም።

፪ በግሪኩ "ውኃ ስጪኝ" ይላል።

፫ አንዳንድ የግእዝ ዘርዕ "ሚስቶቹም" የሚል ይጨምራል።

፬፡፭ ዘፍ. ፴፫፡፲፱፤ ኢያሱ. ፳፬፡፴፪። ፬፡፱ ዕዝ. ፬፡፩-፭፤ ነህ. ፬፡፲፪።

ቁት ምግብ አለኝ" አላቸው። ፴፫ደቀ መዛሙ
ርቱም እርስ በርሳቸው፥ "አንዳች የሚበላው
ምግብ ያመጣለት ሰው ይኖር ይሆን?"[፩] ተባ
ባሉ። ፴፬ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፥
"የእኔስ መብል የላከኝን የአባቴን ፈቃድ አደ
ርግ ዘንድ፥ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው።
፴፭እናንተ እስከ አራት ወር ድረስ መከር ይሆ
ናል የምትሉ አይደለምን? እነሆ፥ እላችኋለሁ፤
ዐይናችሁን አንሡ፤ መከሩም ሊደርስ እንደ
ገረጣ ምድሩን ተመልከቱ። ፴፮አጫጅም ዋጋ
ውን ያገኛል፤ የሚዘራና የሚያጭድም በአንድ
ነት ደስ እንዲላቸው ለዘለዓለም ሕይወት ፍሬን
ይሰበስባል። ፴፯አንዱ ይዘራል፥ ሌላውም ያጭ
ዳል የሚለው ቃል በዚህ እውነት ሆኖአል።
፴፰እኔም ያልደከማችሁበትን እንድታጭዱ ላክ
ኋችሁ፤ ሌሎች ደከሙ፤ እናንተም በድካማ
ቸው ገባችሁ።"

## ስለ ሳምራውያን

፴፱"የሠራሁትን ሁሉ ነገረኝ" ብላ የመሰከ
ረችው ሴት ስለ ነገረቻቸውም ከዚያች ከሰማ
ርያ ከተማ ብዙዎች አመኑበት። ፵ሳምራውያ
ንም ሁሉ ወደ እርሱ መጥተው በእነርሱ ዘንድ
እንዲኖር ማለዱት፤ ሁለት ቀንም ያህል በዚያ
ተቀመጠ። ፵፩ስለ ቃሉም እጅግ ብዙዎች አመ
ኑበት። ፵፪ሴቲቱንም፥ "እኛ ራሳችን ይህ በእ
ውነት የዓለም መድኀኒት ክርስቶስ እንደ ሆነ
ሰምተንና ተረድተን ነው እንጂ በአንቺ ቃል
ያመንበት አይደለም" አሏት።

## ገሊላውያን እንደ ተቀበሉት።

፵፫ከሁለት ቀንም በኋላ ጌታችን ኢየሱስ
ከዚያ ወጥቶ ወደ ገሊላ ሄደ። ፵፬ነቢይ በገዛ
ሀገሩ እንደማይከብር እርሱ ራሱ ጌታችን ኢየ
ሱስ መሰከረ። ፵፭ወደ ገሊላም ደግሞ በገባ ጊዜ
ገሊላውያን ሁሉ ተቀበሉት፤ እነርሱ ለበዓል
ሄደው ስለ ነበር በበዓሉ ቀን በኢየሩሳሌም ያደ
ረገውን ተአምር አይተው ነበርና።
፵፮ጌታችን ኢየሱስም ውኃውን የወይን ጠጅ
ወደ አደረገበት የገሊላ ክፍል ወደምትሆን ወደ
ቃና ዳግመኛ ሄደ። በቅፍርናሆም ልጁ የታመ
መበት የንጉሥ ወገን የሆነ አንድ ሰው ነበረ፤
፵፯እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ
እንደ መጣ በሰማ ጊዜ ወደ እርሱ ሄደ፤ ሊሞት
ቀርቦ ነበርና ወርዶ ልጁን ያድንለት ዘንድ
ለመነው፤ ፵፰ጌታችን ኢየሱስም፥ "ምልክትንና
ድንቅ ሥራን ካላያችሁ አታምኑም" አለው።
፵፱ያም የንጉሥ ወገን የሆነ ሰው፥ "አቤቱ፥
ልጄ ሳይሞት ፈጥነህ ውረድ" አለው። ፶ጌታ
ችን ኢየሱስም፥ "ሂድ፤ ልጅህስ ድኖአል"
አለው፤ ያም ሰው፡- ጌታችን ኢየሱስ በነገረው
ቃል አምኖ ሄደ። ፶፩ሲወርድም አገልጋዮቹ ተቀ
በሉትና፥ "ልጅህስ ድኖአል" ብለው ነገሩት።
፶፪የዳነባትን ሰዓቷንም ጠየቃቸው፤ "ትናንትና
በሰባት ሰዓት ንዳዱ ተወው" አሉት። ፶፫አባ
ቱም፥ ጌታችን ኢየሱስ፥ "ልጅህ ድኖአል"
ባለበት ሰዓት እንደ ሆነች ዐወቀ፤ እርሱም፥
ቤተ ሰቦቹም ሁሉ አመኑ። ፶፬ዳግመኛም ጌታ
ችን ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ መጥቶ ያደረ
ገው ሁለተኛው ተአምር ይህ ነው።

## ምዕራፍ ፭

## ጌታችን መፃጕዕን እንደ ፈወሰው

፩ከዚህም በኋላ በአይሁድ በዓል እንዲህ
ሆነ፤ ጌታችን ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ።
፪በኢየሩሳሌምም በበጎች በር አጠገብ መጠ
መቂያ ነበረች፤ ስምዋንም በዕብራይስጥ ቤተ
ሳይዳ ይሉአታል፤ አምስት እርከኖችም ነበሩ
አት። ፫በዚያም ዕውሮችና አንካሶች፥ ሰውነታ
ቸውም የሰለለ ብዙ ድውያን ተኝተው የው
ኃዉን መናወጥ ይጠባበቁ ነበር። ፬የእግዚአብ
ሔር መልአክ ወደ መጠመቂያዉ ወርዶ ውኃ
ዉን በሚያናውጠው ጊዜ፥ ከውኃዉ መናወጥ
በኋላ በመጀመሪያ ወርዶ የሚጠመቅ ካለበት
ደዌ ሁሉ ይፈወስ ነበርና። ፭በዚያም ከታ
መመ ሠላሳ ስምንት ዓመት የሆነው አንድ
ሰው ነበር። ፮ጌታችን ኢየሱስም ያን ሰው
በአልጋዉ ተኝቶ ባየ ጊዜ በደዌ ብዙ ዘመን
እንደ ቈየ ዐውቆ፥ "ልትድን ትወዳለህን?"
አለው። ፯ድውዩም መልሶ፥ "አዎን ጌታዬ
ሆይ፥ ነገር ግን ውኃዉ በተናወጠ ጊዜ ወደ
መጠመቂያዉ የሚያወርደኝ ሰው የለኝም፤ እኔ
በምመጣበት ጊዜ ሌላው ቀድሞኝ ይወርዳል"
አለው። ፰ጌታችን ኢየሱስም፥ "ተነሥና አል
ጋህን ተሸክመህ ሂድ" አለው። ፱ወዲያውኑም
ያ ሰው ድኖ አልጋውን ተሸክሞ ሄደ፤ ያች
ቀንም ሰንበት ነበረች።

፩ አንዳንድ የግእዝ ዘርዕ "… ወሚመ ዛቲ ብእሲት" የሚል ይጨምራል።
፬፥፵፬ ማቴ. ፲፫፥፶፯፤ ማር. ፮፥፬፤ ሉቃ. ፬፥፳፬። ፬፥፵፭ ዮሐ. ፪፥፳፫። ፬፥፵፮ ዮሐ. ፪፥፩-፲፩።

፲አይሁድም የዳነውን ሰው፥ “ዛሬ ሰን
በት ነው፤ አልጋህን ልትሸከም አይገባህም”
አሉት። ፲፩እርሱም መልሶ፥ “ያዳነኝ እርሱ፦
አልጋህን ተሸክመህ ሂድ አለኝ” አላቸው።
፲፪አይሁድም፥ “አልጋህን ተሸክመህ ሂድ ያለህ
ሰውዬው ማነው?” ብለው ጠየቁት። ፲፫ያ የተ
ፈወሰው ግን ያዳነው ማን እንደ ሆነ አላወ
ቀም፤ ጌታችን ኢየሱስ በዚያ ቦታ በነበሩት
ብዙ ሰዎች መካከል ተሰውሮ ነበርና። ፲፬ከዚ
ህም በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ያን የዳነውን ሰው
በቤተ መቅደስ አገኘውና፥ “እነሆ፥ ድነሃል፤
ግን ከዚህ የባሰ እንዳያገኝህ ዳግመኛ እንዳትበ
ድል ተጠንቀቅ” አለው። ፲፭ያም ሰው ሄዶ ያዳ
ነው ጌታችን ኢየሱስ እንደ ሆነ ለአይሁድ ነገ
ራቸው። ፲፮ስለዚህም አይሁድ ጌታችን ኢየሱ
ስን ያሳድዱትና ሊገድሉትም ይሹ ነበር፤ በሰ
ንበት እንዲህ ያደርግ ነበርና። ፲፯ጌታችን ኢየ
ሱስም መልሶ፥ “አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል፤
እኔም እሠራለሁ” አላቸው። ፲፰ስለዚህም አይ
ሁድ ሊገድሉት በጣም ይፈልጉ ነበር፤ “ሰንበ
ትን የሚሽር ነው” በማለት ብቻ አይደለም፤
ደግሞም እግዚአብሔርን “አባቴ ነው ይላል፤
ራሱንም ከእግዚአብሔር ጋር ያስተካክላል”
በማለት ነው እንጂ።

፲፱ከዚህም በኋላ ጌታችን ኢየሱስ መልሶ እን
ዲህ አላቸው፥ “እውነት እውነት እላችኋለሁ፤
ወልድ ከራሱ ብቻ ምንም ሊያደርግ አይች
ልም፤ አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ፤ ወል
ድም አብ የሚሠራውን ያንኑ እንዲሁ ይሠ
ራል። ፳አብ ልጁን ይወዳልና የሚሠራውንም
ሥራ ሁሉ ያሳየዋል፤ እናንተም ታደንቁ ዘንድ
ከዚህ የሚበልጥ ሥራን ያሳየዋል። ፳፩አብ ሙታ
ንን እንደሚያስነሣቸው፥ ሕይወትንም እንደሚ
ሰጣቸው እንዲሁ ወልድም ለሚወድዳቸው ሕይ
ወትን ይሰጣል። ፳፪አብ ከቶ በማንም አይፈር
ድም፤ ፍርዱን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ።
፳፫ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩ ወልድን
ያከብሩ ዘንድ፤ ወልድን የማያከብር ግን የላከ
ውን አብን አያከብርም። ፳፬እውነት እውነት እላ
ችኋለሁ፤ ቃሌን የሚሰማ በላከኝም የሚያምን
የዘለዓለም ሕይወትን ያገኛል፤ ከሞትም ወደ
ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይሄድም።
፳፭“እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ ሙታን
የእግዚአብሔርን ልጅ ቃል የሚሰሙበት ሰዓት
ይመጣል፤ እርሱም አሁን ነው፤ የሚሰሙትም
ይድናሉ። ፳፮ለአብ በራሱ ሕይወት እንዳለው፥
እንዲሁም ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት
እንዲኖረው ሰጠው። ፳፯የእግዚአብሔር ልጅ
የሰው ልጅ ነውና ይፈርድ ዘንድ ሥልጣንን
ሰጠው።

## ስለ ትንሣኤ ሙታን

፳፰“በመቃብር ያሉ ሁሉ ቃሉን የሚሰሙባት
ጊዜ ትመጣለችና ስለዚህ አታድንቁ። ፳፱መል
ካም የሠሩ ለሕይወት ትንሣኤ፥ ክፉ የሠሩም
ለፍርድ ትንሣኤ ይነሣሉ። ፴እኔ ከራሴ አንዳች
አደርግ ዘንድ አልችልም፤ እንደ ሰማሁ እፈር
ዳለሁ እንጂ፤ ፍርዴም እውነት ነው፤ የላከኝን
ፈቃድ እንጂ የእኔን ፈቃድ አልሻምና።

## ስለ ምስክርነት

፴፩“እኔ ለራሴ ብመሰክር ምስክርነቴ እው
ነት አይደለም። ፴፪ነገር ግን ለእኔ የሚመሰክር
ሌላ ነው፤ ስለ እኔ የሚመሰክረው ምስክርነቱም
እውነት እንደሆነ አውቃለሁ። ፴፫እናንተ ወደ
ዮሐንስ ልካችሁ አልነበረምን? እርሱም ምስክ
ርነቱን በእውነት ነገራችሁ። ፴፬እኔ ግን የሰውን
ምስክርነት የምሻ አይደለሁም፤ ነገር ግን እና
ንተ ትድኑ ዘንድ ይህን እላለሁ። ፴፭እርሱ የሚ
ነድና የሚያበራ መብራት ነበረ፤ እናንተም አን
ዲት ሰዓት በብርሃኑ ደስ ሊላችሁ ወደዳችሁ።
፴፮እኔ ግን ከዮሐንስ ምስክርነት የሚበልጥ ምስ
ክር አለኝ፤ ልሠራውና ልፈጽመው አባቴ የሰ
ጠኝ ሥራ፥ አብ እንደ ላከኝ ያ የምሠራው
ሥራ ምስክሬ ነውና። ፴፯የላከኝ አብም ስለ እኔ
መስክሮአል፤ ከሆነም ጀምሮ ቃሉን አልሰማች
ሁም፤ መልኩንም አላያችሁም። ፴፰ቃሉም የላ
ችሁም፤ በእናንተ ዘንድም አይኖርም፤ እርሱ
የላከውን አላመናችሁምና። ፴፱መጻሕፍትን መር
ምሩ፤ በእነርሱ የዘለዓለም ሕይወትን የምታ
ገኙ ይመስላችኋልና፤ እነርሱም የእኔ ምስክ
ሮች ናቸው። ፵ሕይወትን ታገኙ ዘንድ ወደ
እኔ ልትመጡ አትወዱም። ፵፩እኔ ከሰው ክብ
ርን ልቀበል አልሻም። ፵፪ነገር ግን የእግዚአብ
ሔር ፍቅር በእናንተ እንደሌለባችሁ ዐወቅሁ።
፵፫እኔ በአባቴ ስም መጣሁ፥ አልተቀበላችሁኝ
ምም፤ ሌላው ግን በራሱ ስም ቢመጣ እርሱን
ትቀበሉታላችሁ። ፵፬ከባልንጀራችሁ ክብርን

---

፭፡፲ ነሀ. ፲፫፡፲፱፤ ኤር. ፲፯፡፳፩። ፭፡፳፱ ዳን. ፲፪፡፪። ፭፡፴፫ ዮሐ. ፩፡፲፱-፳፯፤ ፫፡፳፯-፴።
፭፡፴፯ ማቴ. ፫፡፲፯፤ ማር. ፩፡፲፩፤ ሉቃ. ፫፡፳፪።

የምትመርጡ፥ ከአንድ እግዚአብሔርም ክብ
ርን የማትሹ እናንተ እንዴት ልታምኑ ትችላ
ላችሁ? ፵፭እኔ በአብ ዘንድ የምከስሳችሁ አይ
ምሰላችሁ፤ የሚከስሳችሁስ አለ፤ እርሱም እና
ንተ ተስፋ የምታደርጉት ሙሴ ነው። ፵፮ሙሴ
ንስ አምናችሁት ቢሆን እኔንም ባመናችሁኝ
ነበር፤ እርሱ ስለ እኔ ጽፎአልና። ፵፯ሙሴ የጻ
ፈውን ካላመናችሁ ግን የእኔን ቃል እንዴት
ታምናላችሁ?”

## ምዕራፍ ፮

### ወደ ጥብርያዶስ ስለ መሄዱ

(ማቴ. ፲፬፥፲፫-፳፩፤ ማር. ፮፥፴-፵፬)

፩ከዚህ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ወደ ገሊላ
ባሕር ማዶ ወደ ጥብርያዶስ ሄደ። ፪በበሽተ
ኞችም ላይ ያደረገውን ተአምራት ስለ አዩ
ብዙ ሰዎች ተከተሉት፤ ፫ጌታችን ኢየሱስም
ወደ ተራራ ወጣ፤ ከደቀ መዛሙርቱም ጋር
በዚያ ተቀመጠ። ፬የአይሁድ የፋሲካ በዓልም
ቀርቦ ነበር።

### አምስቱን እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ስለ ማበርከቱ

፭ጌታችን ኢየሱስም ዐይኖቹን አንሥቶ ብዙ
ሰዎች ወደ እርሱ ሲመጡ አየና ፊልጶስን፥
“ለእነዚህ ሰዎች የምናበላቸው እንጀራ ከወ
ዴት እንግዛ?” አለው። ፮ሲፈትነው ይህን አለ
እንጂ፥ እርሱስ የሚያደርገውን ያውቅ ነበር።
፯ፊልጶስም መልሶ እንዲህ አለው፥ “ከእነርሱ
ለእያንዳንዱ ጥቂት ጥቂት ይወስዱ ዘንድ የሁ
ለት መቶ ዲናር እንጀራ አይበቃቸውም።”
፰ከደቀ መዛሙርቱም አንዱ የስምዖን ጴጥሮስ
ወንድም እንድርያስ እንዲህ አለው፥ ፱“አም
ስት የገብስ እንጀራና ሁለት ዓሣ የያዘ ብላቴና
በዚህ አለ፤ ነገር ግን እነዚህ ይህን ለሚያህል
ሰው ምን ይበቃሉ?” ፲ጌታችን ኢየሱስም፥
“ሰዎቹን እንዲቀመጡ አድርጉ” አለ፤ የዚያ
ቦታም ሣሩ ብዙ ነበር፤ ወንዶቹም በመስኩ
ላይ ተቀመጡ፤ ቍጥራቸውም አምስት ሺህ
ያህል ነበር። ፲፩ጌታችን ኢየሱስም ያን እንጀራ
ይዞ አመሰገነ፤ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣ
ቸው፤ ደቀ መዛሙርቱም ለተቀመጡት ሰዎች
ሰጡአቸው፤[፩] ከዓሣውም እንዲሁ የፈለጉትን
ያህል ሰጡአቸው። ፲፪ከጠገቡም በኋላ ደቀ መዛ
ሙርቱን፥ “ከቍርስራሹ ምንም የሚወድቅ እን
ዳይኖር የተረፈውን ቍርስራሽ አንሡ፤” አላ
ቸው። ፲፫እነርሱም ሰበሰቡ፥ በልተው ከጠገቡ
በኋላም ከአምስቱ የገብስ እንጀራ የተረፈው
ቍርስራሽ ዐሥራ ሁለት መሶብ ሞላ። ፲፬ሕዝ
ቡም ጌታችን ኢየሱስ ያደረገውን ተአምራት
አይተው፥ “ይህ በእውነት ወደ ዓለም የሚመ
ጣው ነቢይ ነው” አሉ። ፲፭ጌታችን ኢየሱስም
መጥተው ነጥቀው ሊያነግሡት እንደሚሹ ዐወ
ቀባቸውና ብቻውን ወደ ተራራ ሄደ።

### በባሕር ላይ ስለ መሄዱ

(ማቴ. ፲፬፥፳፪-፴፫፤ ማር. ፮፥፵፭-፶፪)

፲፮በመሸም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ባሕር
ወረዱ። ፲፯ወደ ታንኳም ወጡ፤ ወደ ባሕር
ማዶ ወደ ቅፍርናሆምም ሄዱ፤ እነሆም፥
ፈጽሞ ጨለማ ሆነ፤ ጌታችን ኢየሱስም ወደ
እነርሱ ገና አልመጣም ነበር። ፲፰ባሕሩ ግን
ይታወክ ነበር፤ ጽኑ ነፋስ ይነፍስ ነበርና።
፲፱ሃያ አምስት ወይም ሠላሳ ምዕራፍ ያህል
ከሄዱ በኋላ ጌታችን ኢየሱስን በባሕር ላይ
ሲሄድ አዩት፤ ወደ ታንኳዉ በቀረበ ጊዜም
ፈሩ። ፳እርሱም፥ “እኔ ነኝ፤ አትፍሩ” አላ
ቸው። ፳፩ወደ ታንኳውዪቱ ሊያወጡት ሲሹም
ታንኳዪቱ ወዲያውኑ ሊሄዱ ወደ ወደዱበት
ወደብ ደረሰች። ፳፪በማግሥቱም ከባሕሩ ዳር
ቆመው የነበሩ ሰዎች ከአንዲት ታንኳ በቀር
ከዚያ ሌላ ታንኳ እንዳልነበረ፥ ደቀ መዛሙ
ርቱም ለብቻቸው ሄዱ እንጂ ጌታችን ኢየ
ሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ታንኳ እንዳ
ልወጣ አዩ። ፳፫ደግሞም ጌታችን የባረከውን
እንጀራ ከበሉበት ቦታ አቅራቢያ ከጥብርያዶስ
ሌሎች ታንኳዎች መጥተው ነበር። ፳፬እነዚያ
ሰዎችም ጌታችን ኢየሱስ፥ ደቀ መዛሙርቱም
በዚያ እንዳልነበሩ ባዩ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስን
ይፈልጉት ዘንድ በእነዚያ ታንኳዎች ገብተው
ወደ ቅፍርናሆም መጡ። ፳፭በባሕሩ ዳርም ባገ
ኙት ጊዜ፥ “መምህር ሆይ፥ ወደዚህ መቼ
መጣህ?” አሉት።

### ስለ ሕይወት ምግብ

፳፮ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላ
ቸው፥ “እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ እናንተ

---

[፩] “ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው ደቀ መዛሙርቱም ለተቀመጡት ሰጡአቸው” የሚለው በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ የለም።

የምትፈልጉኝ እንጀራ ስለ በላችሁና ስለ ጠገ
ባችሁ ነው እንጂ ተአምራት ስለ አያችሁ አይ
ደለም። ፳፯የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ለዘለዓለም
ሕይወት ለሚኖር መብል ሥሩ እንጂ ለሚጠ
ፋው መብል አይደለም፤ ይህን እግዚአብሔር
አብ አትሞታልና።” ፳፰“እንግዲህ የእግዚአብ
ሔርን ሥራ እንሠራ ዘንድ ምን እናድርግ?”
አሉት። ፳፱ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፥ “ይህ
የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በላከው ታምኑ
ዘንድ ነው፤” አላቸው።

## ምልክት ስለ መጠየቃቸው

፴እነርሱም እንዲህ አሉት፤ “የምትሠራውን
አይተን በአንተ እናምን ዘንድ ምን ተአምራት
ታደርጋለህ? ፴፩አባቶቻችንስ ‘ሊበሉ እንጀራ
ከሰማይ ሰጣቸው’ ተብሎ እንደ ተጻፈ በምድረ
በዳ መና በሉ። ፴፪ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ
አላቸው፥ “እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ ያን
እንጀራ ከሰማይ የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም፤
አባቴ ከሰማይ የእውነት እንጀራን ሰጥቶአችኋል
እንጂ። ፴፫የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚ
ወርድ፥ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነውና።”
፴፬እነርሱም፥ “አቤቱ ከዚያ እንጀራ ሁልጊዜ
ስጠን” አሉት።

## ስለ ሕይወት ኅብስት

፴፭ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፥ “የሕ
ይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ
ከቶ አይራብም፤ በእኔ የሚያምንም ለዘለዓለም
አይጠማም። ፴፮ነገር ግን እላችኋለሁ፤ አያች
ሁኝ፤ አላመናችሁብኝምም። ፴፯አብ የሚሰጠኝ
ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፤ ወደ እኔ የሚመጣው
ንም ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም። ፴፰ከሰማይ
የወረድሁ የላከኝን ፈቃድ እንጂ፤ ፈቃዴን ላደ
ርግ አይደለምና። ፴፱የላከኝ የአብ ፈቃድም ይህ
ነው፤ ከሰጠኝ ሁሉ አንድስ እንኳ ቢሆን እን
ዳይጠፋ ነው፤ ነገር ግን እኔ በኋለኛዪቱ ቀን
አስነሣዋለሁ። ፵የአባቴ ፈቃዱ ይህ ነው፤ ወል
ድን አይቶ የሚያምንበት ሁሉ የዘለዓለም ሕይ
ወትን እንዲያገኝ ነው፤ እኔም በመጨረሻዪቱ
ቀን አስነሣዋለሁ።”

## ስለ አይሁድ ማንጐራጐር

፵፩አይሁድም ስለ እርሱ አንጐራጐሩ፤
“ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ”
ብሎአቸዋልና። ፵፪“እኛ አባቱንና እናቱን የም
ናውቃቸው ይህ የዮሴፍ ልጅ ኢየሱስ አይደ
ለምን? እንግዲህ እንዴት ከሰማይ ወረድሁ
ይለናል?” አሉ። ፵፫ጌታችን ኢየሱስም መልሶ
እንዲህ አላቸው፥ “እርስ በርሳችሁ አታንጐ
ራጕሩ። ፵፬የላከኝ አብ ካልሳበው በቀር ወደ
እኔ መምጣትን የሚችል የለም፤ እኔም በመ
ጨረሻዪቱ ቀን አስነሣዋለሁ። ፵፭‘ሁሉም ከእ
ግዚአብሔር ዘንድ የተማሩ ይሆናሉ’ ተብሎ
በነቢያት መጽሐፍ ተጽፎአል፤ እንግዲህ
ከአባቱ የሰማ ሁሉ ተምሮ ወደ እኔ ይመ
ጣል። ፵፮ከእግዚአብሔር ከሆነው በቀር አብን
ያየው ማንም የለም፤ እርሱም አብን አየው።
፵፯እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ በእኔ የሚ
ያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው። ፵፰የሕይ
ወት እንጀራ እኔ ነኝ። ፵፱አባቶቻችሁስ በም
ድረ በዳ መና በሉ፥ ሞቱም። ፶ከእርሱ የበላ
ሁሉ እንዳይሞት ከሰማይ የወረደ እንጀራ
ይህ ነው።”

## ስለ ሥጋውና ስለ ደሙ

፶፩“ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ እኔ
ነኝ፤ ከዚህ እንጀራ የሚበላ ለዘለዓለም ይኖ
ራል፤ ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው ይህ እን
ጀራ ሥጋዬ ነው።”
፶፪አይሁድም፥ “ይህ እንበላ ዘንድ ሥጋውን
ሊሰጠን እንዴት ይችላል?” ብለው እርስ በር
ሳቸው ተከራከሩ። ፶፫ጌታችን ኢየሱስም እን
ዲህ አላቸው፥ “እውነት እውነት እላችኋ
ለሁ፤ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ፥ ደሙ
ንም ካልጠጣችሁ የዘለዓለም ሕይወት የላች
ሁም። ፶፬ሥጋዬን የሚበላ፥ ደሜንም የሚጠጣ
የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ እኔም በኋለኛዪቱ
ቀን አነሣዋለሁ። ፶፭ሥጋዬ እውነተኛ መብል
ነውና፤ ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና።
፶፮ሥጋዬን የሚበላ፥ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ
ይኖራል፤ እኔም በእርሱ እኖራለሁ። ፶፯የላ
ከኝ አብ ሕያው እንደ ሆነ፥ እኔም ስለ አብ
ሕያው ነኝ፤ ሥጋዬንም የሚበላ እርሱ ደግሞ
ስለ እኔ ሕያው ሆኖ ይኖራል። ፶፰ከሰማይ
የወረደ እንጀራ ይህ ነው፤ አባቶቻችሁ በል
ተውት እንደሞቱበት ያለ መና አይደለም፤
ይህን እንጀራ የሚበላ ግን ለዘለዓለም ሕያው
ሆኖ ይኖራል።” ፶፱በቅፍርናሆምም በምኵራብ
ሲያስተምራቸው ይህን ተናገረ፤

---

፮፡ ፴፩ ዘፀ. ፲፮፡፬፤ ፲፭፤ መዝ. ፸፰፡፳፬። ፮፡ ፵፭ ኢሳ. ፶፬፡፲፫።

## ስለ ተጠራጠሩት ሰዎች

፷ከደቀ መዛሙርቱም ብዙዎቹ ይህን ሰም
ተው፥ "ይህ ነገር የሚያስጨንቅ ነው፤ ማንስ
ሊሰማው ይችላል?" አሉ። ፷፩ጌታችን ኢየሱ
ስም ደቀ መዛሙርቱ ስለዚህ ነገር እንደ አንጐ
ራጐሩ በልቡ ዐወቀባቸውና እንዲህ አላቸው፥
"ይህ ያሰናክላችኋልን? ፷፪እንግዲህ የሰው ልጅ
ቀድሞ ወደ ነበረበት ሲያርግ ብታዩት እንዴት
ይሆን? ፷፫ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው፤
ሥጋ ግን አንዳች አይጠቅምም፤ ይህም እኔ
የምነግራችሁ ቃል መንፈስ ነው፤ ሕይወትም
ነው። ፷፬ነገር ግን ከእናንተ ውስጥ የማያምኑ
አሉ፤" ጌታችን ኢየሱስ ከጥንት ጀምሮ የማ
ያምኑበት እነማን እንደ ሆኑ፥ የሚያሲዘውም
ማን እንደ ሆነ ያውቅ ነበርና። ፷፭እንዲህም
አላቸው፥ "ስለዚህ እላችኋለሁ፤ ከአብ ካል
ተሰጠው በቀር ወደ እኔ መምጣት የሚቻለው
የለም።"

፷፮ስለዚህም ከደቀ መዛሙርቱ ወደ ኋላ
ቻው የተመለሱ ብዙዎች ናቸው፤ ከዚያም
ወዲህ አብረውት አልሄዱም። ፷፯ጌታችን ኢየ
ሱስም ዐሥራ ሁለቱን፥ "እናንተ ደግሞ ልት
ሄዱ ትሻላችሁን?" አላቸው። ፷፰ስምዖን ጴጥ
ሮስም መልሶ እንዲህ አለው፥ "አቤቱ፥ የዘለ
ዓለም የሕይወት ቃል እያለህ ወደ ማን እንሄ
ዳለን? ፷፱እኛስ የሕያው፩ እግዚአብሔር ልጅ
ክርስቶስ አንተ እንደ ሆንህ አምነናል፤ አውቀ
ናልም።" ፸ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ
አላቸው፥ "እኔ እናንተን ዐሥራ ሁለታችሁን
መርጫችሁ የለምን? ነገር ግን ከእናንተ አንዱ
ሰይጣን ነው።" ፸፩ይህንም ስለ ስምዖን ልጅ
ስለ አስቆሮታዊው ይሁዳ ተናገረ፤ እርሱ ያሲ
ዘው ዘንድ አለውና፤ እርሱም ከዐሥራ ሁለቱ
አንዱ ነበር።

## ምዕራፍ ፯

### ወደ ገሊላ ስለ መሄዱ

፩ከዚህ በኋላም ጌታችን ኢየሱስ በገሊላ ይመ
ላለስ ነበረ፤ ወደ ይሁዳ ምድርም ሊሄድ አልወ
ደደም፤ አይሁድ ሊገድሉት ይሹ ነበርና። ፪የአ
ይሁድም የዳስ በዓላቸው ደርሶ ነበር። ፫ወን
ድሞቹም ጌታችን ኢየሱስን እንዲህ አሉት፡
"ደቀ መዛሙርትህ የምትሠራውን ሥራህን እን
ዲያዩ ከዚህ ወጥተህ ወደ ይሁዳ ሀገር ሂድ።
፬ሊገለጥ ወድዶ ሳለ በስውር አንዳች ነገር የሚ
ያደርግ ማንም የለምና፤ አንተ ግን ይህን የም
ታደርግ ከሆነ ራስህን ለዓለም ግለጥ። ፭ወንድ
ሞቹ ገና አላመኑበትም ነበርና። ፮ጌታችን ኢየ
ሱስም እንዲህ አላቸው፥ "ጊዜዬ ገና አልደ
ረሰም፤ የእናንተ ጊዜ ግን ዘወትር የተዘጋጀ
ነው። ፯ዓለም እናንተን ሊጠላችሁ አይችልም፤
እኔን ግን ይጠላኛል፤ ሥራው ክፉ እንደ ሆነ
እኔ እመሰክርበታለሁና። ፰እናንተም ወደዚህ
በዓል ውጡ፤ እኔ አሁን ወደዚህ በዓል አልወ
ጣም፤ ጊዜዬ ገና አልደረሰምና።" ፱እርሱም
እንዲህ ብሎአቸው በገሊላ ቀረ።

### ወደ በዓል ስለ መውጣቱ

፲ወንድሞቹ ለበዓል ከወጡ በኋላ፥ እርሱም
ያንጊዜ በግልጥ ሳይሆን ተሰውሮ ወጣ። ፲፩አይ
ሁድም፥ "የ ወዴት ነው?" እያሉ በበዓሉ
ይፈልጉት ጀመር። ፲፪ሕዝቡም ስለ እርሱ ብዙ
አንጐራጐሩ፥ "ደግ ሰው ነው" ያሉ ነበሩ፤
ሌሎች ግን፥ "አይደለም፤ ሕዝቡን ያስታል
እንጂ" አሉ። ፲፫ነገር ግን፥ አይሁድን በመ
ፍራት የእርሱን ነገር ገልጦ የተናገረ አልነበ
ረም።

### በበዓሉ ላይ ስለ ማስተማሩ

፲፬በበዓሉ ቀኖች እኩሌታም ጌታችን ኢየሱስ
ወደ መቅደስ ወጥቶ ያስተምር ጀመረ። ፲፭አይሁ
ድም፥ "ይህ ሳይማር መጽሐፍን እንዴት ያው
ቃል?" እያሉ ትምህርቱን፪ አደነቁ። ፲፮ስለዚ
ህም ጌታችን ኢየሱስ መልሶ እንዲህ አላቸው፥
"ትምህርቴ የላከኝ ናት እንጂ የእኔ አይደለ
ችም። ፲፯ፈቃዱን ሊያደርግ የሚወድድ ግን
ትምህርቴ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ሆነች፥
የምናገረውም ከራሴ እንዳይደለ እርሱ ያው
ቃል። ፲፰ከራሱ የሚናገር የራሱን ክብር ይሻል፤
የላከውን ያከብር ዘንድ የሚፈልግ ግን እውነ
ተኛ ነው፤ ሐሰትም የለበትም። ፲፱ሙሴ ኦሪትን
ሰጥቶአችሁ የለምን? ከእናንተ አንዱ ስንኳ ኦሪ
ትን የሚያደርግ የለም፤ እንግዲህ ልትገድሉኝ
ለምን ትሻላችሁ?" ፳ሕዝቡም፥ "ጋኔን አለብ

፩ ግሪኩ እና አንዳንድ የግእዝ ዘርዕ "ቅዱስ" ይላል።
፪ "ትምህርቱን" የሚለው በግሪኩ የለም።
፮፡ ፷፰-፷፱ ማቴ. ፲፮፡፲፮፤ ማር. ፰፡፳፱፤ ሉቃ. ፱፡፳። ፯፡፪ ዘሌ. ፳፫፡፴፬፤ ዘዳ. ፲፮፡፲፫።

ህን? ማን ሊገድልህ ይሻል?” ብለው መለሱ
ለት። ፳፩ጌታችን ኢየሱስም መልሶ አላቸው፥
“አንድ ሥራ ሠራሁ፤ ሁላችሁም አደነቃችሁ።
፳፪ስለዚህ ሙሴ ግዝረትን ሰጥቶአችሁ ነበር፤
ነገር ግን ከአባቶች ናት እንጂ ከሙሴ አይደ
ለችም፤ በሰንበትም ሰውን ትገዝሩታላችሁ።
፳፫የሙሴ ሕግ እንዳይሻር ሰው በሰንበት የሚገ
ዘር ከሆነ እንግዲያ ሰውን ሁለንተናውን በሰን
በት ባድነው ለምን ትነቀፉኛላችሁ? ፳፬የእው
ነት ፍርድ ፍረዱ እንጂ ለሰው ፊት በማድላት
አትፍረዱ።”

## ስለ ሕዝቡ ዋይታ

፳፭ከኢየሩሳሌም ሰዎችም እንዲህ የሚሉ
ነበሩ፥ “ይህ አይሁድ ሊገድሉት የሚሹት አይ
ደለምን? ፳፮እነሆ፥ እርሱ በገሀድ ይናገራል፤
እነርሱ ግን ምንም የሚሉት የለም፤ ይህ በእው
ነት ክርስቶስ እንደ ሆነ ምናልባት አለቆች ዐው
ቀው ይሆን? ፳፯ነገር ግን ይህን ከየት እንደ ሆነ
እናውቃለን፤ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜስ ከወ
ዴት እንደ ሆነ ማንም አያውቅም”። ፳፰ጌታ
ችን ኢየሱስም በመቅደስ ሲያስተምር ቃሉን
ከፍ አድርጎ እንዲህ አለ፥ “እኔን ታውቁኛላ
ችሁ፤ ከወዴትም እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ፤
እኔ ራሴ የመጣሁ አይደለሁም፤ ነገር ግን እና
ንተ የማታውቁት የላከኝ እውነተኛ አለ። ፳፱እኔ
ግን አውቀዋለሁ፤ እኔ ከእርሱ ነኝና፥ እርሱም
ልኮኛልና። ፴ስለዚህም ሊይዙት ወደው ነበር፤
ነገር ግን እጁን በእርሱ ላይ ያነሣ የለም፤
ጊዜዉ ገና አልደረሰም ነበርና። ፴፩ከሕዝቡም
ብዙዎች አመኑበትና፥ “በውኑ ክርስቶስ በሚ
መጣበት ጊዜ ይህ ሰው ካደረገው ተአምራት
የሚበልጥ ያደርጋልን?” አሉ።

## ፈሪሳውያን ሊይዙት ሎሌዎችን እንደ ላኩ

፴፪ፈሪሳውያንም ሕዝቡ በእርሱ ምክንያት
እንደ አጕረመረሙ ሰሙ፤ የካህናት አለቆችና
ፈሪሳውያንም ይይዙት ዘንድ ሎሌዎቻቸውን
ላኩ። ፴፫ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፥
“ጥቂት ቀን አብሬአችሁ እኖራለሁ፤ ከዚህም
በኋላ ወደ ላከኝ እሄዳለሁ። ፴፬ትሹኛላችሁ፤
አታገኙኝምም፤ እኔ ወደምሄድበትም እናንተ
መምጣት አትችሉም።” ፴፭አይሁድም እርስ
በርሳቸው እንዲህ አሉ፥ “እኛ ልናገኘው የማ
ንችል ይህ ወዴት ይሄዳል? ወይስ የግሪክን
ሰዎች ለማስተማር በግሪክ ሀገር ወደ ተበተኑት
ይሄዳልን? ፴፮‘ትሹኛላችሁ፤ አታገኙኝምም፤
እኔ ወደምሄድበት እናንተ መምጣት አትች
ሉም’ የሚለን ይህ ነገር ምንድን ነው?”

## ስለ መንፈስ ቅዱስ

፴፯በኋለኛዪቱ በታላቅዋ የበዓል ቀንም
ጌታችን ኢየሱስ ቆመና ድምፁን ከፍ አድ
ርጎ እንዲህ አለ፥ “የተጠማ ወደ እኔ ይም
ጣና ይጠጣ። ፴፰በእኔም የሚያምን መጽሐፍ
እንደ ተናገረ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈ
ልቃል።” ፴፱ይህንም የሚያምኑበት ሰዎች ይቀ
በሉት ዘንድ ስለ አላቸው ስለ መንፈስ ቅዱስ
ተናገረ፤ ጌታችን ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መን
ፈስ ቅዱስ ገና አልወረደም ነበርና።

## በአይሁድ መካከል ስለ ሆነው መለያየት

፵ከሕዝቡም ብዙ ሰዎች ይህን ነገር ሰምተው
“በእውነት ይህ ነቢይ ነው” አሉ። ፵፩“ክር
ስቶስ ነው” ያሉም አሉ፤ እኩሌቶቹም እን
ዲህ አሉ፥ “በውኑ ክርስቶስ ከገሊላ ይወጣ
ልን? ፵፪መጽሐፍ ‘ክርስቶስ ከዳዊት ዘርና ከዳ
ዊት ከተማ ከቤተ ልሔም ይመጣል’ ይል የለ
ምን?” ፵፫ስለ እርሱም ሕዝቡ እርስ በርሳቸው
ተለያዩ። ፵፬ከእነርሱም ሊይዙት የወደዱ ነበሩ፤
ነገር ግን በእርሱ ላይ እጁን ያነሣ የለም።
፵፭ሎሌዎቹም ወደ ካህናት አለቆችና ወደ
ፈሪሳውያን ተመለሱ፤ እነርሱም፥ “ያላመጣ
ችሁት ለምንድን ነው?” አሉአቸው። ፵፮ሎሌ
ዎቻቸውም መልሰው፥ “ያ ሰው እንደ ተናገ
ረው ያለ ከቶ ሰው አልተናገረም” አሉአቸው።
፵፯ፈሪሳውያንም መልሰው እንዲህ አሉአቸው፥
“እናንተም ደግሞ ተሳሳታችሁን? ፵፰ከአለቆች
ወይም ከፈሪሳውያን ያመነበት አለን? ፵፱ኦሪትን
ከማያውቁ ከእነዚህ ስሑታን ሕዝብ በቀር፤ እነ
ርሱም የተረገሙ ናቸው።” ፶ከእነርሱም አንዱ
ቀድሞ በሌሊት ወደ ጌታችን ኢየሱስ የሄደው
ኒቆዲሞስ እንዲህ አላቸው። ፶፩“ሕጋችን አስ
ቀድሞ ሳይሰማ፥ የሠራውንም ሳያውቅ በሰው
ይፈርዳልን?” ፶፪እነርሱም መልሰው፥ “አንተም
ደግሞ ከገሊላ ነህን? ከገሊላ ነቢይ እንደማይነሣ
መርምርና እይ” አሉት። ፶፫ሁሉም እያንዳንዳ
ቸው ወደ ቤታቸው ሄዱ።

፯፥፳፪ ዘፍ. ፲፯፥፲፤ ዘሌ. ፲፪፥፫። ፯፥፳፫ ዮሐ. ፭፥፱። ፯፥፴፯ ዘሌ. ፳፫፥፴፮።
፯፥፴፰ ሕዝ. ፵፯፥፩፤ ዘካ. ፲፬፥፰። ፯፥፵፪ ፪ሳሙ. ፯፥፲፪፤ ሚክ. ፭፥፪። ፯፥፶ ዮሐ. ፫፥፩-፪።

## ምዕራፍ ፰

### ስለ አመንዝራዪቱ ሴት ፍርድ

፩ጌታችን ኢየሱስም ወደ ደብረ ዘይት ሄደ።
፪በጥዋትም ገስግሦ ዳግመኛ ወደ ቤተ መቅደስ
ገባ፤ ሕዝቡም ሁሉ ወደ እርሱ ተሰበሰቡ፤ እር
ሱም ተቀምጦ ያስተምራቸው ጀመር። ፫ጻፎ
ችና ፈሪሳውያንም በዝሙት የተያዘች ሴት
ወደ እርሱ አምጥተው በመካከል አቆሙአት።
፬እንዲህም አሉት፥ "መምህር ሆይ፥ ይቺን
ሴት ስታመነዝር አግኝተን ያዝናት። ፭እንደዚ
ችም ያለችው በድንጋይ እንድትደበደብ ሙሴ
በኦሪት አዘዘን፤ እንግዲህ አንተ ስለ እርስዋ
ምን ትላለህ?" ፮በእርሱም ላይ ምክንያት ሊያ
ገኙ ሲፈትኑት ይህን አሉ፤ ጌታችን ኢየሱ
ስም ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ።
፯ብዙ ጊዜ መላልሰው በጠየቁት ጊዜም ዐይኖ
ቹን አንሥቶ፥ "ከእናንተ ኀጢአት የሌለበት
አስቀድሞ ድንጋይ ይጣልባት" አላቸው። ፰ዳግ
መኛም ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ።
፱እነርሱ ግን ይህን በሰሙ ጊዜ ኅሊናቸው ወቅ
ሶአቸው ከሽማግሌዎች ጀምሮ እስከ ኋለኞቹ
ድረስ፥ አንዳንድ እያሉ ወጡ፤ ጌታችን ኢየ
ሱስም ብቻውን ቀረ፤ ሴትዮዪቱም በመካከል
ቆማ ነበር። ፲ጌታችን ኢየሱስም ቀና ብሎ ወደ
እርስዋ ተመለከተና እንዲህ አላት፥ "አንቺ
ሴት፥ የሚከሱሽ ወዴት አሉ?" ፲፩እርስዋም፥
"ጌታ ሆይ፥ የማየው የለም" ብላ መለሰችለት፤
ጌታችን ኢየሱስም፥ "እኔም አልፈርድብሽም፤
ወደ ቤትሽ ሂጂ፤ ከእንግዲህ ወዲህ ዳግመኛ
ኀጢአት አትሥሪ" አላት።

### ኢየሱስ የዓለም ብርሃን

፲፪ዳግመኛም ጌታችን ኢየሱስ፥ "የዓለም
ብርሃን እኔ ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብር
ሃንን ያገኛል እንጂ በጨለማ ውስጥ አይመላ
ለስም" ብሎ ተናገራቸው። ፲፫ፈሪሳውያንም፥
"አንተ ስለ ራስህ ትመሰክራለህ፤ እንግዲያስ
ምስክርነትህ እውነት አይደለም" አሉት።
፲፬ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፥
"እኔ ስለራሴ ብመሰክርም ምስክርነቴ እውነት
ነው፤ ከየት እንደመጣሁ፥ ወዴት እንደምሄድም
አውቃለሁና፤ እናንተ ግን ከየት እንደ መጣሁ
ወዴት እንደምሄድም አታውቁም። ፲፭እናንተ
ሥጋዊ ፍርድን ትፈርዳላችሁ፤ እኔ ግን በማ
ንም አልፈርድም። ፲፮እኔ ብፈርድም እውነትን
እፈርዳለሁ፤ እኔና የላከኝ አብ ነን እንጂ አንድ
ብቻዬን አይደለሁምና። ፲፯የሁለት ሰዎች ምስክ
ርነት የታመነ እንደ ሆነ በሕጋችሁ ተጽፎአል።
፲፰እኔ ስለ ራሴ ምስክር ነኝ፤ የላከኝ አብም
ይመሰክርልኛል።" ፲፱እነርሱም፥ "አባትህ የት
ነው?" አሉት፤ ጌታችን ኢየሱስም፥ "እኔን
አታውቁም፤ አባቴንም አታውቁም፤ እኔንስ
ብታውቁ አባቴንም ባወቃችሁት ነበር" ብሎ
መለሰላቸው። ፳ጌታችን ኢየሱስም በቤተ መቅ
ደስ ሲያስተምራቸው በሙዳየ ምጽዋት አጠገብ
ይህን ተናገራቸው፤ ነገር ግን አልያዙትም፤
ጊዜው ገና አልደረሰም ነበርና።

### አይሁድ ጌታችን ወደሚሄድበት መሄድ ስላለመቻላቸው

፳፩ዳግመኛም ጌታችን ኢየሱስ፥ "እኔ እሄዳ
ለሁ ትሹኛላችሁም፤ ነገር ግን አታገኙኝም፤[፩]
በኀጢአታችሁም ትሞታላችሁ፤ እኔ ወደምሄድ
በትም እናንተ መምጣት አይቻላችሁም" አላ
ቸው። ፳፪አይሁድም፥ "እኔ ወደምሄድበት እና
ንተ መምጣት አትችሉም የሚለን እርሱ ራሱን
ይገድል ይሆን? እንጃ!" አሉ። ፳፫እርሱም እን
ዲህ አላቸው፥ "እናንተስ ከታች ናችሁ፤ እኔ
ግን ከላይ ነኝ፤ እናንተ ከዚህ ዓለም ናችሁ፤ እኔ
ግን ከዚህ ዓለም አይደለሁም። ፳፬እነሆ፥ በኀጢ
አታችሁ ትሞታላችሁ እንዳልኋችሁ፥ እኔ እንደ
ሆንሁ ባታምኑ በኀጢአትችሁ ትሞታላችሁ።"
፳፭እነርሱም፥ "አንተ ማነህ?" አሉት፤ ጌታችን
ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፥ "በመጀመሪያ ነግሬ
አችኋለሁ። ፳፮ስለ እናንተ የምናገረውና የምፈር
ደው ብዙ አለኝ፤ የላከኝም እውነተኛ ነው፤ እኔ
በእርሱ ዘንድ የሰማሁትን ለዓለም እናገራለሁ።"
፳፯ነገር ግን ስለ አብ እንደ ነገራቸው አላስተዋ
ሉም። ፳፰ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፥
"የሰውን ልጅ ከፍ ከፍ በአደረጋችሁት ጊዜ እኔ
እንደ ሆንሁ ያንጊዜ ታውቃላችሁ፤ አባቴ እንደ
አስተማረኝም እንዲሁ እናገራለሁ እንጂ የምና
ገረው ከእኔ አይደለም። ፳፱የላከኝም ከእኔ ጋር
አለ፤ አብ ብቻዬን አይተወኝም፤ እኔም ዘወትር
ደስ የሚያሰኘውን አደርጋለሁ።" ፴ይህንም በተ
ናገረ ጊዜ ብዙዎች በእርሱ አመኑ።

---

፩ "አታገኙኝም" የሚለው በግሪኩ የለም።

፰፥፭ ዘሌ. ፳፥፲፤ ዘዳ. ፳፪፥፳፪-፳፬።  ፰፥፲፪ ማቴ. ፭፥፲፬፤ ዮሐ. ፱፥፭።  ፰፥፲፫ ዮሐ. ፭፥፴፩።

### ከአይሁድ ወገን ላመኑት የተነገረ

፴፩ጌታችን ኢየሱስም ያመኑበትን አይሁድ
እንዲህ አላቸው፦ “እናንተም በቃሌ ጸንታችሁ
ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ።
፴፪እውነትንም ታውቋታላችሁ፤ እውነትም አር
ነት ታወጣችኋለች።” ፴፫እነርሱም መለሰው፦
“እኛ የአብርሃም ዘር ነን፤ ከሆነ ጀምሮ ለማ
ንም ከቶ ባሮች አልሆንም፤ እንግዲህ እንዴት
አርነት ትወጣላችሁ ትለናለህ?” አሉት።
፴፬ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላ
ቸው፦ “እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ ኀጢ
አትን የሚሠራ ሁሉ የኀጢአት ባርያ ነው።
፴፭ባርያ ዘወትር በቤት አይኖርም፤ ልጅ ግን
ለዘለዓለም ይኖራል። ፴፮ወልድ አርነት ካወጣ
ችሁ በእውነት አርነት የወጣችሁ ናችሁ። ፴፯የአ
ብርሃም ዘር እንደ ሆናችሁስ አውቃለሁ፤ ነገር
ግን ቃሌ በእናንተ ዘንድ አይኖርምና ልትገድ
ሉኝ ትሻላችሁ። ፴፰እኔ በአባቴ ዘንድ ያየሁትን
እናገራለሁ፤ እናንተም በአባታችሁ ያያችሁ
ትን[፲፪] ታደርጋላችሁ።” ፴፱እነርሱም መለሰው፦
“የእኛስ አባታችን አብርሃም ነው” አሉት፤
ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፦ “የአብር
ሃም ልጆች ብትሆኑስ የአብርሃምን ሥራ በሠ
ራችሁ ነበር። ፵አሁንም በእግዚአብሔር ዘንድ
የሰማሁትን እውነት የምነግራችሁን[፲፫] ሰው ልት
ገድሉኝ ትሻላችሁ፤ አብርሃምስ እንዲህ አላደ
ረገም። ፵፩እናንተ ግን የአባታችሁን ሥራ ትሠ
ራላችሁ።” እነርሱም፦ “እኛ ከዝሙት አልተ
ወለድንም፤ ነገር ግን አንድ አባት አለን፤ እር
ሱም እግዚአብሔር ነው” አሉት። ፵፪ጌታችን
ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፦ “እግዚአብሔር
አባታችሁ ቢሆንስ እኔን በወደዳችሁኝ ነበር፤
እኔ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወጥቼ መጥቻለሁና፤
እኔ በገዛ እጄ የመጣሁ አይደለሁም፤ እርሱ
ላከኝ እንጂ። ፵፫እንግዲህ ቃሌን ለምን አታስ
ተውሉም? ቃሌን መስማት ስለማትችሉ ነው።
፵፬እናንተስ ከአባታችሁ ከሰይጣን ናችሁ፤ የአ
ባታችሁንም ፈቃድ ልታደርጉ ትወዳላችሁ፤
እርሱ ከጥንት ጀምሮ ነፍስ ገዳይ ነው፤ በእ
ውነትም አይቆምም፤ በእርሱ ዘንድ እውነት
የለምና፤ ሐሰትንም በሚናገርበት ጊዜ ከራሱ
አንቅቶ ይናገራል፤ ሐሰተኛ ነውና፤ የሐሰትም
አባት ነውና። ፵፭እኔ ግን እውነትን እናገራለ
ሁና አታምኑኝም። ፵፮ስለ ኀጢአት ከእናንተ
የሚወቅሰኝ ማን ነው? እኔ እውነት የምናገር
ከሆንሁ ለምን አታምኑኝም? ፵፯ከእግዚአብሔር
የሆነ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማል፤ ስለዚህ
እናንተ አትሰሙኝም፤ ከእግዚአብሔር አይደ
ላችሁምና።”

፵፰አይሁድም፦ “አንተ ሳምራዊ እንደ ሆንህ፥
ጋኔንም እንደ አለብህ መናገራችን በሚገባ አይደ
ለምን?” ብለው ጠየቁት። ፵፱ጌታችን ኢየሱስም
መልሶ እንዲህ አላቸው፦ “እኔ አባቴን አከብራለሁ
እንጂ ጋኔን የለብኝም፤ እናንተ ግን ትንቁኛላችሁ።
፶እኔ ለራሴ ክብርን አልሻም፤ የሚሻ፥ የሚፈርድም
አለ። ፶፩እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ ቃሌን የሚ
ጠብቅ ለዘለዓለም ሞትን አይቀምስም።” ፶፪አይሁ
ድም እንዲህ አሉት፦ “አሁን ጋኔን እንዳለብህ ዐወ
ቅን፤ አብርሃም ስንኳ ሞቶአል፤ ነቢያትም ሞተ
ዋል፤ አንተ ግን ቃሌን የሚጠብቅ ለዘለዓለም ሞትን
አይቀምስም ትላለህ። ፶፫በውኑ ከሞተው ከአባታ
ችን ከአብርሃም፥ አንተ ትበልጣለህን? ነቢያትም
ሞቱ፤ ራስህን ማን ታደርጋለህ?” ፶፬ጌታችን ኢየሱ
ስም መልሶ እንዲህ አላቸው፦ “እኔ ራሴን ባከብር
ክብሬ ምንም አይጠቅመኝም፤ የሚያከብረኝስ እና
ንተ አምላካችን የምትሉት አባቴ አለ። ፶፭እናንተም
አታውቁትም፤ እኔ ግን አውቀዋለሁ፤ አላውቀውም
ብልም እንደ እናንተ ሐሰተኛ እሆናለሁ፤ እኔ አው
ቀዋለሁ ቃሉንም እጠብቃለሁ። ፶፮አባታችሁ አብር
ሃም የእኔን ቀን ያይ ዘንድ ተመኘ፤[፲፬] አይቶም ደስ
አለው።” ፶፯አይሁድም፦ “ገና አምሳ ዓመት ያልሞ
ላህ እንዴት አብርሃምን አየህ?” አሉት። ፶፰ጌታችን
ኢየሱስም፦ “እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ አብር
ሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ።” አላቸው። ፶፱ሊደበድ
ቡትም ድንጋይ አነሡ፤ ጌታችን ኢየሱስ ግን ተሰወ
ራቸው፤ ከቤተ መቅደስም ወጣ፤ በመካከላቸውም
አልፎ ሄደ።

## ምዕራፍ ፱

### ዕዉር ሆኖ የተወለደውን ስለ ማዳኑ

፩ከዚያም ሲያልፍ ዕዉር ሆኖ የተወለደውን
ሰው አየ። ፪ደቀ መዛሙርቱም፦ “መምህር

---

፲፪ በግሪኩ “የሰማችሁትን” ይላል።
፲፫ አንዳንድ የግእዝ ዘርዕ “ጻድቅ” የሚል ይጨምራል።
፲፬ ግሪኩ “ሐሤት አደረገ” ይላል።
፰፡፴፫ ማቴ. ፫፥፱፤ ሉቃ. ፫፥፰።

ሆይ፥ ይህ ሰው ዕዉር ሆኖ የተወለደው በማን
ኀጢአት ነው? በራሱ ነውን? ወይስ በወላ
ጆቹ?” ብለው ጠየቁት። ፫ጌታችን ኢየሱስም
እንዲህ አላቸው፥ “የእግዚአብሔር ሥራ ሊገ
ለጥበት ነው እንጂ እርሱ አልበደለም፤ ወላጆ
ቹም አልበደሉም። ፬ነገር ግን ቀን ሳለ የላከኝን
ሥራ ልሠራ ይገባኛል፤ ማንም ሥራ ሊሠራ
የማይችልባት ሌሊት ትመጣለችና። ፭በዓለም
ሳለሁ፤ የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ።” ፮ይህንም
ብሎ በምድር ላይ ምራቁን እንትፍ አለ፤ በም
ራቁም ጭቃ አድርጎ የዕዉሩን ዐይኖች ቀባው።
፯እንዲህም አለው፥ “ሂድና በሰሊሆም መጠ
መቂያ ታጠብ” ትርጓሜውም የተላከ ማለት
ነው፤ ሄዶም ታጠበና እያየ ተመለሰ። ፰ጎረቤ
ቶቹና ቀድሞ የሚያውቁት፥፩ ሲለምንም ያዩት
የነበሩት ግን፥ “ይህ በመንገድ፪ ተቀምጦ ይለ
ምን የነበረው አይደለም?” አሉ። ፱“ይህ እርሱ
ነው” ያሉ አሉ፤ ሌሎችም፥ “አይደለም፤
ይመስለዋል እንጂ” አሉ፤ እርሱ ራሱ ግን፥
“እኔ ነኝ” አለ። ፲እነርሱም፥ “ዐይኖችህ እን
ዴት ተገለጡ?” አሉት። ፲፩እርሱም መለሰ፥
“ኢየሱስ የሚባለው ሰው በምራቁ ጭቃ አድ
ርጎ ዐይኖቼን ቀባኝና ሂደህ በሰሊሆም ውኃ
ታጠብ አለኝ፤ ሄጄም ታጠብሁና አየሁ” አላ
ቸው። ፲፪አይሁድም፥ “ሰውየው የት አለ?”
አሉት፤ እርሱም፥ “አላውቅም” አላቸው።

፲፫ያን ዕዉር ሆኖ የተወለደውንም ሰው ወደ
ፈሪሳውያን ወሰዱት። ፲፬ጌታችን ኢየሱስ በም
ራቁ ጭቃ አድርጎ ዐይኖቹን ያበራበት ቀኑ ሰን
በት ነበርና። ፲፭ፈሪሳውያንም እንዴት እንዳየ
ዳግመኛ ጠየቁት፤ እርሱም፥ “በምራቁ ጭቃ
አድርጎ በዐይኖቼ አኖረው፥ ታጥቤም አየሁ”
አላቸው። ፲፮ከፈሪሳውያንም አንዳንዶች፥ “ይህ
ሰው ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ሰንበትን አያ
ከብርምና” አሉ፤ ሌሎች ግን “ኀጢአተኛ
ሰው እንዲህ ያለ ተአምራት ማድረግ እንዴት
ይችላል?” አሉ፤ እርስ በርሳቸውም ተለያዩ።
፲፯ዳግመኛም ዕዉሩን፥ “አንተ ስለ እርሱ ምን
ትላለህ? ዐይኖችህን ከፍቶልሃልና” አሉት፤
እርሱም፥ “ነቢይ ነው” አላቸው።

፲፰አይሁድም የዚያን ያየውን ሰው ወላጆች
እስኪጠሩ ድረስ ዕዉር ሆኖ እንደ ተወለደ፥፫
እንዳየም አላመኑም። ፲፱“ዕዉር ሆኖ ተወ
ለደ የምትሉት ልጃችሁ ይህ ነውን? እንግ
ዲያ አሁን እንዴት ያያል?” ብለው ጠየቁአ
ቸው። ፳ወላጆቹም መልሰው እንዲህ አሉ፥
“ይህ ልጃችን እንደ ሆነ፥ ዕዉር ሆኖም እንደ
ተወለደ እናውቃለን። ፳፩አሁን ግን እንዴት እን
ደሚያይ ዐይኖቹንም ማን እንደ አበራለት አና
ውቅም፤ እርሱን ጠይቁት፤ ዐዋቂ ነውና፤ ስለ
ራሱም መናገር ይችላልና።” ፳፪ወላጆቹ አይሁ
ድን ስለ ፈሩ ይህን አሉ፤ “እርሱ ክርስቶስ
ነው ብሎ በእርሱ የሚያምን ቢኖር ከምኵራብ
ይውጣ” ብለው አይሁድ ተስማምተው ነበ
ርና። ፳፫ስለዚህም ወላጆቹ፥ “ዐዋቂ ነውና እር
ሱን ጠይቁት” አሉ። ፳፬ዕውር የነበረውንም
ሰው ዳግመኛ ጠርተው፥ “ሂድ ለእግዚአብ
ሔር ምስጋና አቅርብ፤ ይህ ሰው ኀጢአተኛ
እንደ ሆነ እኛ እናውቃለን” አሉት። ፳፭ያም
ሰው መልሶ እንዲህ አላቸው፥ “እርሱ ኀጢ
አተኛ እንደ ሆነ እኔ አላውቅም፤ እኔ ዕዉር
እንደ ነበርሁ፤ አሁን ግን እንደማይ ይህን
አንድ ነገር ብቻ አውቃለሁ።” ፳፮ዳግመኛም፥
“ምን አደረገልህ? ዐይኖችህንስ እንደምን አበ
ራልህ?” አሉት። ፳፯እርሱም መለሰ፤ “አት
ሰሙኝም እንጂ ነገርኋችሁ፤ እንግዲህ ደግሞ
ምን ልትሰሙ ትሻላችሁ? እናንተም ደቀ መዛ
ሙርቱ ልትሆኑ ትሻላችሁን?” አላቸው። ፳፰እነ
ርሱም ሰደቡት፤ እንዲህም አሉት፥ “አንተ የእ
ርሱ ደቀ መዝሙር ሁን፤ እኛስ የሙሴ ደቀ
መዛሙርት ነን። ፳፱እግዚአብሔር ሙሴን እንደ
ተነጋገረው እናውቃለን፤ ይህን ግን ከወዴት
እንደ ሆነ አናውቅም።” ፴ያም ሰው መልሶ
እንዲህ አላቸው፥ “ከወዴት እንደ ሆነ፥ አታ
ውቁትምና ይህ እጅግ ድንቅ ነው፤ ነገር ግን
ዐይኖቼን አበራልኝ። ፴፩እኛም እግዚአብሔርን
የሚፈራውንና ፈቃዱን የሚያደርገውን እር
ሱን ይሰማዋል እንጂ ኃጥኣንን እንደማይሰማ
ቸው እናውቃለን። ፴፪ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ
ዕዉር ሆኖ የተወለደውን ዐይኖች ያበራ አል
ተሰማም። ፴፫ይህ ሰው ከእግዚአብሔር ባይሆን
ኖሮ ምንም ማድረግ ባልቻለም ነበር።” ፴፬እነ
ርሱም መለሰው፥ “ራስህ በኀጢአት የተወለ
ድህ አንተ እኛን ታስተምረናለህን?” አሉት፤

---

፩ “የሚያውቁት” የሚለው በግሪኩ የለም።

፪ “በመንገድ” የሚለው በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ የለም።

፫ ግሪኩ “ዕዉር እንደ ነበረ” ይላል።

፱፥፭ ማቴ. ፭፥፲፬፤ ዮሐ. ፰፥፲፪።

ወደ ውጭም አወጡት። ፴፭ጌታችን ኢየሱስም
ወደ ውጭ እንዳወጡት ሰማ፤ አገኘውምና፥
"አንተ በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን?"
አለው። ፴፮ያ ሰውም፥ "አቤቱ፥ አምንበት
ዘንድ እርሱ ማነው?" ብሎ መለሰለት። ፴፯ጌታ
ችን ኢየሱስም፥ "የምታየው፥ ከአንተ ጋርም
የሚነጋገረው እርሱ ነው" አለው። ፴፰እርሱም፥
"አቤቱ፥ አምናለሁ" ብሎ ሰገደለት። ፴፱ጌታ
ችን ኢየሱስም፥ "እኔ የማያዩት እንዲያዩ፥
የሚያዩትም እንዲታወሩ ወደዚህ ዓለም ለፍ
ርድ መጥቻለሁ" አለው። ፵ከፈሪሳውያንም ከእ
ርሱ ጋር የነበሩት ይህን ሲናገር ሰምተው፥
"እኛ ደግሞ ዕዉሮች ነን?" አሉት። ፵፩ጌታ
ችን ኢየሱስም፥ "ዕዉሮችስ ብትሆኑ ኀጢኣት
ባልሆነባችሁም ነበር፤ አሁን ግን እናያለን ትላ
ላችሁ፤ አታዩምም፤ ስለዚህም ኀጢአታችሁ
ጸንቶ ይኖራል" አላቸው።

## ምዕራፍ ፲

### የበጎች በር ምሳሌ

፩"እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ ወደ በጎች
ስፍራ በበሩ የማይገባ፥ በሌላም በኩል የሚ
ገባ ሌባ፥ ወንበዴም ነው። ፪በበሩ የሚገባ ግን
የበጎች ጠባቂ ነው። ፫ለእርሱ በረኛው ይከፍ
ትለታል፤ በጎቹም ቃሉን ይሰሙታል፤ እር
ሱም በጎቹን በየስማቸው ይጠራቸዋል፤ አው
ጥቶም ያሰማራቸዋል። ፬ሁሉንም አውጥቶ ባሰ
ማራቸው ጊዜ በፊት በፊታቸው ይሄዳል፤ በጎ
ቹም ይከተሉታል፤ ቃሉን ያውቃሉና። ፭ሌላ
ውን ግን ይሸሹታል እንጂ አይከተሉትም፤ የሌ
ላውን ቃሉን አያውቁምና።" ፮ጌታችን ኢየሱ
ስም ይህን ምሳሌ ነገራቸው፤ እነርሱ ግን የነገ
ራቸውን አላወቁም።

፯ዳግመኛም ጌታችን ኢየሱስ እንዲህ አላ
ቸው፥ "እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ የበጎች
በር እኔ ነኝ። ፰ከእኔ በፊት የመጡ ሁሉ ሌቦ
ችና ወንበዴዎች ናቸው፤ ነገር ግን፤ በጎች
አልሰሙአቸውም። ፱እውነተኛዉ የበጎች[፩] በር
እኔ ነኝ፤ በእኔ በኩልም የሚገባ ይድናል፤ ይገ
ባልም ይወጣልም፤ መሰማርያም ያገኛል። ፲ሌባ
ግን ሊሰርቅና ሊያርድ፥ ሊያጠፋም ካልሆነ
በቀር አይመጣም፤ እኔ ግን የዘለዓለም[፪] ሕይ
ወትን እንዲያገኙ፥ እጅግም እንዲበዛላቸው
መጣሁ።

### ስለ ቸር ጠባቂ

፲፩"ቸር ጠባቂ እኔ ነኝ፤ ቸር ጠባቂ ስለ
በጎቹ ነፍሱን ይሰጣል። ፲፪ጠባቂ ያይደለ፥ በጎ
ቹም ገንዘቡ ያይደሉ ምንደኛ ግን፥ ተኵላ
ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል፤ ተኵ
ላም መጥቶ በጎቹን ይነጥቃቸዋል፥ ይበትናቸዋ
ልም። ፲፫ምንደኛስ ይሸሻል፤ ስለ በጎቹም አያ
ዝንም፤ ምንደኛ ነውና። ፲፬ቸር ጠባቂ እኔ ነኝ፤
የእኔ የሆኑትን መንጋዎቼን አውቃለሁ፤ የእኔ
የሆኑትም ያውቁኛል። ፲፭አብ እኔን እንደሚያው
ቀኝ እኔም አብን አውቀዋለሁ፤ ለበጎችም ቤዛ
አድርጌ ሰውነቴን አሳልፌ እሰጣለሁ። ፲፮ከዚህ
ቦታ ያይደሉ ሌሎች በጎችም አሉኝ፤ እነር
ሱንም ወደዚህ አመጣቸው ዘንድ ይገባኛል፤
ቃሌንም ይሰሙኛል፤ ለአንድ እረኛም አንድ
መንጋ ይሆናሉ። ፲፯ስለዚህም፤ አብ ይወድደ
ኛል፥ እንደ ገና እስነሣት ዘንድ እኔ ነፍሴን እሰ
ጣለሁና። ፲፰ከእኔ ማንም አይወስዳትም፤ ነገር
ግን እኔ በፈቃዴ እሰጣታለሁ፤ እኔ ላኖራት
ሥልጣን አለኝ፤ መልሼ እወስዳት ዘንድ ሥል
ጣን አለኝና፤ ይህንም ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበ
ልሁ።"

### አይሁድ ለሁለተኛ ጊዜ ስለ መለያየታቸው

፲፱ስለዚህም ነገር አይሁድ እንደገና እርስ በር
ሳቸው ተለያዩ። ፳ከእነርሱም ብዙዎች፥ "ጋኔን
ይዞት ያብዳል፤ ለምንስ ታዳምጡታላችሁ?"
አሉ። ፳፩ሌሎችም ይህ ነገር ጋኔን ከያዘው ሰው
የሚገኝ አይደለም፤ ጋኔን የዕዉሮችን ዐይን
ማብራት ይችላልን?" አሉ።

### ስለ ቤተ መቅደስ መታደስ

፳፪በዚያም ወራት በኢየሩሳሌም የመቅደስ
መታደስ በዓል ሆነ፤ ክረምትም ነበር። ፳፫ጌታ
ችን ኢየሱስም በቤተ መቅደስ በሰሎሞን ደጅ
መመላለሻ ይመላለስ ነበር። ፳፬አይሁድም እር
ሱን ከብበው፥ "እስከ መቼ ድረስ ሰውነታ
ችንን ታስጨንቀናለህ? አንተ ክርስቶስ እንደ

---

፩ "እውነተኛ የበጎች" የሚለው በግሪኩ የለም።

፪ "የዘለዓለም" የሚለው በግሪኩ የለም።

፲፥፱ መዝ. ፳፪፥፪፤ ሕዝ. ፴፬፥፲፩። ፲፥፲፩ ዮሐ. ፲፭፥፲፫፤ ኢሳ. ፵፥፲፩።

፲፥፲፭ ማቴ. ፲፩፥፳፯፤ ሉቃ. ፳፪፥፴፫፤ ዘሌ. ፳፬፥፲፯።

ሆንህ ገልጠህ ንገረን” አሉት። ፳፭ጌታችን ኢየ
ሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፥ “አታምኑኝም
እንጂ ነገርኋችሁ፤ እኔ በአባቴ ስም የምሠራው
ሥራ እርሱ ምስክሬ ነው። ፳፮እናንተ ግን አታ
ምኑኝም፤ እንደ ነገርኋችሁ ከበጎቼ ውስጥ አይ
ደላችሁምና። ፳፯የእኔ የሆኑ በጎቼ ግን ቃሌን
ይሰሙኛል፤ እኔም አውቃቸዋለሁ፤ እነርሱም
ይከተሉኛል። ፳፰እኔም የዘለዓለም ሕይወትን
እሰጣቸዋለሁ፤ ለዘለዓለሙም አይጠፉም፤ ከእ
ጄም የሚነጥቃቸው የለም። ፳፱እነርሱን የሰጠኝ
አባቴ እርሱ ከሁሉ ይበልጣልና፤ ከአባቴም
እጅ መንጠቅ የሚችል የለም። ፴እኔና አብ
አንድ ነን።”

## ስለ አይሁድ ጥላቻ

፴፩ዳግመኛም አይሁድ ሊወግሩት ድንጋይ
አነሡ። ፴፪ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ
አላቸው፥ “ከአባቴ ብዙ መልካም ሥራ አሳ
የኋችሁ፤ ከእነርሱ በየትኛው ሥራ ምክንያት
ትወግሩኛላችሁ?” ፴፫አይሁድም፥ “አንተ፥
ሰው ስትሆን ራስህን እግዚአብሔርን ታደር
ጋለህና፥ ስለ መሳደብህ ነው እንጂ ስለ መል
ካም ሥራህስ አንወግርህም” አሉት። ፴፬ጌታ
ችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፥ “እኔ
አማልክት ናችሁ አልሁ ተብሎ በኦሪታችሁ
ተጽፎ የለምን? ፴፭የእግዚአብሔር ቃል የመጣ
ላቸውን እነዚያን አማልክት ካላቸው፥ የመጽ
ሐፉ ቃል ይታበል ዘንድ አይቻልም። ፴፮እኔ
የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብላችሁ፥ አብ የቀደ
ሰውንና ወደ ዓለምም የላከውን እንዴት ትሳ
ደባለህ? ትሉኛላችሁ። ፴፯የአባቴን ሥራ ባል
ሠራ በእኔ አትመኑ። ፴፰ከሠራሁ ግን፥ እኔን
እንኳን ባታምኑ እኔ በአብ እንዳለሁ አብም
በእኔ እንዳለ ታውቁና ትረዱ ዘንድ ሥራዬን
እመኑ።” ፴፱ዳግመኛም ሊይዙት ፈለጉ፤ ከእጃ
ቸውም አመለጠ።

## ወደ ዮርዳኖስ ማዶ ስለ መሄዱ

፵ዳግመኛም ቀድሞ ዮሐንስ ያጠምቅበት
ወደ ነበረው ስፍራ ወደ ዮርዳኖስ ማዶ ሄደ፤
በዚያም ተቀመጠ። ፵፩ብዙዎችም ወደ እርሱ
ሄደው፥ “ዮሐንስ ምንም ያደረገው ተአምራት
የለም፤ ነገር ግን ዮሐንስ ስለዚህ ሰው የተናገ
ረው ሁሉ እውነት ሆነ” አሉ። ፵፪በዚያም ብዙ
ሰዎች አመኑበት።

## ምዕራፍ ፲፩

## ስለ አልዓዛር

፩የማርያምና የእኅቷ የማርታ መንደር በሚ
ሆን በቢታንያ ስሙ አልዓዛር የሚባል የታ
መመ አንድ ሰው ነበር። ፪ማርያም ግን ጌታች
ንን ሽቱ የቀባችው፥ እግሩንም በጠጕርዋ ያሸ
ችው ናት፤ ወንድምዋ አልዓዛርም ታሞ ነበር።
፫እኅቶቹም፥ “ጌታችን ሆይ፥ እነሆ፥ የምትወ
ደው ታሞአል” ብለው ወደ ጌታችን ኢየሱስ
ላኩ። ፬ጌታችን ኢየሱስም ሰምቶ እንዲህ አለ፥
“ይህ ደዌ በእርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይከ
ብር ዘንድ ስለ እግዚአብሔር ክብር ነው እንጂ
ለሞት አይደለም።”
፭ጌታችን ኢየሱስም ማርታንና እኅቷን ማር
ያምን፥ አልዓዛርንም ይወዳቸው ነበር። ፮እንደ
ታመመ በሰማ ጊዜም በነበረበት ቦታ ሁለት
ቀን ቈየ። ፯ከዚህም በኋላ፥ ደቀ መዛሙርቱን፥
“ኑ፥ ወደ ይሁዳ ሀገር ደግሞ እንሂድ” አላ
ቸው። ፰ደቀ መዛሙርቱም፥ “መምህር ሆይ፥
አይሁድ ሊወግሩህ ይሹ አልነበረምን? ዛሬ
ደግሞ አንተ ወደዚያ ልትሄድ ትሻለህን?”
አሉት። ፱ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ
አላቸው፥ “ቀኑ ዐሥራ ሁለት ሰዓት አይደለ
ምን? በቀን የሚሄድ አይሰናከልም፤ የዚህን
ዓለም ብርሃን ያያልና። ፲በሌሊት የሚሄድ ግን
ይሰነካከላል፤ በውስጡ የሚያየው ብርሃን የለ
ምና።” ፲፩ይህንም ለደቀ መዛሙርቱ፩ ነገራ
ቸው፤ ከዚህም በኋላ፥ “ወዳጃችን አልዓዛር
ተኝቶአል፤ ነገር ግን ላነቃው እሄዳለሁ” አላ
ቸው። ፲፪ደቀ መዛሙርቱም፥ “አቤቱ፥ ከተኛስ
ይነቃል፤፪ ይድናልም” አሉት። ፲፫ጌታችን ኢየ
ሱስም ስለ ሞቱ ተናገረ፤ እነርሱ ግን ስለ እን
ቅልፍ መተኛት መስሎአቸው ነበር። ፲፬ከዚህ
በኋላም ጌታችን ኢየሱስ ገልጦ እንዲህ አላ
ቸው፥ “አልዓዛር ሞተ። ፲፭ታምኑም ዘንድ እኔ
በዚያ ባለመኖሬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል፤
ነገር ግን ኑ፥ ወደ እርሱ እንሂድ።” ፲፮ዲዲሞስ

---

፩ “ለደቀ መዛሙርቱ” የሚለው በግሪኩ የለም።

፪ “ይነቃል” የሚለው በግሪኩ የለም።

፲፡፴፬ መዝ. ፹፩፡፮። ፲፡፵ ዮሐ. ፩፡፳፰። ፲፩፡፩ ሉቃ. ፲፡፴፰፡፴፱። ፲፩፡፪ ዮሐ. ፲፪፡፫።
፲፩፡፬ ዮሐ. ፱፡፫።

የሚሉት ቶማስም፥ ባልንጀሮቹን ደቀ መዛሙ
ርት፥ "እኛም ከእርሱ ጋር እንሞት ዘንድ እን
ሂድ" አላቸው።

### ጌታችን አልዓዛርን ስለ ማስነሣቱ

፲፯ጌታችን ኢየሱስም ወደ ቢታንያ ሄደ፤ ፫
ከዚያም በደረሰ ጊዜ ከተቀበረ አራት ቀን
ሆኖት አገኘው። ፲፰ቢታንያም ለኢየሩሳሌም
ዐሥራ አምስት ምዕራፍ ያህል ቅርብ ነበረች።
፲፱ከአይሁድም ስለ ወንድማቸው ሊያጽናኑአ
ቸው ወደ ማርያምና ወደ ማርታ የሄዱ ብዙ
ዎች ነበሩ። ፳ማርታም ጌታችን ኢየሱስ እንደ
መጣ በሰማች ጊዜ ወጥታ ተቀበለችው፤ ማር
ያም ግን በቤት ተቀምጣ ነበር። ፳፩ማርታም
ጌታችን ኢየሱስን እንዲህ አለችው፥ "ጌታዬ
ሆይ፥ በዚህ ኖረህ ቢሆን ወንድሜ ባልሞተም
ነበር። ፳፪አሁንም ከእግዚአብሔር የምትለምነ
ውን እግዚአብሔር እንዲሰጥህ አውቃለሁ።"
፳፫ጌታችን ኢየሱስም፥ "ወንድምሽስ ይነሣል"
አላት። ፳፬ማርታም፥ "ሙታን በሚነሡባት
በኋለኛዪቱ ቀን እንደሚነሣ አውቃለሁ" አለ
ችው።

### ክርስቶስ ትንሣኤና ሕይወት ስለ መሆኑ

፳፭ጌታችን ኢየሱስም አላት፥ "ትንሣኤና
ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞትም ይነ
ሣል። ፳፮ሕያው የሆነ የሚያምንብኝም ሁሉ
ለዘለዓለም አይሞትም፤ ይህንስ ታምኚለሽን?"
፳፯እርስዋም፥ "አዎን፥ ጌታዬ ሆይ፥ አንተ ወደ
ዓለም የሚመጣው የእግዚአብሔር ልጅ ክርስ
ቶስ እንደ ሆንህ እኔ አምናለሁ" አለችው።

### ጌታችን ለአልዓዛር ስለ ማልቀሱ

፳፰ይህንም ብላ ሄደች፤ እኅቷን ማርያም
ንም ቀስ ብላ ጠራችና፥ "እነሆ፥ መምህራ
ችን መጥቶ ይጠራሻል" አለቻት። ፳፱እርስዋም
ይህን በሰማች ጊዜ ፈጥና ተነሣች፤ ወደ እር
ሱም ሄደች። ፴ጌታችን ኢየሱስም ማርታ በተ
ቀበለችበት ስፍራ ነበረ እንጂ ገና ወደ መን
ደር አልገባም ነበር። ፴፩ሊያጽናኑአት መጥ
ተው በቤት ከእርስዋ ጋር የነበሩ አይሁድም
ፈጥና ተነሥታ እንደ ወጣች ባዩ ጊዜ በዚያ
ለወንድምዋ ልታለቅስ ወደ መቃብሩ የምት
ሄድ መስሎአቸው ተከተሉአት። ፴፪ማርያ
ምም ጌታችን ኢየሱስ ወደ አለበት ስፍራ ደረ
ሰችና በአየችው ጊዜ ከእግሩ በታች ሰግዳ፥
"ጌታዬ ሆይ፥ በዚህ ኑረህ ቢሆን ወንድሜ
ባልሞተም ነበር" አለችው። ፴፫ጌታችን ኢየሱ
ስም እርስዋ ስታለቅስ፥ ከእርስዋ ጋር የመጡ
አይሁድም ሲያለቅሱ ባየ ጊዜ በልቡ አዘነ፤
በራሱም ታወከ። ፴፬እርሱም፥ "የት ቀበራች
ሁት?" አለ፤ እነርሱም፥ "አቤቱ፥ መጥተህ
እይ" አሉት። ፴፭ጌታችን ኢየሱስም እንባውን
አፈሰሰ። ፴፮አይሁድም፥ "ምን ያህል ይወደው
እንደ ነበር እዩ" አሉ። ፴፯ከእነርሱም መካከል፥
"ዕዉር ሆኖ የተወለደውን ዐይን ያበራው ይህ
ሰው ይህስ እንዳይሞት ሊያደርግ ባልቻለም ነበ
ርን?" ያሉ ነበሩ።

፴፰ዳግመኛም ጌታችን ኢየሱስ በልቡ አዘነ፤ ወደ
መቃብሩም ሄደ፤ መቃብሩም ዋሻ ነበር፤ በላዩም
ታላቅ ድንጋይ ተገጥሞበት ነበር። ፴፱ጌታችን ኢየሱ
ስም፥ "ድንጋዩን አንሡ" አላቸው፤ የሟቹ እኅት
ማርታም፥ "ጌታዬ ሆይ፥ አራት ቀን ሆኖታልና
ፈጽሞ ሸትቶ ይሆናል" አለችው። ፵ጌታችን ኢየ
ሱስም፥ "ብታምኚስ የእግዚአብሔርን ክብር ታያ
ለሽ አላልሁሽም ነበርን?" አላት። ፵፩ድንጋዩንም
አነሡ፤ ጌታችን ኢየሱስም ዐይኖቹን አቅንቶ እን
ዲህ አለ፥ "አባት ሆይ፥ ሰምተኸኛልና አመሰግንሃ
ለሁ። ፵፪እኔም ዘወትር እንደምትሰማኝ አውቃለሁ፤
ነገር ግን አንተ እንደ ላክኸኝ ያምኑ ዘንድ በዚህ
ቆመው ስላሉት ሰዎች ይህን እናገራለሁ።" ፵፫ይህ
ንም ብሎ በታላቅ ቃል ጮኸና፥ "አልዓዛር፥ ና፤
ወደ ውጭ ውጣ" አለ። ፵፬ሞቶ የነበረውም እንደ
ተገነዘ፥ እጁንና እግሩንም እንደ ታሰረ፥ ፊቱም
በሰበን እንደ ተጠቀለለ ወጣ፤ ጌታችን ኢየሱስም፥
"እንግዲህስ ፍቱትና ተዉት ይሂድ" አላቸው።

፵፭ስለዚህ ከአይሁድም ወደ ማርታና ወደ ማር
ያም መጥተው የነበሩ ብዙ ሰዎች ጌታችን ኢየሱስ
ያደረገውን አይተው በእርሱ አመኑ። ፵፮ከእነርሱም
መካከል ወደ ፈሪሳውያን ሄደው የከሰሱት፬ ነበሩ፤
ጌታችን ኢየሱስ ያደረገውንም ሁሉ ነገሩአቸው።

### ስለ አይሁድ ምክር

(ማቴ. ፳፮፥፩-፭፤ ሉቃ. ፳፪፥፩-፪)

፵፯የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያንም ጉባኤ
ውን ሰብስበው እንዲህ አሉአቸው፥ "እነሆ፥

---

፫ "ጌታችን ኢየሱስም ወደ ቢታንያ ሄደ" የሚለው በግሪኩ የለም።

፬ "የከሰሱት" የሚለው በግሪኩ የለም።

፲፩፥፳ ሉቃ. ፲፥፴፰፡፵።    ፲፩፥፵፪ ዮሐ. ፲፪፥፳፱፡፴፤ ፲፯፥፳፩።

ይህ ሰው ብዙ ተአምራት ያደርጋል፤ ምን እና
ድርግ? ፵፰እንዲሁ ብንተወውም ሁሉ ያምኑ
በታል፤ የሮም ሰዎችም መጥተው ሀገራችን
ንና ወገናችንን ይወስዱብናል።” ፵፱በዚያችም
ዓመት የካህናት አለቃ የነበረው ስሙ ቀያፋ
የተባለው ከእነርሱ አንዱ እንዲህ አላቸው፥
“እናንተስ ምንም አታውቁም። ፶ምንም አት
መክሩም፤ ሕዝቡ ሁሉ ከሚጠፋ ስለ ሕዝቡ
አንድ ሰው ቢሞት ይሻለናል።” ፶፩ይህንም
ከልቡ የተናገረው አይደለም፤ ነገር ግን በዚ
ያች ዓመት የካህናት አለቃ ነበርና ጌታችን ኢየ
ሱስ ስለ ሕዝቡ ሁሉ ቤዛ ሆኖ ይሞት ዘንድ
ስላለው ይህን ትንቢት ተናገረ። ፶፪ስለ ሕዝቡ
ብቻ አልነበረም፤ የተበተኑትን የእግዚአብሔር
ንም ልጆች በአንድነት ይሰበስባቸው ዘንድ ነው
እንጂ። ፶፫ከዚያችም ቀን ጀምሮ የካህናት አለ
ቆች ሊገድሉት ተማከሩ።

### ጌታችን ኢየሩሳሌምን ትቶ ስለ መሄዱ

፶፬ከዚያም ወዲያ ጌታችን ኢየሱስ በአይሁድ
መካከል በግልጥ አልተመላለሰም፤ ነገር ግን
ለምድረ በዳ አቅራቢያ ወደ ሆነች ምድር፥ ኤፍ
ሬም ወደምትባል ከተማ ሄደ፤ በዚያም ከደቀ
መዛሙርቱ ጋር ተቀመጠ።
፶፭የአይሁድም የፋሲካ በዓል ቀርቦ ነበር፤
ብዙ ሰዎችም ከበዓሉ አስቀድሞ ራሳቸውን
ያነጹ ዘንድ ከየሀገሩ ወደ ኢየሩሳሌም ወጥተው
ነበር። ፶፮አይሁድም ጌታችን ኢየሱስን ይፈል
ጉት ጀመር፤ በቤተ መቅደስም ቆመው እርስ
በርሳቸው፥ “ምን ይመስላችኋል? ለበዓል አይ
መጣ ይሆን?” ተባባሉ። ፶፯የካህናት አለቆችና
ፈሪሳውያንም ያለበትን የሚያውቅ ቢኖር ይይ
ዙት ዘንድ እንዲያመለክታቸው አዘዙ።

## ምዕራፍ ፲፪

### ጌታችንን ሽቱ ስለ ቀባችው ሴት

(ማቴ. ፳፮፥፮-፲፫፤ ማር. ፲፬፥፫-፱)

፩ፋሲካ ከሚውልበት ከስድስተኛው ቀን አስ
ቀድሞ ጌታችን ኢየሱስ ከሙታን ያስነሣው
አልዓዛር ወደ ነበረበት ወደ ቢታንያ መጣ።
፪በዚያም ምሳ አደረጉለት፤ ማርታም ታሳልፍ
ላቸው ነበር፤ አብረውት ምሳ ከበሉትም አንዱ
አልዓዛር ነበር። ፫ማርያም ግን ዋጋዉ የከበ
ረና የበዛ አንድ ነጥር የጥሩ ናርዶስ ሽቱ ወሰ
ደችና የጌታችን ኢየሱስን እግር ቀባችው፤ በፀ
ጕሯም አሸችው፤ የዚያ ሽቱ መዓዛም ቤቱን
መላው። ፬ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ የነበረ ያሲ
ዘው ዘንድ ያለው የስምዖን ልጅ አስቆሮታዊው
ይሁዳ ግን እንዲህ አለ። ፭“ለነዳያን ይሰጥ
ዘንድ ይህን ሽቱ ለሦስት መቶ ዲናር ለምን
አልሸጡትም?” ፮ይህንም ያለ፥ ድሆች አሳዝ
ነውት አይደለም፤ ሌባ ነበርና፥ ሙዳየ ምጽዋ
ቱንም ሲጠብቅ በውስጡ ከሚገባው ይወስድ
ነበርና ስለዚህ ነው እንጂ። ፯ጌታችን ኢየሱስም
እንዲህ አለ፥ “ለምቀበርበት ቀን ትጠብቀው
ዘንድ ተዉአት። ፰ድሆች ግን ዘወትር አብረዋ
ችሁ አሉ፤ ዘወትርም ታገኙአቸዋላችሁ፤ በወ
ደዳችሁም ጊዜ መልካም ታደርጉላቸዋላችሁ፤ ፩
እኔን ግን ዘወትር የምታገኙኝ አይደለም።”
፱ከአይሁድም ብዙ ሰዎች ጌታችን ኢየሱስ
በዚያ እንዳለ በሀወቁ ጊዜ ወደ እርሱ መጡ፤
የመጡትም ጌታችን ኢየሱስን ለማየት ብቻ
አልነበረም፤ ጌታችን ኢየሱስ ከሙታን ለይቶ
ያስነሣዉን አልዓዛርንም ያዩ ዘንድ ነበር እንጂ።
፲የካህናት አለቆችም አልዓዛርን ሊገድሉት ተማ
ከሩ። ፲፩ከአይሁድ ብዙዎች ስለ እርሱ እየሄዱ
በጌታችን በኢየሱስ ያምኑ ነበርና።

### ወደ ኢየሩሳሌም ስለ መግባቱ

(ማቴ. ፳፩፥፩-፲፩፤ ማር. ፲፩፥፩-፲፩)

፲፪በማግሥቱም ለበዓል መጥተው የነበሩ ብዙ
ሰዎች ጌታችን ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም እን
ደሚመጣ በሰሙ ጊዜ፥ ፲፫የዘንባባ ዛፍ ዝን
ጣፊ ይዘው “ሆሣዕና በእግዚአብሔር ስም
የሚመጣ፥ የእስራኤልም ንጉሥ ቡሩክ ነው”
እያሉ ወጥተው ተቀበሉት። ፲፬ጌታችን ኢየሱ
ስም የአህያ ውርንጫ አግኝቶ በእርስዋ ላይ
ተቀመጠ። ፲፭“የጽዮን ልጅ ሆይ፥ አትፍሪ፤
እነሆ፥ ንጉሥሽ በአህያ ውርንጫ ተቀምጦ
ይመጣል” ተብሎ እንደ ተጻፈ፤ ፲፮ደቀ መዛ
ሙርቱም አስቀድመው ይህን ነገር አላወቁም፤
ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ከከበረ በኋላ በዚያ
ጊዜ ይህ ነገር ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ፥ ይህ
ንም እንደ አደረጉለት ትዝ አላቸው። ፲፯ከዚ
ያም አብረውት የነበሩት ሕዝብ አልዓዛርን ከመ

---

፩ “ዘወትርም ታገኙአቸዋላችሁ በወደዳችሁም ጊዜ መልካም ታደርጉላቸዋላችሁ” የሚለው በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ የለም።

፲፪፥፫ ሉቃ. ፯፥፴፯-፴፰። ፲፪፥፰ ዘዳ. ፲፭፥፲፩። ፲፪፥፲፫ መዝ. ፻፲፰፥፳፭-፳፮። ፲፪፥፲፭ ዘካ. ፱፥፱።

ቃብር እንደ ጠራው፥ ከሙታንም እንደ አስ
ነሣው መሰከሩለት። ፲፰ስለዚህም ነገር ሕዝቡ
ሁሉ ሊቀበሉት ወጡ፤ ይህን ተአምራት እንደ
አደረገ ሰምተዋልና። ፲፱ፈሪሳውያንም እርስ በር
ሳቸው፥ “የምታገኙት ምንም ጥቅም እንደ
ሌለ ታያላችሁን? እነሆ፥ ዓለም ሁሉ ተከትሎ
ታል” ተባባሉ።

## ለበዓል ስለ መጡ ሰዎች

፳ከጽርዕ ሰዎችም ይሰግዱ ዘንድ ለበዓል
የወጡ ነበሩ። ፳፩እነርሱም ከገሊላ፥ የቤተ
ሳይዳ ሰው ወደ ሆነው ወደ ፊልጶስ ሄደው፥
“አቤቱ፥ ጌታ ኢየሱስን ልናየው እንወድዳለን”
ብለው ለመኑት። ፳፪ፊልጶስም ሄዶ ለእንድርያስ
ነገረው፤ እንድርያስና ፊልጶስም ሄደው ለጌታ
ችን ለኢየሱስ ነገሩት። ፳፫ጌታችን ኢየሱስም
መልሶ እንዲህ አላቸው፤ “አሁን የሰው ልጅ
ይከብር ዘንድ ጊዜው ደረሰ። ፳፬እውነት እው
ነት እላችኋለሁ፤ የስንዴ ቅንጣት በምድር ላይ
ካልወደቀችና ካልሞተች ብቻዋን ትኖራለች፤
ከሞተች ግን ብዙ ፍሬን ታፈራለች። ፳፭ነፍ
ሱን የሚወዳት ይጥላታል፤ በዚህ ዓለም ነፍሱን
የሚጥላትም ለዘለዓለም ሕይወት ይጠብቃታል።
፳፮እኔን የሚያገለግለኝ ካለ ይከተለኝ፤ የሚያገ
ለግለኝ እኔ ባለሁበት በዚያ ይኖራልና፤ እኔን
የሚያገለግለኝንም አብ ያከብረዋል።

፳፯“አሁንስ ነፍሴ ታወከች፤ ግን ምን እላ
ለሁ? አባት ሆይ፥ ከዚች ሰዓት ነፍሴን አድ
ናት፤ ነገር ግን ስለዚህ ነገር ለዚች ሰዓት ደር
ሻለሁ። ፳፰አባት ሆይ፥ ልጅህን[፪] አክብረው።”
ከሰማይም፥ “አከበርሁህ፤ ደግሞም እንደገና
አከብርሃለሁ፤” የሚል ቃል መጣ። ፳፱በዚያ
ቆመው ይሰሙ የነበሩ ሕዝብ ግን “ነጐድ
ጓድ ነው” አሉ፤ “መልአክ ተናገረው”
ያሉም አሉ። ፴ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እን
ዲህ አላቸው፥ “ይህ ቃል የመጣ ስለ እናንተ
ነው እንጂ ስለ እኔ አይደለም። ፴፩አሁን የዚህ
ዓለም ፍርድ ደረሰ፤ ከእንግዲህስ ወዲህ የዚ
ህን ዓለም ገዥ ወደ ውጭ አስወጥተው ይሰዱ
ታል። ፴፪እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ካልሁ ሁሉን
ወደ እኔ እስባለሁ።” ፴፫ይህንም ያለ በምን ዐይ
ነት ሞት ይሞት ዘንድ እንዳለው ሲያመለክታ
ቸው ነው። ፴፬ሕዝቡም፥ “እኛስ ክርስቶስ ለዘ
ለዓለም እንዲኖር በኦሪት ሰምተን ነበር፤ እንግ
ዲህ እንዴት አንተ ‘የሰው ልጅ ከፍ ከፍ ይል
ዘንድ አለው’ ትለናለህ? እንግዲህ ይህ የሰው
ልጅ ማን ነው?” ብለው መለሱለት። ፴፭ጌታ
ችን ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፥ “ ገና ለጥ
ቂት ጊዜ ብርሃን ከእናንተ ጋር ነው፤ በጨለማ
የሚመላለስ የሚሄድበትን አያውቅምና ጨለማ
እንዳያገኛችሁ ብርሃን ሳለላችሁ ተመላለሱ፤
፴፮የብርሃን ልጆች ትሆኑ ዘንድ ብርሃን ሳለ
ላችሁ በብርሃን እመኑ።” ጌታችን ኢየሱስም
ይህን ተናግሮ ሄደ፤ ተሰወራቸውም። ፴፯ይህ
ንም ያህል ተአምራት በፊታቸው ሲያደርግ አላ
መኑበትም። ፴፰“አቤቱ፥ ምስክርነታችንን ማን
ያምነናል? የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገ
ለጠ?” ያለው የነቢዩ የኢሳይያስ ቃል ይደርስ
ዘንድ። ፴፱ስለዚህም ማመን ተሳናቸው፤ ኢሳ
ይያስ ዳግመኛ እንዲህ ብሎአልና። ፵“በዐይ
ናቸው አይተው፥ በልባቸውም አስተውለው
እንዳይመለሱና እንዳልፈውሳቸው ዐይኖቻቸው
ታወሩ፤ ልባቸውም ደነደነ።” ፵፩ኢሳይያስ ጌት
ነቱን አይቶአልና፥ ይህን ተናገረ፤ ስለ እርሱም
መሰከረ። ፵፪ከሕዝቡ አለቆችም ያመኑበት ብዙ
ዎች ነበሩ፤ ነገር ግን ከምኵራብ አስወጥተው
እንዳይሰዱአቸው በፈሪሳውያን ምክንያት አል
መሰከሩለትም። ፵፫ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ
የሰውን ክብር ወደዋልና።

፵፬ጌታችን ኢየሱስም ድምፁን ከፍ አድ
ርጎ እንዲህ አለ፥ “በእኔ የሚያምን በላከ
ኝም ነው እንጂ በእኔ ብቻ የሚያምን አይደ
ለም። ፵፭እኔን ያየ የላከኝን አየ። ፵፮በእኔ የሚ
ያምን ሁሉ በጨለማ እንዳይኖር ብርሃን እኔ
ወደ ዓለም መጣሁ። ፵፯ቃሌን ሰምቶ የማይጠ
ብቀውን እኔ የምፈርድበት አይደለሁም፤ ዓለ
ምን ላድን እንጂ በዓለም ልፈርድበት አልመ
ጣሁምና። ፵፰የሚክደኝን፥ ቃሌንም የማይቀበ
ለውን ግን የሚፈርድበት አለ፤ እኔ የተናገር
ሁት ቃል እርሱ በመጨረሻዪቱ ቀን ይፈር
ድበታል። ፵፱የተናገርሁት ከእኔ የሆነ አይደለ
ምና፤ ነገር ግን የላከኝ አብ እንድናገር፥ እን
ዲህም እንድል እርሱ ትእዛዝን ሰጠኝ። ፶ትእ
ዛዙም የዘለዓለም ሕይወት እንደ ሆነ አውቃ
ለሁ፤ እኔም የምናገረውን አብ እንዳለኝ እን
ዲሁ እናገራለሁ።”

---

[፪] በግሪኩ እና በአብዛኛው የግእዝ ዘርዕ “ስምህን” ይላል።

፲፪፡፳፭ ማቴ. ፲፡፴፱፤ ፲፮፡፳፭፤ ማር. ፰፡፴፭፤ ሉቃ. ፱፡፳፬፤ ፲፯፡፴፫።

፲፪፡፴፬ መዝ. ፻፲፡፬፤ ኢሳ. ፱፡፯፤ ሕዝ. ፴፯፡፳፭፤ ዳን. ፯፡፲፬። ፲፪፡፴፰ ኢሳ. ፶፫፡፩። ፲፪፡፵ ኢሳ. ፮፡፲።

## ምዕራፍ ፲፫

### ጌታ የደቀ መዛሙርቱን እግር እንደ አጠበ

፩ከፋሲካ በዓል አስቀድሞ ጌታችን ኢየሱስ
ከዚህ ዓለም ወደ ላከው ወደ አብ ይሄድ ዘንድ
ጊዜው እንደ ደረሰ ባወቀ ጊዜ በዓለም ያሉትን
የወደዳቸውን ወገኖቹን ፈጽሞ ወደዳቸው።
፪ራት ሲበሉም አሳልፎ ይሰጠው ዘንድ በስም
ዖን ልጅ በአስቆሮቱ ሰው በይሁዳ ልብ ሰይ
ጣን አደረ። ፫ጌታችን ኢየሱስም፥ አብ ሁሉን
በእጁ እንደ ሰጠው፥ ከእግዚአብሔር እንደ
ወጣ፥ ወደ እግዚአብሔርም እንደሚሄድ ባወቀ
ጊዜ፥ ፬ራት ከሚበሉበት ተነሥቶ ልብሱን አኖ
ረና ማበሻ ጨርቅ አንሥቶ ወገቡን ታጠቀ።
፭በኵስኵስቱም ውኃ ቀድቶ የደቀ መዛሙር
ቱን እግር ያጥብ ጀመር፤ በዚያ በታጠቀው
ማበሻ ጨርቅም አበሰ። ፮ወደ ስምዖን ጴጥሮ
ስም ደረሰ፤ እርሱም፥ "አቤቱ፥ አንተ እግ
ሬን ታጥበኛለህን?" አለው። ፯ጌታችን ኢየሱ
ስም፥ "እኔ የምሠራውን አንተ ዛሬ አታው
ቅም፤ ኋላ ግን ታስተውለዋለህ" ብሎ መለ
ሰለት። ፰ጴጥሮስም፥ "መቼም ቢሆን አንተ
እግሬን አታጥበኝም" አለው፤ ጌታችን ኢየሱ
ስም፥ "እውነት እውነት እልሃለሁ፤ እኔ እግ
ርህን ካላጠብሁህ ከእኔ ጋር ዕድል ፋንታ የለ
ህም" ብሎ መለሰለት። ፱ስምዖን ጴጥሮስም፥
"አቤቱ፥ እንኪያስ የምታጥበኝ እጆቼንና ራሴ
ንም እንጂ እግሮቼን ብቻ አይደለም፤" አለው።
፲ጌታችን ኢየሱስም፥ "ፈጽሞ የታጠበ ከእግሩ
በቀር ሊታጠብ አያስፈልገውም፤ ሁለንተናው
ንጹሕ ነውና፤ እናንተማ ንጹሓን ናችሁ፤ ነገር
ግን ሁላችሁ አይደላችሁም" አለው። ፲፩ጌታ
ችን ኢየሱስም አሳልፎ የሚሰጠውን ያውቅ
ነበርና ስለዚህ "ሁላችሁ ንጹሓን አይደላች
ሁም" አለ።

### ለደቀ መዛሙርቱ የተናገረው ቃል

፲፪እግራቸውንም ካጠባቸው በኋላ ልብሱን
አንሥቶ ለበሰና እንደ ገና ከእነርሱ ጋር ተቀ
መጠ፤ እንዲህም አላቸው፥ "ያደረግሁላችሁን
ዐወቃችሁን? ፲፫እናንተ 'መምህራችን፥ ጌታች
ንም' ትሉኛላችሁ፤ መልካም ትላላችሁ፤ እኔ
እንዲሁ ነኝና። ፲፬እንግዲህ እኔ መምህራችሁና
ጌታችሁ ስሆን እግራችሁን ካጠብኋችሁ እና
ንተም እንዲሁ የባልጀሮቻችሁን እግር ልታ
ጥቡ ይገባችኋል።፩ ፲፭እኔ እንደ አደረግሁላ
ችሁ እናንተም ልታደርጉ ምሳሌ ሰጥቻችኋ
ለሁና። ፲፮እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ ከጌ
ታው የሚበልጥ አገልጋይ የለም፤ ከላከው የሚ
በልጥ መልእክተኛም የለም። ፲፯ይህንም ዐው
ቃችሁ ብትሠሩ ብፁዓን ናችሁ። ፲፰ነገር ግን
ይህን የምናገር ስለ ሁላችሁ አይደለም፤ የመ
ረጥኋቸው እነማን እንደ ሆኑ እኔ አውቃለሁ፤
ነገር ግን መጽሐፍ 'እንጀራዬን የሚመገብ ተረ
ከዙን በእኔ ላይ አነሣ' ያለው ይፈጸም ዘንድ
ነው። ፲፱በሆነም ጊዜ እኔ እንደ ሆንሁ ታምኑ
ዘንድ ከዛሬ ጀምሮ ከመሆኑ አስቀድሞ እነግራ
ችኋለሁ። ፳እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ እኔ
የምልከውን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔንም
የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል።"

### አሳልፎ የሚሰጠውን ስለ ማመልከቱ

(ማቴ. ፳፮፥፳-፳፭፤ ማር. ፲፬፥፲፯-፳፩)

፳፩ይህንም ተናግሮ ጌታችን ኢየሱስ በልቡ
አዘነ፤ መሰከረ፤ እንዲህም አለ፥ "እውነት እው
ነት እላችኋለሁ፤ ከእናንተ አንዱ አሳልፎ ይሰ
ጠኛል።" ፳፪ደቀ መዛሙርቱም ይህን ስለ ማን
እንደ ተናገረ ተጠራጥረው እርስ በርሳቸው
ተያዩ፤ ፳፫ጌታችን ኢየሱስም ይወደው የነበረ
ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ በጌታችን ኢየሱስ አጠ
ገብ ተቀምጦ ነበር። ፳፬ስምዖን ጴጥሮስም እርሱን
ጠቀሰና፥ "ይህን ስለ ማን እንደ ተናገረ ጠይቀህ
ንገረን" አለው። ፳፭ያም ደቀ መዝሙር በጌታ
ችን ኢየሱስ አጠገብ ቀረብ ብሎ፥ "ጌታ ሆይ፥
እርሱ ማነው?" አለው። ፳፮ጌታችን ኢየሱስም
መልሶ፥ "ይህ እኔ እንጀራ በወጥ አጥቅሼ የምሰ
ጠው ነው" አለው፤ ያን ጊዜም እንጀራ በወጥ
አጥቅሶ ለስምዖን ልጅ ለአስቆሮታዊው ይሁዳ
ሰጠው። ፳፯እንጀራውንም ከተቀበለ በኋላ ወዲያ
ውኑ በይሁዳ ልብ ሰይጣን አደረበት፤ ጌታችን
ኢየሱስም፥ "እንግዲህ የምታደርገውን ፈጥነህ
አድርግ" አለው። ፳፰አብረውትም በማዕድ የተ
ቀመጡት ስለ ምን ይህን እንዳለው አላወቁም።

---

፩ በግሪኩ "እርስ በርሳችሁ ልትተጣጠቡ ይገባችኋል" ይላል።

፲፫፥፪ ሉቃ. ፳፪፥፫። ፲፫፥፲፫ ማቴ. ፳፫፥፰። ፲፫፥፲፭ ሉቃ. ፳፪፥፳፯።
፲፫፥፲፮ ማቴ. ፲፥፳፬፤ ሉቃ. ፮፥፵፤ ዮሐ. ፲፭፥፳። ፲፫፥፲፰ መዝ. ፵፥፱።
፲፫፥፳ ማቴ. ፲፥፵፤ ማር. ፱፥፴፯፤ ሉቃ. ፱፥፵፰፤ ፲፥፲፮።

፳፱ሙዳየ ምጽዋቱ በይሁዳ ዘንድ ነበረና፥ ለበዓል
የምንሻውን ወይም ለነዳያን የምንሰጠውን ግዛ[፪]
ያለው የመሰላቸው ነበሩ። ፴ይሁዳም ያን እንጀራ
ተቀብሎ ወዲያውኑ ወጣ፥ ሌሊትም ነበር።።

## ከራት በኋላ የተነገረ

፴፩ይሁዳም ከወጣ በኋላ ያንጊዜ ጌታችን ኢየ
ሱስ እንዲህ አላቸው፥ "አሁን የሰው ልጅ
ከበረ፤ እግዚአብሔርም በእርሱ ከበረ። ፴፪እግ
ዚአብሔር በእርሱ ከከበረ እግዚአብሔርም
እርሱን ያከብረዋል፥ ያንጊዜም ያከብረዋል።
፴፫ልጆቼ ሆይ፥ ገና ጥቂት ጊዜ ከእናንተ ጋር
አለሁ፤ ትሹኛላችሁ፤ ለአይሁድም እኔ ወደም
ሄድበት እናንተ መምጣት አይቻላችሁም እንዳ
ልኋቸው፥ አሁንም ለእናንተ እነግራችኋለሁ።

## ስለ አዲስ ትእዛዝ

፴፬"እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፥ አዲስ ትእ
ዛዝ እሰጣችኋለሁ፤ እኔ እንደ ወደድኋችሁ እናን
ተም እንዲሁ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ። ፴፭እርስ
በርሳችሁም ብትዋደዱ፥ የእኔ ደቀ መዛሙርት
እንደ ሆናችሁ በዚህ ሁሉ ያውቋችኋል።"

## ጌታ ጴጥሮስ እንደሚክድ ስለ መናገሩ

(ማቴ. ፳፮፥፴፩-፴፭፤ ሉቃ. ፳፪፥፴፩-፴፬)

፴፮ስምዖን ጴጥሮስም፥ "ጌታ ሆይ፥ ወዴት
ትሄዳለህ?" አለው፤ ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፥
"ወደምሄድበት አሁን ልትከተለኝ አትችልም፤
ኋላ ግን ትከተለኛለህ" አለው። ፴፯ጴጥሮስም፥
"ጌታ ሆይ፥ ስለ ምን አሁን ልከተልህ አልች
ልም? እኔ ነፍሴንም እንኳ ቢሆን ስለ አንተ አሳ
ልፌ እሰጣለሁ" አለው። ፴፰ጌታችን ኢየሱስም
መልሶ እንዲህ አለው፤ "ነፍስህን ስለ እኔ አሳ
ልፈህ ትሰጣለህን? እውነት እውነት እልሃለሁ፤
ሦስት ጊዜ እስክትክደኝ ዶሮ አይጮህም።

## ምዕራፍ ፲፬

## ስለ እምነት

፩"ልባችሁ አይደንግጥ፤ በእግዚአብሔር
እመኑ፤ በእኔም እመኑ። ፪በአባቴ ቤት ብዙ
ማደሪያና ማረፊያ[፩] አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ኖሮ
ቦታ ላዘጋጅላችሁ እሄዳለሁ እላችሁ ነበር። ፫ከሄ
ድሁና ቦታ ካዘጋጀሁላችሁም ዳግመኛ እመጣ
ለሁ፤ እናንተም እኔ በአለሁበት ትኖሩ ዘንድ
ወደ እኔ እወስዳችኋለሁ። ፬ወዴትም እንደም
ሄድ ራሳችሁ ታውቃላችሁ፤ መንገዱንም ታው
ቃላችሁ።" ፭ቶማስም፥ "ጌታዬ ሆይ፥ የምትሄ
ድበትን የማናውቅ እንግዲህ መንገዱን እንዴት
እናውቃለን?" አለው። ፮ጌታችን ኢየሱስም እን
ዲህ አለው፥ "የእውነትና የሕይወት መንገድ[፪]
እኔ ነኝ፤ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ
የሚመጣ የለም። ፯እኔንስ ብታውቁኝ አባቴንም
ባወቃችሁት ነበር፤ ከእንግዲህ ወዲህ ግን አው
ቃችሁታል፤ አይታችሁትማል።"
፰ፊልጶስም፥ "ጌታ ሆይ፥ አብን አሳየንና
ይበቃናል" አለው። ፱ጌታችን ኢየሱስም እን
ዲህ አለው፥ "ፊልጶስ፥ ይህን ያህል ዘመን
አብሬአችሁ ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ
አብን አየ፤ እንግዲህ እንዴት አብን አሳየን ትላ
ለህ? ፲እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ
አታምንምን? እኔ የምነግራችሁ ይህ ቃልም
ከራሴ የተናገርሁት አይደለም፤ በእኔ ያለ አብ
እርሱ ይህን ሥራ ይሠራዋል እንጂ። ፲፩እኔ
በአብ እንዳለሁ፥ አብም በእኔ እንዳለ እመኑ፤
ያለዚያም ስለ ሥራዬ እመኑኝ።
፲፪"እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ በእኔ የሚ
ያምን እኔ የምሠራውን ሥራ እርሱም ይሠ
ራል፤ ከዚያም የሚበልጥ ይሠራል፤ እኔ ወደ
አብ እሄዳለሁና። ፲፫አብ በወልድ ይከብር ዘንድ
በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርግላችኋለሁ።
፲፬በስሜ የምትለምኑት ነገር ቢኖር ያን አደር
ግላችኋለሁ።

## ስለ ጰራቅሊጦስ

፲፭"ከወደዳችሁኝስ ትእዛዜን ጠብቁ። ፲፮እኔም
አብን እለምነዋለሁ፤ እርሱም ለዘለዓለም ከእ
ናንተ ጋር ይኖር ዘንድ ሌላ አጽናኝ ይልክላች
ኋል። ፲፯እርሱም ዓለም ስለማያየውና ስለማያው
ቀው ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ
ነው፤ እናንተ ግን ታውቁታላችሁ፤ በእናንተ
ዘንድ ይኖራልና፤ ያድርባችሁማልና።

---

[፪] በግሪኩ "... ለበዓል የምንሻውን ግዛ ወይም ለነዳያን ስጥ ያለው የመሰላቸው ነበሩ" ይላል።

[፩] "ማረፊያ" የሚለው በግሪኩ የለም።

[፪] በግሪኩ "እኔ መንገድ፥ እውነትና ሕይወትም ነኝ" ይላል።

፲፫፥፴፫ ዮሐ. ፯፥፴፬። ፲፫፥፴፬ ዮሐ. ፲፭፥፲፪፤ ፲፯፤ ፩ዮሐ. ፫፥፳፫፤ ፪ዮሐ. ፭። ፲፬፥፫ ዮሐ. ፲፯፥፳፬።
፲፬፥፲ ዮሐ. ፫፥፲፩።

፲፰“የሙት ልጆች ትሆኑ ዘንድ አልተዋች
ሁም፤ ወደ እናንተ እመጣለሁ። ፲፱ገና ጥቂት
ጊዜ አለ፤ እንግዲህ ወዲህም ዓለም አያየኝም፤
እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፤ እኔ ሕያው ነኝና፤
እናንተም ሕያዋን ትሆናላችሁ። ፳እኔ በአብ
እንዳለሁ፥ አብም በእኔ እንዳለ፥[፫] እናንተም
በእኔ፥ እኔም በእናንተ እንዳለሁ ያንጊዜ ታው
ቃላችሁ። ፳፩ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለ የሚ
ጠብቀውም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ የሚወደ
ኝንም አባቴ ይወደዋል፤ እኔም እወደዋለሁ፤
ራሴንም እገልጥለታለሁ።” ፳፪የአስቆሮቱ ሰው
ያይደለ ይሁዳም፥ “ጌታ ሆይ፥ ለዓለም ያይ
ደለ ለእኛ ራስህን ትገልጥ ዘንድ እንዳለህ የተ
ናገርኸው ምንድን ነው?” አለው። ፳፫ጌታችን
ኢየሱስም መልሶ አለው፥ “የሚወደኝ ቃሌን
ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል፤ ወደ እርሱም
መጥተን በእርሱ ዘንድ ማደሪያ እናደርጋለን።
፳፬የማይወደኝ ግን ቃሌን አይጠብቅም፤ ይህም
የምትሰሙት ቃል የላከኝ የአብ ቃል ነው እንጂ
የእኔ ቃል አይደለም።

፳፭“ከእናንተም ጋር ሳለሁ ይህን ነገርኋችሁ።
፳፮ነገር ግን አብ በስሜ የሚልከው[፬] የእውነት
መንፈስ ጰራቅሊጦስ እርሱ ሁሉን ያስተምራ
ችኋል፤ እኔ የነገርኋችሁንም ሁሉ ያሳስባች
ኋል።

## ስለ ሰላም

፳፯“ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜንም
እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደ
ሚሰጠው አይደለም፤ ልባችሁ አይደንግጥ፤
አትፍሩም። ፳፰እኔ እንደምሄድ ወደ እናን
ተም እንደምመለስ የነገርኋችሁን ሰምታች
ኋል፤ ብትወዱኝስ ወደ አብ በመሄዴ ደስ
ባላችሁ ነበር፤ እርሱ አብ ይበልጠኛልና።
፳፱አሁንም ይህ በሆነ ጊዜ ታምኑ ዘንድ አስ
ቀድሜ ሳይሆን ነገርኋችሁ። ፴እንግዲህ ወዲህ
ከእናንተ ጋር ብዙ አልናገርም፤ የዚህ ዓለም
ገዢ ይመጣልና፤ በእኔም ላይ ምንም አያ
ገኝም። ፴፩ነገር ግን አብን እንደምወደው
ዓለም ያውቅ ዘንድ አብ ትእዛዙን እንደ
ሰጠኝ እንዲሁ አደርጋለሁ፤ ተነሡ ከዚህ፤
እንሂድ።

## ምዕራፍ ፲፭

### ጌታችን ኢየሱስ እውነተኛ የወይን ሐረግ ስለ መሆኑ

፩“እውነተኛ የወይን ሐረግ እኔ ነኝ፤ ተካ
ዩም አባቴ ነው። ፪በእኔ ያለውን፥ ፍሬ የማያፈ
ራውን ቅርንጫፍም ሁሉ ያስወግደዋል፤ የሚ
ያፈራውን ቅርንጫፍ ሁሉ ግን በብዙ እንዲያ
ፈራ ያጠራዋል። ፫እናንተ ግን ስለ ነገርኋችሁ
ቃል ፈጽማችሁ ንጹሓን ናችሁ። ፬በእኔ ኑሩ፤
እኔም በእናንተ፤ ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ከአ
ልኖረ ብቻውን ሊያፈራ እንደማይችል እናን
ተም እንዲሁ በእኔ ካልኖራችሁ ፍሬ ማፍራት
አትችሉም። ፭እኔ የወይን ግንድ ነኝ፤ ቅርንጫ
ፎቹም እናንተ ናችሁ፤ በእኔ የሚኖር እኔም
በእርሱ፥ ብዙ ፍሬ የሚያፈራ እርሱ ነው፤ ያለ
እኔ ምንም ማድረግ አትችሉምና። ፮በእኔ የማ
ይኖር ቢኖር እንደ ደረቅ ቅርንጫፍ ወደ ውጭ
ይጥሉታል፤ ሰብስበውም በእሳት ያቃጥሉታል።
፯በእኔም ብትኖሩ ቃሌም በእናንተ ቢኖር የምት
ሹትን ሁሉ ትለምናላችሁ፤ ይደረግላችሁማል።
፰ብዙ ፍሬ ብታፈሩ፥ ደቀ መዛሙርቴም ብት
ሆኑ በዚህ አባቴ ይከበራል። ፱አብ እንደ ወደ
ደኝ እንዲሁ ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬም ኑሩ።
፲የምትወዱኝ ብትሆኑ ትእዛዜን ጠብቁ፤ እኔ
የአባቴን ትእዛዝ እንደ ጠበቅሁ፥ በፍቅሩም
እንደምኖር እናንተም ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍ
ቅሬ ትኖራላችሁ። ፲፩ደስታዬ በእናንተ ይኖር
ዘንድ፥ ደስታችሁም ፍጹም ይሆን ዘንድ ይህን
ነገርኋችሁ።

፲፪“እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ
እንድትዋደዱ የእኔ ትእዛዝ ይህች ናት። ፲፫ስለ
ወዳጆቹ ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ ሰው ያለ
እንደ ሆነ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር የለም። ፲፬እና
ንተስ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ካደረጋችሁ ወዳጆቼ
ናችሁ። ፲፭እንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም፤
ባሪያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና፤ እና
ንተን ግን ወዳጆቼ እላችኋለሁ፤ በአባቴ ዘንድ
የሰማሁትን ሁሉ ነግሬአችኋለሁና። ፲፮እኔ መረ
ጥኋችሁ እንጂ እናንተ የመረጣችሁኝ አይደ
ለም፤ እንድትሄዱ፥ ፍሬም እንድታፈሩ፥ ፍሬ

---

፫ “አብ በእኔ እንደ አለ” የሚለው በግሪኩ የለም።

፬ በግሪኩ እና በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ “መንፈስ ቅዱስ” ይላል።

፲፬፥፲፰ ማቴ. ፳፰፥፳። ፲፬፥፳፪ ሉቃ. ፯፥፲፯። ፲፭፥፮ ማቴ. ፲፫፥፵-፵፪፤ ፲፭፥፯፡፰፤ ዮሐ. ፲፬፥፲፫።
፲፭፥፲፪ ዮሐ. ፲፫፥፴፬፤ ፲፭፥፲፫፤ ፩ዮሐ. ፫፥፲፮፤ ፪ዮሐ. ፭።

አችሁም እንዲኖር፥ አብንም በስሜ የምትለም
ኑት ነገር ቢኖር ሁሉን እንዲሰጣችሁ ሾምኳ
ችሁ። ፲፯እርስ በርሳችሁም እንድትዋደዱ ይህን
አዝዣችኋለሁ።

### ዓለም የጌታን ተከታዮች እንደሚጠላ

፲፰“ዓለም ቢጠላችሁ አስቀድሞ እኔን እንደ
ጠላ ዕወቁ። ፲፱እናንተስ ከዓለም ብትሆኑ ዓለም
በወደዳችሁ ነበር፤ ዓለም ወገኖቹን ይወዳልና፤
ነገር ግን እኔ ከዓለም መረጥኋችሁ እንጂ እና
ንተ ከዓለም አይደላችሁምና ስለዚህ ዓለም
ይጠላችኋል። ፳እኔ፡- ከጌታው የሚበልጥ አገ
ልጋይ የለም ያልኋችሁን ቃሌን ዕስቡ፤ እኔን
ካሳደዱ እናንተንም ያሳድዱአችኋል፤ ቃሌን
ጠብቀው ቢሆንስ ቃላችሁንም በጠበቁ ነበር።
፳፩ነገር ግን ስለ ስሜ ይህን ሁሉ ያደርጉባ
ችኋል፤ የላከኝን አያውቁትምና። ፳፪ባልመጣ
ሁና ባልነገርኋቸውስ ኖሮ ኀጢአት ባልሆነባቸ
ውም ነበር፤ አሁን ግን ለኀጢአታቸው ምክን
ያት የላቸውም። ፳፫እኔን የሚጠላ አባቴን ይጠ
ላል። ፳፬ሌላ ያልሠራውን ሥራ በመካከላቸው
ባልሠራ ኖሮ ኀጢአት ባልሆነባቸውም ነበር፤
አሁን ግን እኔንም አባቴንም አይተዋል፤ ጠል
ተውማል። ፳፭ነገር ግን በኦሪታቸው፡- በከንቱ
ጠሉኝ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸም ዘንድ
ነው።

### መንፈስ ቅዱስ ከአብ ስለመሥረፁ

፳፮“እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ ጰራቅሊ
ጦስ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መን
ፈስ በመጣ ጊዜ፥ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል።
፳፯እናንተም ትመሰክራላችሁ፤ ከጥንት ጀምሮ
ከእኔ ጋር ኑራችኋልና።

## ምዕራፍ ፲፮

### በሃይማኖት ስለ መጽናት

፩“እንዳትሰናከሉ ይህን ነገርኋችሁ። ፪ከም
ኵራባቸው ያስወጡአችኋል፤ ደግሞም እናን
ተን የሚገድላችሁ ሁሉ ለእግዚአብሔር አገል
ግሎት የሚያቀርብ የሚመስልበት ጊዜ ይመ
ጣል። ፫ይህንም የሚያደርጉባችሁ አብንም፥
እኔንም ስላላወቁ ነው። ፬ነገር ግን ጊዜው ሲደ
ርስ እኔ እንደ ነገርኋችሁ ታስቡ ዘንድ ይህን
ነገርኋችሁ። አስቀድሜ ግን ይህን አልነገርኳ
ችሁም ነበር፤ ከእናንተ ጋር ነበርሁና። ፭አሁን
ግን ወደ ላከኝ ወደ አብ እሄዳለሁ፤ ከእናንተ
አንዱ እንኳ፡- ‘ወዴት ትሄዳለህ?’ ብሎ አይጠ
ይቀኝም። ፮ነገር ግን ይህን ስለ ነገርኋችሁ በል
ባችሁ ኀዘን ሞላ።

### መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸው ተስፋ ስለመስጠቱ

፯“እኔ በእውነት የሚሆነውን እነግራችኋለሁ፤
እኔ ብሄድ ይሻላችኋል፤ እኔ ካልሄድሁ ጰራቅሊ
ጦስ ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እኔ ከሄድሁ ግን
እርሱን እልክላችኋለሁ። ፰እርሱም በመጣ ጊዜ
ዓለምን ስለ ኀጢአትና ስለ ጽድቅ፥ ስለ ፍርድም
ይዘልፈዋል። ፱ስለ ኀጢአት፥ በእኔ አላመኑምና
ነው፤ ፲ስለ ጽድቅ፥ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፥
እንግዲህ ወዲህም አታዩኝምና ነው። ፲፩ስለ ፍር
ድም፥ የዚህ ዓለም ገገር ይፈረድበታልና ነው።
፲፪“የምነግራችሁ ብዙ ነገር ነበረኝ፤ ነገር
ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም። ፲፫ያ የእ
ውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ግን ወደ እውነት
ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚሰማውን ሁሉ ይናገ
ራል እንጂ እርሱ ከራሱ አይናገርምና፤ የሚመ
ጣውንም ይነግራችኋል። ፲፬እርሱም እኔን ያከ
ብረኛል፤ ከእኔ ወስዶ ይነግራችኋልና። ፲፭ለአብ
ያለው ሁሉ የእኔ ነው፤ ስለዚህም ከእኔ ወስዶ
ይነግራችኋል አልኋችሁ።
፲፮“ጥቂት ጊዜ አለ፤ አታዩኝምም፤ ደግሞም
ጥቂት ጊዜ አለ፤ እንደገናም ታዩኛላችሁ፤ ወደ
አብ እሄዳለሁና።” ፲፯ደቀ መዛሙርቱም እርስ
በርሳቸው፥ “ጥቂት ጊዜ አለ፤ አታዩኝምም፤
ደግሞም ጥቂት ጊዜ አለ፤ እንደገናም ታዩኛላ
ችሁ፥ ወደ አብ እሄዳለሁና የሚለን ይህ ነገር
ምንድነው?” ተባባሉ። ፲፰“ይህ ጥቂት የሚለን
ምንድነው? የሚናገረውን አናውቅም” አሉ።
፲፱ጌታችን ኢየሱስም ሊጠይቁት እንደሚሹ
ዐውቆ እንዲህ አላቸው፥ “ጥቂት ጊዜ አለ፤
አታዩኝምም፤ ደግሞም ጥቂት ጊዜ አለ፤ እን
ደገናም ታዩኛላችሁ” ስለ አልኋችሁ፥ ስለዚህ
ነገር እርስ በርሳችሁ ትመራመራላችሁን?

### ስለ ኀዘንና ስለ ደስታ

፳“እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ እናንተ ታለ
ቅሳላችሁ፤ ታዝኑማላችሁ፤ ዓለምም ደስ ይለ

---

፲፭፥፳ ማቴ ፲፥፳፬፤ ሉቃ. ፮፥፵፤ ዮሐ. ፲፫፥፲፮።
፲፮፥፪ ዮሐ. ፱፥፳፪፤ ማቴ. ፳፬፥፱፤ ፲፮፥፬ ሉቃ. ፳፪፥፶፫፤ ፲፮፥፳፤ ማር. ፲፮፥፲፤ ሉቃ. ፳፬፥፲፯፤ ፲፮፥፳፩፤ ዘፍ. ፫፥፲፮።

ዋል፤ እናንተ ግን ታዝናላችሁ፤ ነገር ግን ኀዘና
ችሁ ወደ ደስታ ይለወጣል። ፳፩ሴት በምትወል
ድበት ጊዜ ወራቷ ስለ ደረሰ ታዝናለች፤ ነገር
ግን ልጅዋን ከወለደች በኋላ ስለ ደስታዋ ከዚያ
ወዲያ ምጥዋን አታስበውም፤ በዓለም ወንድ
ልጅን ወልዳለችና። ፳፪እናንተም ዛሬ ታዝናላ
ችሁ፤ እንደገናም አያችኋለሁ፤ ልባችሁም ደስ
ይለዋል፤ ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም።
፳፫ያንጊዜም እኔን የምትለምኑኝ አንዳች የለም፤
እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ በስሜ አብን ብት
ለምኑት ሁሉን ይሰጣችኋል። ፳፬እስካሁን ምንም
በስሜ አልለመናችሁም፤ ደስታችሁ ፍጹም
ይሆን ዘንድ ለምኑ፤ ታገኙማላችሁ።

### ዓለምን ድል ስለ መንሣት

፳፭"ዛሬስ በምሳሌ ነገርኋችሁ፤ ነገር ግን የአ
ብን ነገር ገልጬ እነግራችኋለሁ እንጂ ለእና
ንተ በምሳሌ የማልናገርበት ጊዜ ይመጣል።
፳፮ያንጊዜ በስሜ ትለምናላችሁ፤ እኔም ስለ እና
ንተ አብን እለምነዋለሁ አልላችሁም፤ ፳፯እና
ንተ ስለ ወደዳችሁኝ፤ ከእግዚአብሔርም እንደ
ወጣሁ ስለ አመናችሁብኝ እርሱ ራሱ አብ
ወድዷችኋልና። ፳፰ከአብ ወጣሁ፤ ወደ ዓለምም
መጣሁ፤ ዳግመኛም ዓለምን እተወዋለሁ፤ ወደ
አብም እሄዳለሁ።"

፳፱ደቀ መዛሙርቱም እንዲህ አሉት፥
"እነሆ፥ ዛሬ ገልጠህ ትናገራለህ፤ ምንም በም
ሳሌ የተናገርኸው የለም። ፴አሁን አንተ ሁሉን
እንደምታውቅ፥ ማንም ሊነግርህ እንደማትሻ
ዐወቅን፤ በዚህም ከእግዚአብሔር እንደ ወጣህ
እናምናለን።" ፴፩ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እን
ዲህ አላቸው፥ "አሁን ታምናላችሁን? ፴፪እያን
ዳንዳችሁ በየቦታዉ የምትበታተኑበት፥ እኔንም
ብቻዬን የምትተዉበት ጊዜ ይደርሳል፤ ደርሶ
አልም፤ እኔ ግን ብቻዬን አይደለሁም፤ አብ
ከእኔ ጋር ነውና። ፴፫በእኔም ሰላምን እንድታ
ገኙ ይህን ነገርኋችሁ፤ በዓለም ግን መከራን
ትቀበላላችሁ፤ ነገር ግን ጽኑ፤ እኔ ዓለሙን
ድል ነሥቼዋለሁና።"

## ምዕራፍ ፲፯

### ጌታችን ወደ አብ እንደ ጸለየ

፩ጌታችን ኢየሱስም ይህን ነገር ተናግሮ ዐይ
ኖቹን ወደ ሰማይ አነሣና እንዲህ አለ፥ "አባት
ሆይ፥ ሰዓቱ ደርሶአልና ልጅህ ያከብርህ ዘንድ
ልጅህን አክብረው፤ ፪ሥጋ በለበሰው ሁሉ ላይ
ሥልጣንን እንደ ሰጠኸው መጠን ለሰጠኸው
ሁሉ የዘለዓለም ሕይወትን ይሰጣቸው ዘንድ።
፫ብቻህን እውነተኛ አምላክ የሆንህ አንተን፥
የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ
ይህች የዘለዓለም ሕይወት ናት። ፬እኔ ልሠራው
የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር ላይ አከበር
ሁህ። ፭አሁንም አባት ሆይ፥ ዓለም ሳይፈጠር
ከአንተ ጋር በነበረኝ ክብር በአንተ ዘንድ አክ
ብረኝ።

፮"ከዓለም ለይተህ ለሰጠኸኝ ሰዎች ስም
ህን ገለጥሁ፤ ያንተ ነበሩ፤ እነርሱንም ለእኔ
ሰጥተኸኛል፤ ቃልህንም ጠበቁ። ፯የሰጠኸኝም
ሁሉ ከአንተ እንደ ሆነ ዛሬ ዐወቁ። ፰የሰጠኸ
ኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና፤ እነርሱም ተቀብ
ለው ከአንተ እንደ ወጣሁ በእውነት ዐወቁ፤
አንተም እንደ ላክኸኝ አመኑ። ፱እኔ ስለ እነ
ርሱ እለምናለሁ፤ የምለምንህ ስለ ዓለም አይ
ደለም፤ ስለ ሰጠኸኝ ነው እንጂ፤ ያንተ ናቸ
ውና። ፲የእኔም የሆነ ሁሉ የአንተ ነው፤ የአን
ተም የሆነ የእኔ ነው፤ እኔም በእነርሱ ከብሬአ
ለሁ። ፲፩እንግዲህ በዓለም አልኖርም፤ እነርሱ
ግን በዓለም ይኖራሉ፤ እኔም ወደ አንተ እመ
ጣለሁ፤ ቅዱስ አባት ሆይ፥ እነዚህን የሰጠኸኝን
እንደ እኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ በስምህ ጠብቃ
ቸው፤ ፲፪እኔ በዓለም ከእነርሱ ጋር ሳለሁ ግን
የሰጠኸኝን በስምህ እጠብቃቸው ነበር፤ ጠበቅ
ኋቸውም፤ የመጽሐፉም ቃል ይፈጸም ዘንድ
ከጥፋት ልጅ በቀር ከእነርሱ አንድ ስንኳን አል
ጠፋም። ፲፫አሁን ግን ወደ አንተ እመጣለሁ፤
በእነርሱም ደስታዬ ፍጹም ይሆን ዘንድ ይህን
በዓለም እናገራለሁ። ፲፬እኔ ቃልህን ሰጠኋቸው፤
ዓለም ግን ጠላቸው፤ እኔ ከዓለም እንዳይደለሁ
እነርሱ ከዓለም አይደሉምና። ፲፭ከክፉ ነገር እን
ድትጠብቃቸው ነው እንጂ ከዓለም እንድትለ
ያቸው አልለምንም። ፲፮እኔ ከዓለም እንዳይደ
ለሁ ከዓለም አይደሉምና። ፲፯በእውነትህ ቀድ
ሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነውና። ፲፰አንተ እኔን
ወደ ዓለም እንደ ላክኸኝ እኔም እነርሱን ወደ
ዓለም ላክኋቸው። ፲፱እነርሱም በእውነት ቅዱ
ሳን ይሆኑ ዘንድ ስለ እነርሱ እኔ ራሴን እቀ
ድሳለሁ።

፳"የምለምንህም ስለ እነዚህ ብቻ አይደለም፤
በቃላቸው ስለሚያምኑብኝም ነው እንጂ፤

---

፲፯፥፪ ማቴ ፳፰፥፲፰። ፲፯፥፲፪ መዝ. ፵፩፥፱፤ ዮሐ. ፲፫፥፲፰። ፲፯፥፲፭፤ ማቴ. ፮፥፲፫፤ ፲፯፥፲፯፤ መዝ. ፻፲፱፥፻፵፪።

፳፩ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ፥ አንተ አብ በእኔ
እንዳለህ፥ እኔም በአንተ እንዳለሁ፥ እነርሱም
እንደ እኛ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ፥ አንተም
እንደ ላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ። ፳፪እኔም የሰ
ጠኸኝን ክብር ሰጠኋቸው፤ እኛ አንድ እንደ
ሆን እነርሱም እንደ እኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ።
፳፫እኔ በእነርሱ እኖራለሁ፤ አንተም በእኔ፤ በአ
ንድ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ፤ አንተም እንደ ላክ
ኸኝና እንደ ወደድኸኝ፩ እኔም እነርሱን እንደ
ወደድኋቸው። ፳፬አባት ሆይ፥ የሰጠኸኝ እነዚህ
እኔ ባለሁበት አብረውኝ ይኖሩ ዘንድና የሰጠ
ኸኝን ክብሬን ያዩ ዘንድ እወድዳለሁ፤ ዓለም
ሳይፈጠር ወድደኸኛልና። ፳፭ጻድቅ አባት ሆይ፥
ዓለም አላወቀህም፤ እኔ ግን ዐወቅሁህ፤ እነዚ
ህም አንተ እንደ ላክኸኝ ዐወቁ። ፳፮እኔን የወ
ደድህበት ፍቅር በእነርሱ ይኖር ዘንድ፥ እኔም
በእነርሱ እኖር ዘንድ ስምህን ነገርኋቸው፤ ደግ
ሞም እነግራቸዋለሁ፤”

## ምዕራፍ ፲፰

### ይሁዳ ጌታችንን አሳልፎ ስለ መስጠቱ

(ማቴ. ፳፮፥፵፯-፶፮፤ ሉቃ. ፳፪፥፵፯-፶፫)

፩ጌታችን ኢየሱስም ይህን ተናግሮ አትክልት
ወደ አለበት ስፍራ ወደ ቄድሮስ ወንዝ ማዶ
ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወጣ፤ ከደቀ መዛሙር
ቱም ጋር ወደዚያ ገባ። ፪አሳልፎ የሚሰጠው
ይሁዳም ያን ስፍራ ያውቀው ነበር፤ ጌታችን
ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደዚያ ብዙ
ጊዜ ይሄድ ነበርና። ፫ይሁዳም ከካህናት አለቆ
ችና ከፈሪሳውያን ወታደሮችን ተቀበለ፤ ሎሌ
ዎቻቸውንም በረዳትነት ወሰደ፤ ፋኖስና የችቦ
መብራት፥ የጦር መሣሪያም ይዞ ወደዚያ ሄደ።
፬ጌታችን ኢየሱስም የሚደርስበትን ሁሉ ዐውቆ
ወደ እነርሱ ወደ ውጭ ወጣና፥ “ማንን ትሻ
ላችሁ?” አላቸው። ፭“የናዝሬቱን ኢየሱስን”
ብለው መለሱለት፤ ጌታችን ኢየሱስም፥ “እኔ
ነኝ” አላቸው፤ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳም በዚ
ያው አብሮአቸው ቆሞ ነበር። ፮ጌታችን ኢየሱ
ስም፥ “እኔ ነኝ” ባላቸው ጊዜ፤ ወደ ኋላቸው
ተመልሰው በምድር ላይ ወደቁ። ፯ከዚህም
በኋላ እንደገና፥ “ማንን ትሻላችሁ?” ብሎ ጠየ
ቃቸው፤ እነርሱም፥ “የናዝሬቱን ኢየሱስን”
አሉት። ፰ጌታችን ኢየሱስም፥ “እኔ ነኝ አል
ኋችሁ፤ እኔን የምትሹ ከሆነ እነዚህን ተዉአ
ቸው፤ ይሂዱ” አላቸው። ፱ይህም፥ “ከእነዚህ
ከሰጠኸኝ አንድ ስንኳ አልጠፋም”፪ ያለው
ቃሉ ይፈጸም ዘንድ ነው። ፲ስምዖን ጴጥሮ
ስም ሾተል ነበረው፤ ሾተሉንም መዝዞ የሊቀ
ካህናቱን አገልጋይ መትቶ ቀኝ ጆሮውን ቈረ
ጠው፤ የዚህም አገልጋይ ስም ማልኮስ ይባል
ነበር። ፲፩ጌታችን ኢየሱስም ጴጥሮስን፥ “ሾተ
ልህን ወደ አፎቱ መልስ፤ አብ የሰጠኝን ጽዋ
ሳልጠጣ እተወዋለሁን?” አለው።

### ወደ ሊቃነ ካህናት ስለ መሄዱ

፲፪ጭፍሮችና የሺ አለቃው፥ የአይሁድም
ሎሌዎች ጌታችን ኢየሱስን ይዘው አሰሩት።
፲፫አስቀድሞም ወደ ሐና ወሰዱት፤ በዚያች
ዓመት የካህናት አለቃ ለነበረው ለቀያፋ አማቱ
ነበርና። ፲፬ቀያፋም “ስለ ሕዝቡ ሁሉ አንድ
ሰው ቢሞት ይሻላል” ብሎ አይሁድን የመከ
ራቸው ነበር።

### ስለ ጴጥሮስ ክህደት

(ማቴ. ፳፮፥፷፱፡፸፤ ማር. ፲፬፥፷፮-፷፰)

፲፭ስምዖን ጴጥሮስና ሌላው ደቀ መዝሙርም
ጌታችን ኢየሱስን ከሩቅ ተከተሉት፤ ያ ደቀ
መዝሙር ግን በሊቀ ካህናቱ ዘንድ የታወቀ
ነበር፤ ከጌታችን ኢየሱስ ጋርም ወደ ሊቀ ካህ
ናቱ ግቢ ገባ። ፲፮ጴጥሮስ ግን በስተውጭ በበሩ
ቆሞ ነበር፤ ያም በሊቀ ካህናቱ ዘንድ ይታወቅ
የነበረው ሌላው ደቀ መዝሙር ወጣና ለበረኛ
ዪቱ ነግሮ ጴጥሮስን አስገባው። ፲፯በረኛዪቱ አገ
ልጋይም፥ “አንተም ከዚያ ሰው ደቀ መዛሙ
ርት ወገን አይደለህምን?” አለችው፤ እርሱም፥
“አይደለሁም” አላት። ፲፰አገልጋዮችና ሎሌዎ
ችም በዚያ ቆመው እሳት አንድደው ይሞቁ
ነበር፤ የዚያች ሌሊት ብርድ ጽኑ ነበርና፤ ጴጥ
ሮስም ከእነርሱ ጋር ቆሞ ይሞቅ ነበረ።

### ሊቀ ካህናቱ እንደ ጠየቀው

(ማቴ. ፳፮፥፶፱-፷፮፤ ሉቃ. ፳፪፥፷፮-፸፩)

፲፱ሊቀ ካህናቱም ጌታችን ኢየሱስን፡- ስለ
ደቀ መዛሙርቱና ስለ ትምህርቱ ጠየቀው።
፳ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፥

---

፩ በግሪኩ “... እኔን በወደድኸኝ መጠን እነርሱን እንደ ወደድሃቸው ...” ይላል።

፪ በግሪኩ “... አንዱን ስንኳ አላጠፋሁም” ይላል።

፲፰፥፲፩ ማቴ ፳፮፥፶፪፤ ማር. ፲፬፥፵፮፤ ሉቃ. ፳፪፥፵፪። ፲፰፥፲፬ ዮሐ. ፲፩፥፵፱-፶።

“እኔ ለዓለም በግልጥ ተናገርሁ፤ አይሁድ
ሁሉ በሚሰበሰቡበት በምኵራብም፥ በቤተ መቅ
ደስም ሁልጊዜ አስተማርሁ፤ በስውርም የተና
ገርሁት አንዳች ነገር የለም። ፳፩እንግዲህ እኔን
ለምን ትጠይቀኛለህ? የተናገርሁትን የሰሙኝን
ጠይቃቸው፤ እኔም የተናገርሁትን እነሆ፥ እነ
ርሱ ያውቃሉ።” ፳፪ይህንም ባለጊዜ ከቆሙት
ሎሌዎች አንዱ፥ “ለሊቀ ካህናቱ እንዲህ ትመ
ልስለታለህን?” ብሎ ጌታችን ኢየሱስን በጥፊ
መታው። ፳፫ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፥ “ክፉ
ተናግሬ እንደ ሆንሁ ስለ ክፉ መስክርብኝ፤
መልካም ተናግሬ እንደ ሆንሁ ግን ለምን ትመ
ታኛለህ?” አለው። ፳፬ሐናም ጌታችን ኢየሱ
ስን እንደ ታሰረ ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ
ላከው።

፳፭ስምዖን ጴጥሮስም ቆሞ እሳት ይሞቅ
ነበር፤ “አንተስ ከእርሱ ደቀ መዛሙርት ወገን
አይደለህምን?” አሉት፤ እርሱም፥ “አይደለ
ሁም” ብሎ ካደ። ፳፮ጴጥሮስ ጆሮውን ከቈ
ረጠው ሰው ዘመዶች ወገን የሆነ ከሊቀ ካህ
ናቱ አገልጋዮችም አንድ ሰው፥ “እኔ በአትክ
ልት ቦታ ውስጥ ከእርሱ ጋር አይቼህ አልነበረ
ምን?” አለው። ፳፯ጴጥሮስም ደግሞ ካደ፤ ያን
ጊዜም ዶሮ ጮኸ።

### ጌታ በጲላጦስ ፊት ስለ መቆሙ
(ማቴ. ፳፯፥፩-፪፤ ማር. ፲፭፥፩-፭)

፳፰ጌታችን ኢየሱስንም ከቀያፋ ወደ ፍርድ
አደባባይ ወሰዱት፤ አይሁድ ግን ፈጽሞ ስለ
ነጋ የፋሲካውን በግ ሳይበሉ እንዳይረክሱ ወደ
ፍርድ አደባባይ አልገቡም። ፳፱ጲላጦስም ወደ
እነርሱ ወደ ውጭ ወጥቶ፥ “ይህን ሰው ወደ
እኔ ያመጣችሁበት በደሉ ምንድነው?” አላ
ቸው። ፴እነርሱም፥ “ክፉ የሠራ ባይሆንስ
ወደ አንተ አሳልፈን ባልሰጠነው ነበር” ብለው
መለሱለት። ፴፩ጲላጦስም፥ “እናንተ ወስዳችሁ
እንደ ሕጋችሁ ፍረዱበት” አላቸው፤ አይሁ
ድም፥ “እኛስ ማንንም ልንገድል አልተፈቀደ
ልንም” አሉት። ፴፪ይህም በምን ዐይነት ሞት
ይሞት ዘንድ እንዳለው ሲያመለክት የተናገረው
የጌታችን የኢየሱስ ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው።
፴፫ጲላጦስም እንደገና ወደ ፍርድ አደባባይ
ገብቶ ጌታችን ኢየሱስን ጠራና፥ “የአይሁድ
ንጉሥ አንተ ነህን?” አለው። ፴፬ጌታችን ኢየሱ
ስም፥ “ይህን የምትናገር ከራስህ ነውን? ወይስ
ስለ እኔ የነገረህ ሌላ አለን?” ብሎ መለሰለት።
፴፭ጲላጦስም መልሶ፥ “እኔ አይሁዳዊ ነኝን?
ለእኔ አሳልፈው የሰጡህ ወገኖችህና ሊቃነ ካህ
ናት አይደሉምን? እረ ምን አድርገሃል?”
አለው። ፴፮ጌታችን ኢየሱስም፥ “የእኔ መን
ግሥት ከዚህ ዓለም አይደለችም፤ መንግሥ
ቴስ በዚህ ዓለም ብትሆን ኖሮ ለአይሁድ እን
ዳልሰጥ አሽከሮቼ በተዋጉልኝ ነበር፤ አሁንም
መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም” ብሎ መለሰ
ለት። ፴፯ጲላጦስም፥ “እንግዲያ አንተ ንጉሥ
ነህን?” አለው፤ ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፥
“እኔ ንጉሥ እንደ ሆንሁ አንተ ራስህ ትላለህ፤
እኔ ስለዚህ ተወለድሁ፤ ስለዚህም ለእውነት
ልመሰክር ወደ ዓለም መጣሁ፤ ከእውነት የሆነ
ሁሉ ቃሌን ይሰማኛል” አለው። ፴፰ጲላጦስም፥
“እውነት ምንድነው?” አለው፤ ይህንም ተና
ግሮ ዳግመኛ ወደ አይሁድ ወጣና እንዲህ አላ
ቸው፥ “እኔ አንዲት ስንኳን በደል አላገኘሁበ
ትም። ፴፱ነገር ግን በየዓመቱ በፋሲካ በዓል ከእ
ስረኞች አንድ እንድፈታላችሁ ልማድ አላችሁ፤
እንግዲህ የአይሁድን ንጉሥ ልፈታላችሁ ትወዳ
ላችሁን?” አላቸው። ፵ዳግመኛም ድምፃቸውን
ከፍ አድርገው፥ “በርባንን እንጂ ይህን አይደ
ለም፤” አሉ፤ በርባን ግን ወንበዴ ነበር።

## ምዕራፍ ፲፱

### አይሁድ ጌታን እንደ ገረፉትና እንደ ተዘባበቱበት
(ማቴ. ፳፯፥፳፯-፴፪፤ ማር. ፲፭፥፲፭-፳፩)

፩ከዚህም በኋላ ጲላጦስ ጌታችን ኢየሱስን ይዞ
ገረፈው። ፪ጭፍሮችም የእሾህ አክሊል ጎንጕ
ነው በራሱ ላይ ደፉበት፤ የቀይ ሐር መጐና
ጸፊያም አለበሱት። ፫ወደ እርሱም እየመጡ፥
“የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፥ ሰላም ለአንተ ይሁን”
ይሉት ነበር፤ በጥፊም ይመቱት ነበር። ፬ጲላጦ
ስም እንደገና ወደ ውጭ ወጣና፥ “እነሆ፥ በእ
ርሱ ላይ አንዲት በደል ስንኳን ያገኘሁበት እንደ
ሌለ ታውቁ ዘንድ ወደ ውጭ አወጣላችኋለሁ”
አላቸው። ፭ጌታችን ኢየሱስም የእሾህ አክሊል
ደፍቶ፥ የቀይ ሐር መጐናጸፊያም ለብሶ ወደ
ውጭ ወጣ፤ ጲላጦስም፥ “እነሆ፥ ሰውዬው”
አላቸው። ፮ሊቃነ ካህናትና ሎሌዎቻቸውም ባዩት
ጊዜ፥ “ስቀለው! ስቀለው!” እያሉ ጮሁ፤ ጲላ
ጦስም፥ “እናንተ ራሳችሁ ውሰዱና ስቀሉት፤

፲፰፥፴፪ ዮሐ. ፫፥፲፬፤ ፲፪፥፴፪።

እኔስ በእርሱ ላይ በደል አላገኘሁበትም" አላ
ቸው። ፯አይሁድም መልሰው፥ "እኛ ሕግ አለን፤
እንደ ሕጋችንም ሊሞት ይገባል፤ ራሱን የእግዚአ
ብሔር ልጅ አድርጎአልና" አሉት። ፰ጲላጦስም
ይህን ነገር ሰምቶ እጅግ ፈራ።

### ጲላጦስ ዳግመኛ እንደ መረመረው

፱ደግሞም ወደ ፍርድ አደባባይ ገባና ጌታ
ችን ኢየሱስን፥ "አንተ ከወዴት ነህ?" አለው፤
ጌታችን ኢየሱስ ግን ምንም አልመለሰለትም።
፲ጲላጦስም፥ "ለእኔም አትነግረኝምን? ልሰቅ
ልህ ሥልጣን እንደ አለኝ፥ ወይም ልፈታህ
ሥልጣን እንዳለኝ፥ አታውቅምን?" አለው።
፲፩ጌታችን ኢየሱስም፥ "ከሰማይ ካልተሰጠህ
በቀር በእኔ ላይ አንዳች ሥልጣን የለህም፤ ስለ
ዚህ ለአንተ አሳልፎ የሰጠኝ ሰው ታላቅ ኀጢ
አት አለበት" አለው። ፲፪ስለዚህም ጲላጦስ
ሊፈታው ወድዶ ነበር፤ አይሁድ ግን፥ "ይህን
ከፈታኸው የቄሣር ወዳጅ አይደለህም፤ ራሱን
ንጉሥ የሚያደርግ ሰው ሁሉ በቄሣር ላይ የሚ
ያምፅ ነውና" ብለው ጮሁ።

### ጲላጦስ ወደ ሊቶስጥሮስ እንደ አወጣው

(ማቴ. ፳፯፥፲፭-፴፩፤ ሉቃ. ፳፫፥፲፫-፳፭)

፲፫ጲላጦስም ይህን ሰምቶ ጌታችን ኢየሱስን
ወደ ውጭ አወጣው፤ በዕብራይስጥም ገበታ
ተብሎ በሚጠራው "ጸፍጸፍ" በሚሉት ቦታ
ላይ በወንበር ተቀመጠ። ፲፬የፋሲካም የመዘጋጀት
ቀን ነበር፤ ጊዜዉም ስድስት ሰዓት ያህል ነበር፤
ጲላጦስም አይሁድን፥ "እነሆ፥ ንጉሣችሁ" አላ
ቸው፤ ፲፭እነርሱ ግን፥ "አስወግደው! ስቀለው!"
እያሉ ጮሁ። ጲላጦስም፥ "ንጉሣችሁን ልስቀ
ለውን?" አላቸው፤ ሊቃነ ካህናቱም፥ "ከቄሣር
በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም" ብለው መለሱ።

### ጌታችን ስለ መሰቀሉ

(ማቴ. ፳፯፥፴፪-፵፬፤ ማር. ፲፭፥፳፩-፴፪)

፲፮ከዚህ በኋላ ሊሰቅሉት አሳልፎ ሰጣቸው፤
ጌታችን ኢየሱስንም ተቀብለው ወሰዱት።
፲፯መስቀሉንም ተሸክሞ በዕብራይስጥ ጎልጎታ
ወደ ተባለው ቀራንዮ ወደሚባል ቦታ ወጣ።
፲፰በዚያም ሰቀሉት፤ ከእርሱም ጋር አንዱን
በቀኝ፥ አንዱንም በግራ አድርገው ሌሎች
ሁለት ወንበዴዎችን ሰቀሉ፤ ኢየሱስንም በመ
ካከላቸው ሰቀሉ። ፲፱ጲላጦስም ጽሕፈት ጽፎ
በመስቀሉ ላይ አኖረ፤ ጽሕፈቱም፥ "የአይሁድ
ንጉሥ የናዝሬቱ ኢየሱስ" የሚል ነበር። ፳ከአ
ይሁድም ይህቺን ጽሕፈት ያነበብዋት ብዙዎች
ነበሩ፤ ጌታችን ኢየሱስን የሰቀሉበት ቦታ ለከ
ተማ ቅርብ ነበርና፤ ጽሕፈቱም የተጻፈው በዕብ
ራይስጥ፥ በሮማይስጥና በግሪክ ነበር። ፳፩ሊቃነ
ካህናትም ጲላጦስን አሉት፥ "እርሱ ራሱ 'እኔ
የአይሁድ ንጉሥ ነኝ' እንዳለ እንጂ የአይሁድ
ንጉሥ ብለህ አትጻፍ።" ፳፪ጲላጦስም፥ "የጻፍ
ሁትን ጻፍሁ" ብሎ መለሰላቸው።

### ልብሱን እንደ ተካፈሉ

፳፫ጭፍሮችም ጌታችን ኢየሱስን በሰቀሉት
ጊዜ ልብሶቹን ወስደው ከጭፍሮቹ ለእያንዳ
ንዱ አራት ክፍል አድርገው መደቡት፤ ቀሚ
ሱንም ወሰዱ፤ ቀሚሱም ከላይ ጀምሮ የተሠራ
ሥረወጥ እንጂ የተሰፋ አልነበረም። ፳፬እርስ በር
ሳቸውም፥ "ዕጣ እንጣጣልና ለደረሰ ይድረሰው
እንጂ አንቅደደው ተባባሉ፤" ይህም "ልብሶ
ቹን ለራሳቸው ተካፈሉ፤ በቀሚሴም ላይ ዕጣ
ተጣጣሉ" ያለው የመጽሐፍ ቃል ይፈጸም
ዘንድ ነው፤ ጭፍሮችም እንዲሁ አደረጉ።

### ጌታ እናቱን ለደቀ መዝሙሩ አደራ ስለ መስጠቱ

፳፭በጌታችን በኢየሱስ መስቀል አጠገብም
እናቱ፥ የእናቱም እኅት፥ የቀለዮጳም ሚስት
ማርያም፥ መግደላዊት ማርያምም ቆመው
ነበር። ፳፮ጌታችን ኢየሱስም እናቱንና የሚወ
ደውን ደቀ መዝሙሩን ቆመው ባያቸው ጊዜ
እናቱን፥ "አንቺ ሆይ፥ እነሆ፥ ልጅሽ" አላት።
፳፯ከዚህም በኋላ ደቀ መዝሙሩን፥ "እናትህ
እነኋት" አለው፤ ከዚያችም ሰዓት ጀምሮ ደቀ
መዝሙሩ ተቀብሎ ወደ ቤቱ ወሰዳት።

### ስለ ጌታችን ሞት

(ማቴ. ፳፯፥፵፭-፶፮፤ ማር. ፲፭፥፴፫-፵፩)

፳፰ከዚህም በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ሁሉ
እንደ ተፈጸመ ባየ ጊዜ የመጽሐፉ ቃል
ይፈጸም ዘንድ "ተጠማሁ" አለ። ፳፱በዚ
ያም ሆምጣጤ የመላበት ማሰሮ ነበር፤ እነ
ርሱም ሆምጣጤውን በሰፍነግ ሞልተው በስ
ምዛ ዘንግ ከአፉ አገናኝተው ጨመቁት።[፩]

---

፩ "ጨመቁት" የሚለው በግሪኩ የለም።

፲፱፥፳፬ መዝ. ፳፩፥፲፰። ፲፱፥፳፰ መዝ. ፷፰፥፳፩፤ ፳፩፥፲፭።

፴ጌታችን ኢየሱስም ሆምጣጤውን ቀምሶ፥
“ሁሉ ተፈጸመ” አለ፤ ራሱንም አዘንብሎ
ነፍሱን ሰጠ።

## ከመስቀል ስለ መውረዱ

፴፩አይሁድ ግን የመዘጋጀት ቀን ነበርና፥
የዚያች ሰንበትም ቀን ታላቅ ናትና “ሥጋ
ቸው በሰንበት በመስቀል ላይ አይደር”
አሉ፤ ጭን ጭናቸውንም ሰብረው ያወር
ዷቸው ዘንድ ጲላጦስን ለመኑት። ፴፪ጭፍ
ሮችም መጥተው ከእርሱ ጋር የተሰቀሉትን
የአንደኛውንና የሁለተኛውን ጭኖች ሰበሩ።
፴፫ወደ ጌታችን ኢየሱስም ሄደው ፈጽሞ
እንደ ሞተ ባዩ ጊዜ ጭኑን አልሰበሩም።
፴፬ነገር ግን ከጭፍሮቹ አንዱ የቀኝ፩ ጎኑን
በጦር ወጋው፤ ያንጊዜም ከእርሱ ደምና
ውኃ ወጣ። ፴፭ያየውም መሰከረ፤ ምስክርነ
ቱም እውነት ነው፤ እርሱም እናንተ ልታ
ምኑ እውነት እንደሚናገር ያውቃል። ፴፮ይህ
ሁሉ የሆነው “ከእርሱ ዐፅሙን አትስበሩ”
ያለው የመጽሐፍ ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው።
፴፯ሌላዉም መጽሐፍ ደግሞ“ የወጉትን ያዩ
ታል” ይላል።

## ወደ መቃብር ስለ መውረዱ

(ማቴ. ፳፯፥፶፯-፷፩፤ ሉቃ. ፳፫፥፶-፶፯)

፴፰ከዚህም በኋላ አይሁድን ስለፈራ በስ
ውር የጌታችን የኢየሱስ ደቀ መዝሙር የነበ
ረው የአርማትያስ ሰው ዮሴፍ የጌታችን የኢ
የሱስን ሥጋ ይወስድ ዘንድ ጲላጦስን ለመ
ነው፤ ጲላጦስም ፈቀደለት። እርሱም ሄዶ
የጌታችን የኢየሱስን ሥጋ ወሰደ። ፴፱ቀድሞ
በሌሊት ወደ ጌታችን ኢየሱስ ሄዶ የነበረው
ኒቆዲሞስም መጣ፤ ቀብተውም የሚቀብሩ
በትን መቶ ወቄት የከርቤና የሬት ቅልቅል
ሽቶ አመጣ። ፵እንደ አይሁድ አገናነዝ ሥር
ዐትም የጌታችን የኢየሱስን ሥጋ ወስደው
ከሽቱ ጋር በበፍታ ገነዙት። ፵፩በዚያም በተ
ሰቀለበት ቦታ የአትክልት ስፍራ ነበር፤ በዚያ
የአትክልት ስፍራ ውስጥም በውስጡ ሰው
ያልተቀበረበት አዲስ መቃብር ነበር። ፵፪ጌታ
ችን ኢየሱስንም በዚያ ቀበሩት፤ ለአይሁድ
የመሰናዳት ቀን ነበርና፤ መቃብሩም ለሰቀ
ሉበት ቦታ ቅርብ ነበር።

## ምዕራፍ ፳

## ጌታችን ስለ መነሣቱ

(ማቴ. ፳፰፥፩-፰፤ ሉቃ. ፳፬፥፩-፲፪)

፩ከሳምንቱም በመጀመሪያዉ ቀን ማርያም
መግደላዊት በማለዳ ገና ጨለማ ሳለ ወደ መቃ
ብር መጣች፤ ድንጋዩንም ከመቃብሩ አፍ ተነ
ሥቶ አገኘችው። ፪ፈጥናም ወደ ስምዖን ጴጥ
ሮስና ጌታችን ኢየሱስ ይወደው ወደ ነበረው
ወደዚያ ወደ ሌላዉ ደቀ መዝሙር መጥታ፥
“ጌታዬን ከመቃብር ወስደውታል፤ ወዴትም
እንደ ወሰዱት አላውቅም” አለቻቸው። ፫ጴጥ
ሮስና ያ ሌላዉ ደቀ መዝሙርም ወጥተው ወደ
መቃብሩ ሄዱ። ፬ሁለቱም በአንድነት ሲሮጡ
ያ ሌላዉ ደቀ መዝሙር ጴጥሮስን ቀድሞት
ወደ መቃብሩ ደረሰ። ፭ጐንበስ ብሎም ሲመ
ለከት በፍታዉን ተቀምጦ አየ፤ ነገር ግን ወደ
ውስጥ አልገባም። ፮ስምዖን ጴጥሮስም ተከት
ሎት ደረሰና ወደ መቃብሩ ገባ፤ ፯በፍታዉ
ንም በአንድ ወገን ተቀምጦ አየ፤ በራሱ ላይ
የነበረው መጠምጠሚያም ሳይቃወስ ለብቻው
ተጠቅልሎ አየ፤ ከበፍታዉ ጋርም አልነበረም።
፰ከዚህም በኋላ አስቀድሞ ወደ መቃብሩ የደ
ረሰው ሌላዉ ደቀ መዝሙር ገባ፤ አይቶም
አመነ፤ ፱ከሙታን ተለይቶ ይነሣ ዘንድ እንደ
አለው በመጻሕፍት የተጻፈውን ገና አላወቁም
ነበርና። ፲ከዚህም በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ተመ
ልሰው ወደ ቤታቸው ገቡ።

## ለማርያም መግደላዊት እንደ ተገለጠ

(ማቴ. ፳፰፥፱፡፲፤ ማር. ፲፮፥፱-፲፩)

፲፩ማርያም ግን ከመቃብሩ በስተውጭ እያለ
ቀሰች ቆማ ነበረ፤ እያለቀሰችም ወደ መቃብሩ
ጐንበስ ብላ ተመለከተች። ፲፪ሁለት መላእክት
ንም ነጭ ልብስ ለብሰው የጌታችን የኢየሱስ
ሥጋ በነበረበት ቦታ አንዱ በራስጌ፥ አንዱም
በግርጌ ተቀምጠው አየች። ፲፫እነዚያ መላእክ
ትም፥ “አንቺ ሴት፥ ምን ያስለቅስሻል?” አሉ
አት፤ እርስዋም፥ “ጌታዬን ከመቃብር ውስጥ
ወስደውታል፤ ወዴትም እንደ ወሰዱት አላው
ቅም” አለቻቸው። ፲፬ይህንም ተናግራ ወደ
ኋላዋ መለስ ስትል ጌታችን ኢየሱስን ቆሞ
አየችው፤ ጌታችን ኢየሱስም እንደ ሆነ አላወ

---

፩ በግሪኩ “ቀኝ” አይልም።

፲፱፥፴፮ ዘፀ. ፲፪፥፵፮፤ ዘኍ. ፱፥፲፪፤ መዝ. ፴፫፥፳። ፲፱፥፴፯፤ ዘካ. ፲፪፥፲፤ ራእ. ፩፥፯። ፲፱፥፴፱ ዮሐ. ፫፥፩-፪።

ቀችም። ፲፮ጌታችን ኢየሱስም፥ “አንቺ ሴት፥
ምን ያስለቅስሻል? ማንንስ ትሺያለሽ?” አላት፤
እርስዋ ግን የአትክልት ቦታ ጠባቂ መስሎአት፥
“ጌታዬ፥ አንተ ወስደኸው እንደ ሆነ ሄጄ ወደ
እኔ እንዳመጣውና ሽቱ እንድቀባው[፩] ወዴት
እንደ አኖርኸው ንገረኝ” አለችው። ፲፯ጌታችን
ኢየሱስም፥ “ማርያም!” አላት፤ እርስዋም
መለስ ብላ በዕብራይስጥ ቋንቋ፥ “ረቡኒ!” አለ
ችው፤ ትርጓሜዉም “መምህር” ማለት ነው።
፲፯ጌታችን ኢየሱስም፥ “አትንኪኝ፤ ገና ወደ
አባቴ አላረግሁምና፤ ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ
ሂጂና፦ ወደ አባቴ፥ ወደ አባታችሁ ወደ አም
ላኬ፥ ወደ አምላካችሁም አርጋለሁ አለ ብለሽ
ንገሪአቸው” አላት። ፲፰ማርያም መግደላዊትም
ሄደች፤ ጌታን እንደ አየች፥ ይህንም እንዳላት
ለደቀ መዛሙርቱ ነገረቻቸው።

## ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ እንደ ተገለጠላቸው

(ማቴ. ፳፰፥፲፮-፳፤ ሉቃ. ፳፬፥፴፮-፵፱)

፲፱ያም ከሳምንቱ የመጀመሪያው ቀን በመሽ
ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ አይሁድን ስለ ፈሩ ተሰ
ብስበው የነበሩበት ቤት ደጁ ተቈልፎ ሳለ ጌታ
ችን ኢየሱስ መጥቶ በመካከላቸው ቆመና፥
“ሰላም ለእናንተ ይሁን” አላቸው። ፳ይህ
ንም ብሎ እጆቹንና ጎኑን[፪] አሳያቸው፤ ደቀ
መዛሙርቱም ጌታችንን ባዩት ጊዜ ደስ አላ
ቸው። ፳፩ጌታችን ኢየሱስም ዳግመኛ እንዲህ
አላቸው፥ “ሰላም ለእናንተ ይሁን፤ አብ እኔን
እንደ ላከኝ እንዲሁ እኔ እናንተን እልካችኋ
ለሁ።” ፳፪ይህንም ብሎ እፍ አለባቸው፤ እን
ዲህም አላቸው፥ “መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ።
፳፫ኀጢአታቸውን ይቅር ያላችሁላቸው ይሰረ
ይላቸዋል፤ ይቅር ያላላችኋቸው ግን አይሰረ
ይላቸውም።”

## ስለ ቶማስ

፳፬ጌታችን ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ዲዲሞስ የሚ
ሉት ከዐሥራ ሁለቱ[፫] ደቀ መዛሙርት አንዱ
ቶማስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አልነበረም።
፳፭ሌሎች ደቀ መዛሙርትም፥ “ጌታችንን አየ
ነው” አሉት፤ እርሱ ግን፥ “የችንካሩን ምል
ክት በእጁ ካላየሁ፥ ጣቴንም ወደ ተቸነከረበት
ካልጨመርሁ፥ እጄንም ወደ ጎኑ ካላገባሁ አላ
ምንም” አላቸው።

፳፮ከስምንት ቀን በኋላም ዳግመኛ ደቀ መዛ
ሙርቱ በውስጡ ሳሉ፥ ቶማስም አብሮአቸው
ሳለ በሩ እንደ ተዘጋ ጌታችን ኢየሱስ መጣ፤
በመካከላቸውም ቆመና፥ “ሰላም ለእናንተ
ይሁን” አላቸው። ፳፯ከዚህም በኋላ ቶማስን፥
“ጣትህን ወዲህ አምጣና እጆቼን እይ፤ እጅ
ህንም አምጣና ወደ ጎኔ አግባ፤ እመን እንጂ
ተጠራጣሪ አትሁን” አለው። ፳፰ቶማስም፥
“ጌታዬ አምላኬም” ብሎ መለሰ። ፳፱ጌታችን
ኢየሱስም፥ “ስለ አየኸኝ አመንህን? ብፁዓንስ
ሳያዩ የሚያምኑ ናቸው” አለው።

፴ጌታችን ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተ
ጻፈ ብዙ ሌላ ተአምራት በደቀ መዛሙርቱ
ፊት አደረገ። ፴፩ነገር ግን ይህ የተጻፈ ኢየሱስ
እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ
እናንተ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም በስሙ የዘ
ለዓለም[፬] ሕይወትን ታገኙ ዘንድ ነው።

## ምዕራፍ ፳፩

## ለሐዋርያት በጥብርያዶስ ባሕር ስለ መገለጡ

፩ከዚህም በኋላ ጌታችን ኢየሱስ በጥብርያ
ዶስ ባሕር አጠገብ ለደቀ መዛሙርቱ እንደ
ገና ተገለጠላቸው፤ እንዲህም ተገለጠላቸው።
፪ስምዖን ጴጥሮስ፥ ዲዲሞስ የሚሉት ቶማስ፥
ከገሊላ ቃና የሆነው ናትናኤል፥ የዘብዴዎስ
ልጆችና ሌሎችም ከደቀ መዛሙርቱ ሁለት
አብረው ነበሩ። ፫ስምዖን ጴጥሮስ፥ “እኔ ዓሣ
ላጠምድ እሄዳለሁ” አላቸው፤ እነርሱም፥
“እኛም አብረንህ እንመጣለን” አሉት፤ ሄደ
ውም ወደ ታንኳ ገቡ፤ ግን በዚያች ሌሊት የያ
ዙት ምንም የለም።

፬በነጋ ጊዜም ጌታችን ኢየሱስ በባሕሩ ዳር
ቆሞ ነበር፤ ደቀ መዛሙርቱም አዩት፤ ግን
ጌታችን ኢየሱስ እንደ ሆነ አላወቁም። ፭ጌታ
ችን ኢየሱስም፥ “ልጆች ሆይ አንዳች የሚ
በላ ነገር አላችሁን?” አላቸው፤ እነርሱም፥

[፩] “ሽቱ እንድቀባው” የሚለው በግሪኩ የለም።

[፪] በግእዙ “ወእገሪሁ” የሚል ይጨምራል።

[፫] በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ “ከዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት” ይላል።

[፬] “የዘለዓለም” የሚለው በግሪኩ የለም።

፳፥፳፫ ማቴ. ፲፮፥፲፱፤ ፲፰፥፲፰። ፳፩፥፫ ሉቃ. ፭፥፭

«የለም» አሉት። ፮ጌታችን ኢየሱስም፥ «መረባ
ችሁን በታንኳዪቱ በስተቀኝ በኩል ጣሉ፤ ታገ
ኛላችሁም» አላቸው፤ ፩ መረባቸውንም በጣሉ
ጊዜ ከተያዘው ዓሣ ብዛት የተነሣ ስቦ ማውጣት
ተሳናቸው። ፯ጌታችን ኢየሱስ ይወደው የነበረ
ያ ደቀ መዝሙርም ለጴጥሮስ፥ «ጌታችን ነው
እኮ» አለው፤ ስምዖን ጴጥሮስም ጌታችን እንደ
ሆነ በሰማ ጊዜ የሚለብሰውን ልብስ አንሥቶ
በወገቡ ታጠቀ፤ ራቁቱን ነበርና ወደ ባሕር
ተወረወረ። ፰ሌሎች ደቀ መዛሙርት ግን በታ
ንኳ መጡ፤ ከሁለት መቶ ክንድ ያህል በቀር
ከምድር አልራቁም ነበርና፤ ዓሣ የመላባቸውን
መረቦቻቸውንም እየሳቡ ሄዱ።

፱ወደ ምድርም በወረዱ ጊዜ ፍሙ መርቶ፥
ዓሣም በላዩ ሆኖ፥ እንጀራም ተሠርቶ አገኙ።
፲ጌታችን ኢየሱስም፥ «አሁን ከያዛችኋቸው
ዓሣዎች አምጡ» አላቸው። ፲፩ስምዖን ጴጥ
ሮስም ወደ ታንኳ ገብቶ መቶ አምሳ ሦስት
ታላላቅ ዓሣዎችን መልቶ የነበረውን መረብ
ወደ ምድር ሳበ፤ ብዛቱም ይህን ያህል ሲሆን
መረቡ አልተቀደደም። ፲፪ጌታችን ኢየሱስም፥
«ኑ፥ ምሳ ብሉ» አላቸው፤ ከደቀ መዛሙር
ቱም አንተ ማነህ? ብሎ ሊጠይቀው የደፈረ
የለም፤ ጌታችን እንደ ሆነ ዐውቀዋልና። ፲፫ጌታ
ችን ኢየሱስም መጣና ኅብስቱን አንሥቶ ሰጣ
ቸው፤ ከዓሣውም እንዲሁ። ፲፬ጌታችን ኢየሱ
ስም ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ለደቀ
መዛሙርቱ ሲገለጥላቸው ይህ ሦስተኛ ጊዜዉ
ነበር።

## ጌታችን ጴጥሮስን ትወደኛለህ ወይ ብሎ እንደ ጠየቀው

፲፭ምሳም ከበሉ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ፡- ስም
ዖን ጴጥሮስን፥ «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥
ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን?» አለው፤ እር
ሱም፥ «አዎን፥ ጌታዬ ሆይ፥ እኔ እንደምወ
ድህ አንተ ታውቃለህ» አለው፤ ጌታችን ኢየ
ሱስም፥ «በጎቼን ጠብቅ» አለው። ፲፮ዳግመ
ኛም፥ «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ትወደኛ
ለህን?» አለው፤ እርሱም፥ «አዎን፥ ጌታዬ
ሆይ፥ እኔ እንደምወድህ አንተ ታውቃለህ»
አለው፤ «ጠቦቶቼን አሰማራ» አለው። ፲፯ሦስ
ተኛ ጊዜም፥ «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ትወ
ደኛለህን?» አለው፤ ጴጥሮስም ሦስት ጊዜ ትወ
ደኛለህን? ስላለው ተከዘ፤ «ጌታዬ ሆይ፥ አንተ
ሁሉን ታውቃለህ፤ እኔም እንደምወድህ አንተ
ታውቃለህ» አለው፤ «እንኪያስ ግልገሎቼን
ጠብቅ» አለው። ፲፰«እውነት እውነት እልሃ
ለሁ፤ አንተ ጐልማሳ ሳለህ በገዛ እጅህ ወገብ
ህን ታጥቀህ ወደ ወደድኸው ትሄድ ነበር፤ በሸ
መገልህ ጊዜ ግን እጆችህን ትዘረጋለህ፤ ወገ
ብህንም ሌላ ያስታጥቅሃል፤ ወደማትወደውም
ይወስድሃል።» ፲፱በምን ሞት እግዚአብሔርን
ያከብር ዘንድ እንዳለው ሲያመለክት ይህን ተና
ገረ፤ ይህንም ብሎ ተከተለኝ አለው።

## ስለ ወንጌላዊው ዮሐንስ

፳ጴጥሮስም መለስ ብሎ ጌታችን ኢየሱስ
ይወደው የነበረውን ያን ደቀ መዝሙር ሲከተ
ለው አየ፤ እርሱም ራት ሲበሉ በጌታችን በኢ
የሱስ አጠገብ የነበረውና «ጌታ ሆይ፥ አሳልፎ
የሚሰጥህ ማነው?» ያለው ነው። ፳፩ጴጥሮስም
እርሱን አይቶ፥ «ጌታ ሆይ፥ ይህስ እንዴት
ይሆናል?» አለው። ፳፪ጌታችን ኢየሱስም፥
«እስክመጣ ይኖር ዘንድ ብወድድስ አንተን
ምን አግዶህ፤ አንተ ግን ተከተለኝ» አለው።
፳፫ያም ደቀ መዝሙር እንደማይሞት ይህ ነገር
በወንድሞች ዘንድ ተነገረ፤ ጌታችን ኢየሱስ
ግን፥ «እስክመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድ
ድስ አንተን ምን አግዶህ» አለ እንጂ አይሞ
ትም አላለውም።

፳፬ስለዚህ ነገር ምስክር የሆነ፥ ስለ እርሱም
ይህን የጻፈ ይህ ደቀ መዝሙር ነው፤ ምስክርነ
ቱም እውነት እንደ ሆነ እኛ እናውቃለን።

፳፭ጌታችን ኢየሱስ የሠራቸው ሌሎች ብዙ
ሥራዎች አሉ፤ ሁሉ እያንዳንዱ ቢጻፍ ግን
የተጻፉትን መጻሕፍት ዓለም ስንኳን ባልቻላ
ቸውም ነበር።

ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ የዘብዴዎስ ልጅ ሐዋርያው ዮሐንስ ጌታችን በሥጋ ወደ ሰማይ ባረገ በሠላሳ ዓመት፥ ቄሳር ኔሮን በነገሠ በሰባት ዓመት በዮናናውያን ቋንቋ ለኤፌሶን ሰዎች የጻፈፍው ወንጌል ተፈጸመ። ምስጋና ለእግዚአብሐር ይሁን። አሜን።

---

፩ አንዳንድ የግእዝ ዘርዕ «መላ ሌሊቱን ደከምን፤ ምንም ያያዝነው ነገር የለም፤ ነገር ግን በአንተ ቃል እንጥላለን አሉት» የሚለውን ከሉቃስ ምዕ. ፭ ቍ. ፲፭ ያለውን አምጥቶ ይጽፋል።

፳፩፥፮ ሉቃ. ፭፥፮።